



ዋጋ 25.00 ብር

ነገረ ቅዱሳን - ፪ (ነገቅ.ቮ፪፬)

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ
መጽሐፍ



አዘጋጆች፡- መ/ር ዐሥራት ደስታ
ዲ/ን ከፍያለው ጥላሁን
እና
ዲ/ን አሰግነው ካሣ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች
ማ/መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን
ትምህርት ክፍል
፲፱፻፺፰ ዓ.ም

© ማኅበረ ቅዱሳን

፲፱፻፺፰ ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኤዲቶሪያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው።

አድራሻ

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰንበትቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Tel:- +251-11 124-61-82/83/84

Email - eoc-m-kidusan@ethionet.et

Website:http://www.eotc-mkidusan.org

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ..... ፩

ምዕራፍ አንድ

፩. ቀኖና በቤተ ክርስቲያን 1
፩.፩. ቀኖና ምንድን ነው? 2
፩.፪. የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጮች (Source of Cannon laws) 3
፩.፫. ዐበይት የቀኖና ቤተክርስቲያን ባሕርያት 4
፩.፬. በቀኖና የሚፈጸሙ ሐደቶች 6
፩.፭. የቀኖና ቤተክርስቲያን ጥቅም 7

ምዕራፍ ሁለት

፪. ቀኖና ቅዱሳን በቤተ ክርስቲያን (canonization of saints) 10
፪.፩. የቅድስና ሕይወት በቤተክርስቲያን 10
፪.፪. የቀኖና ቅድስና ዐበይት መሥፈርቶች (Criteria on canonization of saints) 11
፪.፫. በቀኖና ቅዱሳን ቅድስናን የሚረጋገጥ አስፈላጊነት 13
፪.፬. የቅዱሳን መታሰቢያቸው በቤተክርስቲያን 14

ምዕራፍ ሦስት

፫. በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ዐበይት የሚባሉ ቅዱሳንና ታሪካቸው 19
፫.፩. ከሮሚት በፊት የነበሩ ቅዱሳንና ታሪካቸው 19
ሀ. ኢትዮጵያዊው ሸንደረባ (በ፬፱ ዓ.ም) 19
ለ. አብርሃ ወአጽብሐ (ከ፫፻፲፫-፫፻፷፬ ዓ.ም) 21
ሐ. አጼ ካሌብ (ከ፭፻፳፭ - ፭፻፸፭ ዓ.ም) 27

መ. ቅዱስ ያሬድ 27
ሠ. አባ ሰላማ /ኩሎቱ ብርሃን/ (ከ፲፻፱፭-፲፻፺፱ ዓ.ም) 30
ረ. የተሰዓቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልእኮ መቅድም 31
ሰ. ተሰዓቱ ቅዱሳን 33
ሸ. ዓፄ ገብረ መስቀል 47
፫.፪ ከሮሚት እስከ አሕመድ ግራኝ 47
ሀ. ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ (በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን) 47
ለ. ቅዱስ ሐርቤ (በ፲፬ኛ መቶ ክፍለ ዘመን) 53
ሐ. ቅዱስ ላሊበላ 54
መ. ቅድስት መስቀል ክብራ 57
ሠ. ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ (በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም) 58
ረ. አቡነ ተክለ ሃይማኖት (ከ፲፭፻፳፫ - ፲፭፻፹፫ ዓ.ም) 59
ሰ. አባ ኢዮስጣቴዎስ (ከ፲፭፻፹፫-፲፭፻፺፱ ዓ.ም) 62
ሸ. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ (በ፲፭፻፺፰ ዓ.ም) 63
ቀ. ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ 68
በ. አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ (ከ፰-፲፱ መቶ ክፍለ ዘመን) 70
፫.፫. ከአሕመድ ግራኝ እስከ ዛሬ 72
ሀ. ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ 72
ለ. ፍትሮተ ክርስቶስ 77
ሐ. አቡነ መብዓ ጽዮን (በ፲፰ኛ መቶ ክፍለ ዘመን) 80
መ. አቡነ ተጠምቀ መድኅን (በ፲፭፻፲፫) 82
ሠ. ሌሎች ቅዱሳን 85

ምዕራፍ ዐራት

፬. የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪክ ምንጮች 114
፬.፩. ገድል 114
፬.፪. ስንክሳር 114
፬.፫. የአብነት ት/ቤቶች ትውፊት 115

መግቢያ

ነገረ ቅዱሳን ማለት ቅዱሳት/ ለምት ከልደታቸው እስከ ዕረፍታቸው ድረስ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ሕገ እግዚአብ ሐርን አክብረው ትእዛዙቱን ፈጽመው የኖሩና የሚኖሩ የእግዚአብ ሐር ልጆችን እንዲሁም የቅዱሳን መላእክትን ነገር የምንማርበት ትምህርት ነው። ኅገር የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የአንድነት ትምህርት ሙሉ መግለጫ ሆኖ ያገለግላል። ለምሳሌ ኅገረ ቅዱሳኑ ሲል ሃይማኖት ይዘው ምግባር ሠርተው በሥርዓት ተጉዘው እስከ ሞት ድረስ ታምነው ለተገኙ የእግዚአብሔር ልጆች እግዚአብ ሐር ክብሩን እንደገለጸላቸውና እንደሚገልጽባቸው እንዲሁም ፈቃዱን ለመፈጸም ስለሚፋጠኑት ቅዱሳን መላእክት የምንማርበት ትምህርት ነው።

ቅድስና ደግሞ የባሕርይና የጸጋ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የባሕርይ ቅድስና ፕዝበኩቱ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ማለት ቅድስናው ከርሱ የማይለይ፡- ከማንም ያልተዋሰው፥ ወይም ያልተቀ በለው፥ ማንም ሊወስድበት የማይችል የራሱ ፕዝበ ማለት ነው። ኢሳ፮፥፫፣ ራዕይ፬፮ ይህንን ቅድስናውንም ራሱ ሲናገር ‘እኔ እግዚአብ ሐር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ’ ብሏል። ዘሌ.፲፱፥፪ ስለዚህ ቅድስና የባሕርይ ፕዝበ ለሆነ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋናና ክብር እንዲሁም ስግደት ለሌላ ለማንም የማይሰጥ ነው። የጸጋ ቅድስና ደግሞ ከእግዚአብሔር በጸጋ /በስጦታ/ የተሰጠ ወይም የተገኘ ማለት ነው። ሰፍጠራን ቅድስና መገኛ ምንጩ ራሱ እግዚአብሔር ነው። ‘እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ’ ዘሌ.፲፱፥፪ በማለት ሰው ሁሉ የቅድስናው ተሳታፊ ይሆን ዘንድ በአባታዊ ቸርነቱ ሰጥቷል። የቅድስና ጥሪ ለሰው ዘር በሙሉ የተላለፈ ጥሪ ቢሆንም ዋተጠሩ ብዙዎች የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸው’ ማቴ.፳፪፥፲፬ እንደተባለው የፈጣሪያቸውን የቅድስና ጥሪ የተቀበሉና በዚህ ሕይወት የኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው።

ቅዱሳን የሚባሉት መላእክት፣ ሰማዕታት፥ ጻድቃን ሊቃውንት ናቸው። ቅዱሳን ሰማዕታት መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ

ክርስቶስ በጲላጦስ ፊት ኀኔ እውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ፥ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ። ዮሐ.፲፰+፴፯ በማለት እንደመሰከረ የርሱን አሠረፍኖት (መንገድ፣ ፍለጋ) የተከተሉት ናቸው። ቅዱሳን ጻድቃን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐርባ መዓልትና ዐርባ ሌሊት በገዳመ ቆሮንቶስ የፈጸመውን ተግባር አብነት (አርአያ) ያደረጉ ናቸው። 'ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ በነፍሱ ግን ከተጎዳ ምን ይጠቀመዋል?' ማቴ.፲፮+፳፮ የሚለውን ቃል በመረዳት በምናኔ (ዓለምን በመናቅ) ሕይወት የኖሩ ናቸው። ቅዱሳን ሊቃውንት ደግሞ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሠላሳ ዓመት ከሠላሳ ወር ሐዋርያትን በምሳሌ እየመሰለና እየተረጐመ እንዳስተማረ እርሱን አብነት አድርገው ያስተማሩ ናቸው። ሊቃውንት ወጥተው ወርደው ደክመው ስለ ቸኝ ሳይሉ ያልተመሰለውን መስለው የተመሰለውን ተርጉመው ለማስተማር መጻሕፍትን በመተርጐም መናፍቃን ሲነሡ ጉባኤ ሠርተው ተከራክረው ረትተው ያስተማሩ ቅዱሳን ይባላሉ። 'መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው' እንዲል ሮሜ.፲+፲፭። ይህ መጽሐፍ ርእሱ ነገረ ቅዱሳን ሁለት ተብሎ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንንና ቀኖና ቅዱሳንን በማስቀደም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ዐበይት የሚባሉ ቅዱሳን ታሪካቸውን በመተንተን የኢትዮጵያ ቅዱሳን ታሪክ ምንጮችን በመጠቀም ይፈጸማል።

ይህም ማለት የኢትዮጵያውያን ቅዱሳንን ዝርዝር ሳያጓድል ታሪካቸውንም በምልዓትና በስፋት አቅርቧል ማለት አይደለም። ለመግለጽም እንደመዘጋጀቱ መጠን አስከና ጠበብ ያለ መሆኑን በመገንዘብ በሌሎች የሊቃውንት መጻሕፍትና በቅዱሳት ገድል ታሪካቸውን ማጥናት፣ ገድላቸውን ማወቅና በቃል ኪዳናቸውም መጠቀም ያስፈልጋል። ይልቁንም ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ላይ ሠፊና ጥልቅ ምርምር አለመደረጉን ቤተክርስቲያናችን በሲኖዶስ ራሷን የቻለችውም በቅርብ ጊዜ መሆኑ ስለሆነችን ቅዱሳን ብዙ አለማወቃችንና ለማወቅ የሚያስፈልገንም ጥረት ቀላል አለመሆኑን ያስረዳናል። ስለዚህ ሳይሰለቹና ሳይንቁ፣ አይታወቅምም ሳይሉ የቅዱሳኑን ታሪክ ማጥናትና መመርመር ገና ያልተጀመረ ሥራ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ምዕራፍ አንድ

፩. ቀኖና በቤተክርስቲያን

ማንኛውም የቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚመራው ሐዋርያዊ በሆነ ሥርዓት ነው። ይህንን ሥርዓት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት፣ ሐዋርያትም ለተከታዮቻቸው በቃልና በጽሑፍ አስተምረዋል። ጌታችን 'ከእኔ ተማሩ' ሲል ሐዋርያት 'እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ ከእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና. . .' በማለት አብነት ሆነዋል። ፪ተሰ.፫ + ፯ በተሰጣቸው ሰማያዊ ሥልጣን ተጠቅመዋል። በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ያሉ የእመናን የከፋ ኀጢአት በፈጸሙ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዷል ነው ፩ቆሮ.፭ + ፭ በማለት ወስኖባቸዋል። በማኅበረ ሐዋርያት ሥርዓት ላይ እምነት የጐደላቸው ሐናንያና ሰጲራ በቅዱስ ጴጥሮስ ተቀጥተዋል። ሐዋ.፭ + ፩ ሐዋርያት ከሥርዓት ውጪ የሚሔዱትን መገሠጽ እንደሚገባ አስተምረዋል። 'ያለሥርዓት የሚሔዱትን ገሥጹ' ተብሎ ፩ተሰ.፭ + ፲፬ እንዲል።

የቤተክርስቲያን ሥርዓት መጠበቅ አለመጠበቅ የሚታወቀው በቤተክርስቲያን ሕገ ቀኖና ሲመዘን ነው። የቤተክርስቲያን መምህር ነኝ፣ ምሥጢራትን እፈጽማለሁ ነኝ፣ ማኅበራዊ አገልግሎትም እየሰጠሁ ነው ማለት ብቻውን አይበቃም። የምሰጠው ትምህርት፣ የምፈጽመውና የማስፈጽመው ምሥጢራት ቤተክርስቲያን፣ የምሰጠው ማኅበራዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን ሕግ የተቃኘ የተመዘነ መሆን አለበት። ያለዚያ ግን መልካም አደረግን የምንለው ነገር በቤተክርስቲያን ቀኖና (ሚዛን) ሲመዘን ቀሎ ሊገኝ ይችላል። ዳን.፭ + ፳፯ 'በሚዛን ተመዝነህ ቀለህ ተገኘህ' ተብሏል። ይህ ሰው (ብልጣሶር) ቀሎ የተገኘው ቀኖና ኦሪትን ሕገ ኦሪትን በመጣስ ንዋየ ቅዱሳቱን የእርሱ መገልገያ ስላደረገ ነው። የቤተክርስቲያን ቋሚነትም የሚመራው በሕገ ቤተክርስቲያን ነው። ሕገ ቤተክርስቲያን ስንል የሚከተሉትን ዓበይት ድንጋጌዎችን ያካትታል።

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹትን ሕግጋተ እግዚአብሔርን
ለ. በሐዋርያት ሲኖዶስ የተወሰኑትን ድንጋጌዎች
ሐ. ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሊቃውንት የወሰኑትን ቀኖና
መ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሐዋርያትን የመሰሉ (Apolistic Fathers) ብላ የተቀበለቻቸው አባቶች የደነገጓቸው ውሳኔዎችን (Creeds)
ሠ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በምትቀበላቸው ዓለም አቀፍ የቤተክርስቲያን ጉባኤዎች የተደነገጉ ድንጋጌዎችን
ሠ. በታላላቅ ገዳማት በትውፊታዊ ሥርዓት የተደነገጉ ድንጋጌዎችን
ረ. በተለያዩ ዘመናት በቅዱስ ሲኖዶስ ታይተው ከተራ ቁጥር 'ሀ' እስከ 'ሠ' የተገለጹትን ጥተተ መልኩ ዝርዝር አፈጻጸማቸው የተደነገገላቸውን የቤተክርስቲያን ቀኖናዎች (Cannons)

ከላይ የተገለጹ የቀኖና ቤተክርስቲያን ክፍሎች አንዱ ከአንዱ ጋር የተያያዘ ነው። አንዱ ለአንዱ መሠረት ነው። በዚህም ክፍል የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችን (Cannons) እንመለከታለን።

፩.፩. ቀኖና ምንድነው?

ቀኖና (Cannon) የጽርዕ /ግሪክ/ ቃል ነው። ትርጉሙ ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ፣ ፍርድ፣ ቅጣት መጠን፣ ልክ /መለኪያ/ ማለት ነው። /ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት/። የቤተክርስቲያን በዓላት፣ አጽዋማትና ሌሎች መንፈሳዊ የሆኑ አገልግሎቶች በዝርዝር በቀኖና የተወሰኑ ናቸው። ተጋድሎአቸውን የፈጸሙ ቅዱሳን ቅድስናቸው በቀኖና ተመዝኖ ይረጋገጣል። ቅዱሳት መጻሕፍት 'ቅዱሳት' የተባሉት በቀኖና ቤተክርስቲያን ታይተው ተመዝነው ነው። ከዚህ አንጻር ቀኖና የቤተክርስቲያን የሆነው ኅልውና የመለያ መለኪያ /Standard/ ነው።

፩.፪. የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጮች (Source of Cannon laws)

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ

ቁጥራቸው ሰማንያ አንድ የሆኑ አሥራው /ሥሮች- መሠረቶች/ መጻሕፍት የቀኖና ቤተክርስቲያን ዋና ምንጭ (መሠረት) ናቸው። ብዙ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችን አሰባስቦ በያዘው ፍትሐ ነገሥት የተገለጸው ይህንን ያረጋግጣል። 'ፍርድን መጻሕፍት ከብሉይና ከሐዲስ እንዲያወጡ አዘዛቸው. . .' እንዲል /ፍትሐ ነገሥት መቅድም/. በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ድንጋጌዎች አሉ። ለምሳሌ፡- በብሉይ ዘሌ.፲፪ + ፩ 'እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ተናገረው ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት። . . . በስምንተኛው ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ' ዘኁ.፮ + ፳፫ 'የእስራኤልን ልጆች ስትባርኳቸው እንዲህ በሏቸው፤ እግዚአብሔር ይባርክህ፣ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፣ ይራራልህም።' በሐዲስም፡-

- የሐዋርያትን አገልግሎት በተመለከተ (ማቴ.፲፰ + ፲፰)
- በሐዋርያት መካከል ሊኖር ስለሚገባ የእርስ በርስ ግንኙነት (ማር.፱ + ፴፭)
- ስለምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አፈጻጸም (ማር.፲፮ + ፲፮፣ ዮሐ.፫ + ፭፣ ዮሐ.፮)
- ስለ ቅዱስ ጋብቻ (ማቴ.፭ + ፴፪ ማቴ.፲፱ + ፱)
- ስለቤተክርስቲያን አገልጋዮች ሹመት፣ ስለሚያሟሏቸው መስፈርቶችና ከሥልጣን መሻር (፩ጢሞ.፫ + ፪)
- ስለቤተክርስቲያንና ስለመንግሥት ግንኙነት (ሮሜ ፲፫ + ፩)
- በክርስቲያኖችና ክርስቲያን ባልሆኑ መካከል ስላለው ግንኙነት (፩ቆሮ.፭ + ፱) እና ሌሎችም ተጠቅሰዋል።

ከላይ በምሳሌነት ያየናቸው ድንጋጌዎች ለቀኖና ቤተክርስቲያን መሠረት ናቸው። ቀኖና ቤተክርስቲያን ከላይ ለተጠቀሱት ዝርዝሮች የአፈጻጸም መመሪያ ነው። አፈጻጸማቸውም ትክክል መሆን ያለመሆን የሚመዘንበት ሚዛን ነው። ከዚህም በላይ አንዳንድ የሐዋርያት ቀኖናዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈዋል። ሐዋ.፲፭ + ፳፱

ለ. በሊቃውንት ቤተክርስቲያን በመጽሐፍና በቃል የተደነገጉ ድንጋጌዎች

በነቢያት አድሮ ብሉይ ኪዳንን፣ በሐዋርያት አድሮ ሐዲስ ኪዳንን ያጸፈ እግዚአብሔር ከቤተክርስቲያን አባቶች እንደማይለይ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። 'እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ. . .' ማቴ.፳፰ + ፳ እንዲል። ሐዋርያት እስከ ዓለም ፍጻሜ በምድር በሕይወተ ሥጋ እንደማይኖሩ የተረዳ፣ የታወቀ ነገር ነው። ቃል ኪዳኑም ከእነርሱ በኋላ ስለሚነሡ /ስለሚሾሙ/ የቤተክርስቲያን አባቶች የተነገረ መሆኑ ግልጽ ነው። 'ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ. . .' ማር. ፲፫ + ፴፯ እንዲል።

ስለዚህም በነቢያት በሐዋርያት አድሮ ሥርዓት የሠራ፣ ሕግ የደነገገ አምላክ በሊቃውንት ቤተክርስቲያንም አድሮ ሥርዓት ይሠራል። ሕግም ይደነግጋል። በሊቃውንት ቤተክርስቲያን የተሠሩ ሥርዓቶች፣ የተደነገጉ ድንጋጌዎች፣ የተጻፉ አዋልድ መጻሕፍት የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጭ ናቸው። ይህንንም የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችን የያዘው ፍትሐ ነገሥት ያረጋግጣል። 'ይህ መጽሐፍ (ፍትሐ ነገሥት) ከቅዱሳት መጻሕፍት /ከአሥራው መጻሕፍትና ከአዋልድ መጻሕፍት/ ከቤተክርስቲያን ሕጎች ልበናም ካለናቸው ላይ የተሰበሰበ መሆኑን እንረዳለን. . .' ፍትሐ ነገሥት መቅድም።

ሐ. ክርስቲያናዊ ትውፊት

በቃልና በጽሑፍ ከቀደሙ አባቶች የተወረሱ ብዙ ሕጎችና ሥርዓቶች አሉ። 'ወንድሞቻችን ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በቃላት ቢሆን ወይም በመልእክታችን ያስተማርናችሁን ወግ ያዙ' ፪ተሰ.፪ + ፲፭ እንዲል። እንደ ክርስቲያናዊ ወግ /ሥርዓት በትውፊት /በውርስ/ የተገኙ ሕጎች የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጮች ናቸው። በተለይ የኢትዮጵያ ታላላቅ ገዳማት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን በውርስ የተገኙ የብዙ ቀኖናዎች ባለቤት አድርገዋታል። ፍትሐ ነገሥታችን ትውፊት የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጭ መሆኑን ያረጋግጣል። 'ሕግ ሊቃውንት ከጻፉት የቀረው ከልቡናና ከልማድ የተገኘ እንደሆነ ተነገረ . . .' እንዲል /ፍትሐ ነገሥት የመውረስ አንቀጽ ቁጥር ፲፮፻፴፩/

በአጠቃላይ ፍትሐ ነገሥት ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን የቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጮችን ሲያጠቃልል 'ይህ መጽሐፍ (ፍትሐ ነገሥት) ከቅዱሳት መጻሕፍት፣ ከቤተክርስቲያን ሕጐችና ልበናም ካለናቸው ላይ የተሰበሰበ መሆኑን እንረዳለን። ልማድም /ትውፊት/ (የማይማሩትና ባህላዊ ሥርዓት ውርስ (ትብዓል)) ያለማቋረጥና ያለመተው በአንድነት ተነገርአል. . .' በማለት ገልጾታል። /ፍትሐ ነገሥት መቅድም/

፩.፫. ዐበይት የቀኖና ቤተክርስቲያን ባሕርያት

ሀ. ሥልጣን ባለው የቤተክርስቲያን አካል ሊሻሻሉ ይችላሉ

የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ እንደየጊዜውና እንደየሁኔታው ቀኖና ቤተክርስቲያንን ሊያሻሽል ይችላል። የቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት በጠበቀ መልኩ የጐደለውን መሙላት፣ የጠመመውን ማቅናት የቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣን ነው። ከሥርዓቱ መቀነስ (ማጉደል) ግን አይችልም። ሐዋርያትም 'እኛ ከሥራ ሁሉ ማናቸውንም ያጐደልነው ብንሆን እናንተ በሚገባ አሟሉት፤. . . ከእኛ የቀረ ምን ቢኖር እግዚአብሔር ለተገባ ሰው ይገልጠው፤ ቤተክርስቲያን ጸጥታ ወዳለው ወደብ ትመራ ዘንድ' /ፍትሐ ነገሥት መቅድም/ በማለት አረጋግጠዋል። 'ካለ ኃጥአን በንስሐ መመለስ ብዙ ዘመን ቢፈርዱ የሥራቸውን ለውጥ በሚያዩበት መጠን ማጽናናትን፣ ማቅለልን (ማሻሻልን) ለሊቃውንት ሰጥቷል. . .' /ፍትሐ ነገሥት መቅድም/።

ለ/ ፍትሕ ሥጋዊና መንፈሳዊን ያጠቃለለ ነው

የቤተክርስቲያን ቀኖናዎች ፍትሕ ሥጋዊና ፍትሕ መንፈሳዊን የተመለከቱ አንቀጾችን ያካተቱ ናቸው። ስለዚህም ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ ሰው ፍትሕን ለመስጠት ያስችላሉ። ፩ቆሮ.፮ + ፩ 'ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፈንታ ከዓመጸኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን?' ፩ኛ ቆሮ.፮ + ፪።

ሐ/ ስለሁሉ ነገር በቀኖና አልተደነገገም

በፍትሐ መንፈሳዊና በፍትሐ ሥጋዊ ሲደነገጉ የሚገኙ ዐበይት ድንጋጌዎች ተደንግገዋል። ነገር ግን በቀኖና ባይገለጽም በቅዱሳት መጻሕፍት፣ በሕገ ልቡና በአንድ ወይም በሌላ መልክ የታወቁ ናቸው። ሐዋርያት 'ወንድሞቻችን ሆይ ከእኛ የቀረው /እኛ በቀኖና ያልደነገግነውን/ መጻሕፍት ያስተምሩዋችኋል' እንዲሉ። (ፍትሐ ነገሥት መቅድም)

መ/ በአንድ ወቅት በአንድ ቦታ አልተደነገገም

የቀኖና ምንጭ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያየ ቦታ፣ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እንደ ተጻፉ ሁሉ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎችም በተለያየ ቦታና ጊዜ በተለያዩ ሰዎች ተደንግገዋል። ከኋላ የተነሡ አባቶች የቀደሙት የደነገጓቸውን ሰብስበዋል። በትውፊት ያሉትን ወርሰዋል። በጉባኤም አጽድቀዋል።

፩.፬. በቀኖና የሚረጋገጡ ሒደቶች (Canonicity)

ለመጻሕፍትና ተጋድሏቸውን ለፈጸሙ ቅዱሳን የቅድስና መዓርግ የሚሰጥበት ሒደት /ሥርዓት/ ሁለት ዓይነት ነው።

ሀ. ይፋዊ ቀኖና /official canonicity/

በየዘመኑ የነበሩ የቤተክርስቲያን አባቶች በሲኖዶስ ወስነው ለቤተ ክርስቲያን የሚያውጁት ይፋዊ ቀኖና ይባላል። በ፵ ዓ.ም በኢየሩሳሌም ከተደረገው የሐዋርያት ሲኖዶስ ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ዓለም የሚነሡ የቤተክርስቲያን አባቶች በሲኖዶስ ይፋዊ ቀኖና /ድንጋጌ/ ይደነግጋሉ። መናፍቃን ከእማኑ ይለያሉ። ለቅዱሳን መዓርገ ቅድስና ይሰጣሉ። መጻሕፍትን አሥራው፣ አዋልድ ብለው ለይተው ያውጃሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በምትቀበላቸው ዓለም አቀፍ የቤተክርስቲያን ጉባኤያት የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሁሉ ይፋዊ የቤተክርስቲያን ቀኖናዎች ናቸው።

ለ. ትውፊታዊ ቀኖና /traditional canonicity/

ቅዱስ ሲኖዶስ ለመሰብሰብ ባልቻሉባቸው የመከራ፣ የስደትና በተለያዩ ሁኔታዎች በታላላቅ የሃይማኖት አባቶች የሚደረግ ድንጋጌ ነው። በዚህም ብዙ ተጋድሎአቸውን የፈጸሙ አባቶች ቅዱስ ተብለው ተሰይመዋል። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳንና አዋልድ መጻሕፍት ቅድስናቸው የተረጋገጠው በትውፊታዊ ቀኖና ነው። ይህ ቀኖና ብዙ ጊዜ ሲኖዶስ ሕጋዊ እያደረገውና እያረጋገጠው ይሔዳል። ለምሳሌ፡- የግብፅ ቤተክርስቲያን በችግር ጊዜ ታላላቅ አበው ወስነው ያስተላለፉትን በሰላም ጊዜ የሚቀመጠው ሲኖዶስ እየወሰነ ያረጋግጠው ነበር። የእኛ ቤተክርስቲያንም ለብዙ ዓመታት ያለ ሲኖዶስ ትኑር እንጂ ሊቃውንቱ እና መናንያን አባቶች የሠሩት ሥርዓት አለ። ይህን አሁንም ትጠቀምበታለች። በሲኖዶስ መርምሮ ማጽደቅና ሕጋዊ ማድረግ ደግሞ ድንጋጌውን የበለጠ መልክ ይሰጠው ነበረ።

፩.፭ የቀኖና ቤተክርስቲያን ጥቅም

የአንዲት ቤተክርስቲያን ትምህርት ሥርዓትና ትውፊት የሚጠበቀው በቀኖና አጥርነት ነው። የቅዱሳት መጻሕፍት፣ በዓላት፣ አጽዋማት ወዘተ ዓይነት፣ ብዛትና ድንበሩ የሚወሰነው በቀኖና ነው። ይህም በአሕዛብ ፍልስፍና በሕልም ትዝታና በጥንቆላ ድርሰቱን ያቀነባበረ ሁሉ 'ይኸውላችሁ ቅዱስ መጽሐፍ . . .' እንዳይል መከላከያ ነው። ማንም ተነሥቶ 'እኔ ቅዱስ ነኝ፣ ስሙኝ ተከተሉኝ . . .' እንዳይል በሩ በቀኖና ተዘግቷል።

ቀኖና የቤተክርስቲያን የሆነውን ለመጠበቅ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሰፍር ቁጥር ለማስረከብና ሐሰቱን ከእውነት ለመለየት ዋነኛ መሣሪያ ነው። ስለዚህ ቀኖና ለቤተክርስቲያን የጥበቃዋ አጥር፣ ሰፍር ቁጥር ለማውረስ እውነተኛ ሚዛንና እውነትን ከሐሰት የመለያ የልቡና አጉሊ መነጽር ነው።

ገላ.፩ + ፮-፲ 'የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ። ነገር ግን ከሰማይ መልአክም ቢሆን እኛ

ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን ተብሎ እንደተነገረ ቀኖናችን ሰብረን እንገባለን ለሚሉት ይህን ያደርጉ ዘንድ እንደግይችሉ ተከልክለዋል።

መመሪያ I. <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ/።</u>

፩. የቤተክርስቲያንን ቀኖና ማሻሻልም ሆነ መወሰን የሚችለው ማንነው?
ሀ. የሰበካ ጉባኤ ለ. የምእመናን ጉባኤ
ሐ. ቅዱስ ሲኖዶስ መ. ቅዱስ ፓትርያርኩ

፪. ከሚከተሉት ውስጥ በቀኖና ቤተክርስቲያን ሊሰተካከል የሚችለው የቱ ነው?
ሀ. ምሥጢረ ሥላሴ ለ. ሥርዓተ ቤተክርስቲያን
ሐ. ነገረ መለኮት መ. ነገረ ማርያም

፫. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ በቀኖና ቤተክርስቲያን ሊወሰኑ (ሊሻሻሉ) የሚችሉትን ለይ/ጽ/።
ሀ. በዓላትና አጽዋማት
ለ. መታሰቢያ የሚገባውን ቅዱስ ወይም የሚገባትን ቅድስት መወሰን
ሐ. የቤተ መገሪያዎችን መሰየት
መ. ልምከሱ አዕማደ ምሥጢራት
ሠ. የምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አፈጻጸም

መመሪያ II. <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ/።</u>

፩. ቀኖና ቤተክርስቲያን ምንጯ መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስም የተወሰነው በቀኖና ቤተክርስቲያን ነው።
፪. በቀኖና ቤተክርስቲያን ያልተቀመጠ /ያልተደነገገ/ ሥርዓት የለም።
፫. ቀኖና ቤተክርስቲያን ወደፊት ሊጨመርበትም ሆነ ሊቀነስለት ይችላል።

መመሪያ III. <u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የተስፋፋ መልስ ስጥ/ጭ/።</u>

፩. የባሕርይ ቅድስና ከጸጋ ቅድስና በምን ይለያል?
፪. ሕገ ቤተክርስቲያን የሚያካትታቸውን ዐበይት ድንጋጌዎች ዘርዝር/ሪ/።
፫. ቅዱሳን ቅድስናቸው ተመዝኖና የሚረጋገጠው በምንድን ነው?

ምዕራፍ ሁለት

፪. ቀኖና ቅዱሳን በቤተክርስቲያን /canonization of saints/

፪.፩. <u>የቅድስና ሕይወት በቤተክርስቲያን</u>

ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት። ከሐዋርያት በኋላ የተነሡ ሊቃውንት "ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ንባኤ ዘሐዋርያት" በማለት በቅድስናዋ ማመን በቅድስናዋም መታመን ከሃይማኖት መመከሪያዎች (መግለጫዎች) አንዱ እንደሆነ ደንግገዋል። በሥርዓተ ቅዳሴም "ውስተ ሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን" የሚለው የቤተክርስቲያንን ቅድስናዋን በአናትነቷ አምነን በልጅነት መንፈስ እንድንጠራ ሐዋርያት አስተምረዋል። የቤተክርስቲያን ምሳሌ የነበረ ችው አሪታዊት ቤተ መቅደስና በውስጧም ያለው ቅዱስ እንደሆነና በአምነት የሚያስባቸው ሁሉ እንደሚቀደስ ተጽፎአል። "መመናኛውን ድንኳንሽ የምስክሩን ታቦት . . . ሁሉንም ትቀድሳቸዋለህ። ቅድስተ ቅዱሳን ይሆናሉ የሚነካቸውም ሁሉ ቅዱስ ይሆናል" ዘጸ.፴÷፳፱-፴ እንደተባለ።

በሐዲስ ኪዳንም የቤተክርስቲያን ምሳሌ የሆነውን ደብረ ታቦርን ሐዋርያት "ቅዱሱ ተራራ" ፪ጴጥ.፩ ÷ ፲፰ በማለት ጠርተውታል። ክርስቶስ መከራ የተቀበለው እርሷን ለመቀደስ ነው። "ክቡሱ ጋር እንጽዋ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ" ኤፌ.፭ ÷፳፮ እንዲል። ቤተክርስቲያን ቅድስናዋ ለዓለም የተረፈ ነው። ብዙዎችን ቀድሳለች። ዛሬም ትቀድሳለች። ወደ ቅድስና የመጥራት፣ በቅድስና ሕይወት መጠበቅና መንከባከብ የቤተክርስቲያን ሥራ ነው። ተጋድሎ አቸውን በምድር ለፈጸሙት ልጆቿዋም በቀኖና መዝና ቅዱስ" የሚል መዓርግ ሰመስጠት ሥልጣን አላት። ይህም ሥልጣን ከክርስቶስ የተገኘ ነው።

ወደ ቅድስና ሕይወት ሰውን በትምህርት እንድትመራ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ሥልጣን ተሰጥታታል። /ማቴ.፳፰ ÷ ፲፰/ ማንም

ቤተክርስቲያን የቅድስና መዓርግ ሰጥታ ቅዱስ እገሌ የምትሰው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በማየት /በመመዘን/ ነው።

ሀ. <u>ሰማዕትነት በመክፈል</u>

በአለውያን ነገሥታት ፊት ሃይማኖታቸውን መስክረው፣ መከራ መስቀሉን ተሸክመው ለቤተክርስቲያን የዘላለም ምስክር በመሆን ያበረከቱትን አስተዋጽኦ በመመዘን የቅድስና መዓርግ ይሰጣል። በኔሮን፣ በድዮቅልጥያኖስ፣ በመክስምያኖስ ዘመነ መንግሥት ለእምነታቸው፣ ለቤተክርስቲያን ብለው በመንኩራኩር ተፈጭተዋል፣ እንደ ፈትል ሰም ተጠምተው (ተነክረው) በእሳት ተቃጥለዋል፣ በመጋዝ ተሰንጥቀዋል፣ ስለዚህም በደማቸው ቀለምነት በአጥንታቸው ስባሪ ብዕርነት የቤተክርስቲያንን ታሪክ እና ትምህርተ እምነት ያጸፉና ያደመቁ ልጆቹዋን ቤተክርስቲያን ቅዱስ ብላ ታከብራለች። በኢትዮጵያ በዮዲት፣ በግራኝ፣ በአፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት፣ በፋሽስት ጣልያን ለሃይማኖትነትን የከፈሉ አባቶችም ሰማዕታት ናቸው።

ለ. <u>በገደግዊ ሕይወት በመጽናትና ተአምራት በማድረግ ያበረከቱት አስተዋጽኦ</u>

በክርስቶስ ፍቅር ተስቦው የላመ የጣመ ሳይበሉ፣ የሞቀ የደመቀ ሳይለብሱ በበረሃ ወድቀው፣ በሠገር ተንከራትተው፣ ጻዋ ጥሰው፣ ጠፃ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ያበረከቱት አስተዋጽኦ አንዱ የቀኖና ቅዱሳን መመዘኛ ነው። የቅድስና ባለቤት እግዚአብሔርም "ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኝኝም ነገር ስለሚመርጡ ቃልኪዳኔንም ስለሚይዙ ሸንደረቦች እንዲህ ይላል፡- በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች የሚበልጥ መታሰቢያ ስም እሰጣቸዋለሁ፡ የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ" ኢሳ.፶፮ ÷ ፬-፭ እንዲል ስለ ቅዱሳን መታሰቢያ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ ለቅዱሳን በቤቱና በቅጥሩ ውስጥ መታሰቢያ ሰጥቷል። "እግዚአብሔር ሰንበቴን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኝኝም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔን ስለሚይዙ ሸንደረቦች እንዲህ ይላል። በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች የሚበልጥ መታሰቢያ ስም እሰጣቸዋለሁ። የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ . . . ኢሳ. ፶፮ ÷ ፬። በቤቴና በቅጥሬ ሲል የሚነተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ሀ. <u>በሕንፃ ቤተክርስቲያን</u>

ቤተክርስቲያን ቤተ እግዚአብሔር ናት። እግዚአብሔር ዊቴ ብሎ ጠርቷታል። ዊቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላል" ኢሳ.፶፮ ÷ ፯፣ ማቴ.፳፩÷ ፲፫። የክርስቶስም አካል ናት። ኤፌ.፩÷ ፳፫ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቤት ተብላ በስሙ ትጠራለች። ይህንም እግዚአብሔር ለሶሎሞን ቤተመቅደስ በሠራ ጊዜ በቃል ኪዳን አረጋግጦለታል። "ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ። . . ." ፪ነገ. ፮ ÷ ፲፮ ነገር ግን ቤተ መቅደሱ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መሠረት ቅዱሳንን ለማሰብ በእነርሱ ስም ይሰየማል። የቅዱስ ሚካኤል፣ የቅዱስ ገብርኤል፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ የቅድስት ድንግል ማርያም፣ የእቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ወዘተ በመባል በስማቸው ይሰየማል። ይህ ቤቱ የእግዚአብሔር ሲሆን መታሰቢያነቱ ለቅዱሳን መሆኑን ያመለክታል።

ለ. <u>የመታሰቢያ መጽሐፍ በመጻፍ</u>

የእግዚአብሔር ቤት በቅዱሳት መጻሕፍት የተሞላች ቤተ መጻሕ ፍት ናት። አሥራው መጻሕፍትም ይሁኑ አዋልድ መጻሕፍት በመን ፈስ ቅዱስ መሪነት በቅዱሳን የተጻፉ ናቸው። ስለ ቅድስናቸውና መታሰቢያቸውም ይናገራሉ። ሰማርያም እንተ ዕፍረትም የተነገረው ይህንን ይገልጣል። "እርሷ በሰውነቱ ላይ ይህን ሽቱ አፍስሳ ለመቃ ብሬ አደረገች። እውነት እላችኋለሁ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በሚሰበክበት እርሷዋ ያደረገችው ዳግም ለእርሷ

ተነሱ አስተማሪ መሆን አይችልም፣ አልታዘዙምና። ያዕ.፪ ÷ ፩ "ወሊይኩኑ እም ውስቴትክሙ ብዙኃን መምህራን፣ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ።" በምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የቅድስና ሕይ ወትን ለማልበስና ለመገለባበጥ ቤተክርስቲያን ታገለግለች። ማቴ.፳፰÷ ፲፰፣ ማቴ.፲፮ ÷ ፩፣ ዮሐ.፫ ÷ ፭/ የማይታዘዙትን የመሠጽ /የመቅጣትና አውግዞ የመለየት ሥልጣን አላት። /ሐዋ.፭ ÷ ፩፣ ማቴ.፲፰ ÷ ፲/። ቤተክርስቲያን በሚታወቀው መሠረት፣ ቦታ የእርሷ የሆነውን ትምህርት መማር ይገባታል። የቅድስና መንገድ መጀመሪያ ትምህርት ነውና። የቤተክርስቲያን ምሥጢራትን መፈጸም ለቅድስና ሕይወት ሰማያዊ ጸጋ ማግኛ መሣሪያ ነው። በሕይወተ ሥጋ ሳለ በትምህርት ጠርታ አትርባ በምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ተገልባበጠ እንደምትጠፋ ሁሉ ተጋድሎአቸውን የፈጸሙትን በቀኖና መዝና መዓርገ ቅድስና ትሰጣለች።

፪.፪. <u>የቀኖና ቅድስና ዐበይት መሥፈርቶች /Criteria on canonization of saints/</u>

ገድላቸውን ለፈጸሙ ከዕረፍታቸው /ከሞታቸው/ በኋላ ሥራቸው ተመዝኖ መዓርገ ቅድስና ተረጋግጦ ይሰጣል። ይህም በይፋዊ ቀኖና ወይም በትውፊታዊ ቀኖና ሊሆን ይችላል። ሐዋርያ ትም ጲጵስቅለያ በተባለ መጽሐፋቸው በ ፹፮ኛው አንቀጽ ሰማዕታት ይኸኑ በነቢኤሙ ክፉራነ፤ ሰማዕታት በአናንተ ዘንድ የከበሩ ይሁኑ በማለት ቀኖና (ሥርዓት) ሠርተዋል። ዕጩ ሆኖ የቀረበው ሰው ቅዱስ ተብሎ ከመሰየሙ በፊት ዐበይት መስፈርቶች መኖራ ከፈሉን ወይም ሁሉንም ሚሟሉ መረጋገጥ አለበት።

ሀ. <u>ሃይማኖት በመጠበቅና በማስጠበቅ ያበረከተው አስተዋጽኦ</u>

ኃይለ ቃል መገኘ፣ ትርጓሜ አልጉቶ መጻሕፍት ጽፎ ወይተ ራሱንና ምእመናንን በመጠበቅ ያደረገው አስተዋጽኦ ይመዘናል። በኒቅያ፣ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን ጉባኤያት መናፍቃንን አውግዘው ሊቃውንት ያስፈሩትን ቀኖና ቤተክርስቲያን የጻፉትንና ለምእመናን የሃይማኖት መሠረተ የሆነውን ሃይማኖተ አበው የዘረጋጁትን አባቶች

በኢትዮጵያ አባ ዮሐኒ፣ አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አባ ኢየሱስ ሞዓ፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ዐሥራ ሁለቱ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት /፲፪ቱ ንቡራነ ዕድ/ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ በማንበር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ።

ሐ. <u>የተሰጠዩ መንፈሳዊ አገልግሎት በመፈጸም ያበረከቱት አስተዋጽኦ</u>

ቤተክርስቲያን በማደራጀት በጊዜያቸው፣ በጉልበታቸው፣ በዕውቀ ታቸው፣ በሥልጣናቸው ወዘተ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በሚገባ ይታ ያል። በዚህም ከምእመናንና ከነገሥታት ብዙዎች ለቅድስና መዓርገ በቅተዋል።

፪.፫. <u>በቀኖና ቅዱሳን ቅድስናን የማረጋገጥ አስፈላጊነት</u>

ቅዱሳንን ቅዱስ ብሎ በቀኖና መመዘን አስፈላጊነት የሚጉላው ቅዱሳን ትኅንት፣ ዛሬና ነገ ለቤተክርስቲያን ካላቸው ጥቅም ነው። ከእነዚህም የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

ሀ. ቅዱሳን የቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና፣ ትው ፊትን ለይተው በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት በመጽሐፍ ጽፈዋል። የቅዱሳንን ቅድስና በቀኖና መወሰን የመጻሕፍቶቻቸውን ቅድስና የመወሰን አንዱ አካል ነው።

ለ. የከፈሉት ሰማዕትነት፣ የተቀበሉት መከራ፣ ያሳዩት ትዕግሥትና ጽናት ለምእመናን ያለውን አርአያነት በቃልና በጽሑፍ ለማስተ ማር ማንነታቸውን መመዘን ያስፈልጋል። "እኔ ክርስቶስን እንደ ምመስል እኔን ምሰሉ. . ." እንዲል ፩ኛቆሮ.፲፩ ÷ ፩።

ሐ. ከእግዚአብሔር ያገኙትን የቃል ኪዳናቸውን በረከት በተለያዩ መንገድ ምእመናን እንዲጠቀሙ ለማድረግ። ምሳ.፲ ÷ ፮

መ. የነበሩበት ዘመን፣ ያበረከቱት አስተዋጽኦና አጠቃላይ ሁኔታዎች በወቅቱ የነበረውን የቤተክርስቲያን ሁኔታ ስለሚያሳይ ታሪክቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ አካል በመሆኑ።

ከላይ በተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶች ቅዱሳንን በቀኖና መዝኖ ቅድስናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ሰይጣን የብርሃን

መልአክ መስሎ እንዲይገባ መከላከያ ነው። ተኩላዎች በጉቾን መስ ሰው እንዲቀላቀሉ ይጠብቃል። ምእመናን በክርስቶስ የወይን ግንድ ነት ላይ ቅርንጫፍ በመሆን ብዙ ፍሬ ያፈሩ የሃይማኖት አባቶቻ ቸውን እንዲያውቁና እንዲጠቀሙ ያስችላል። ቤተክርስቲያን መታሰቢ ያቸውን ሰይታ ለመፈጸም ያስችላታል።

፪.፬. <u>የቅዱሳን መታሰቢያ በቤተክርስቲያን</u>

እግዚአብሔር በደሙ የዋጃት ቤተክርስቲያን በቅዱሳን ትምህ ርት፣ ጸሎትና የቅድስና አገልግሎት የታጠረች ናት። የቤተክርስ ቲያንና የቅዱሳን ሕይወት የተሰናሰለ ነው። አይለያዩም። ቅዱሳን በእምነታቸው፣ ለቤተክርስቲያን በርጥብ ቆዳ ተጠቅልለው ለአውሬ ተጥለውላታል። ተርበው ቅርሷን ጠብቀውላታል። ጨለማ እንዲይ ርካት እንደፈትል ሰም ተጠምተው (ተነክረው) እንደ ሻፍ በርተው ሳታል። ትምህርቷን ከትውልድ ትውልድ ሰማሸጋገር በተለምና በወረቀት ብቻ ሳይሆን በደማቸው በተሰበረ አጽማቸው ሞምር ጀፈዋል። የሰይፍን ሀብል በአንገታቸው በእጅቱት (ምስጋና) አጥልቀዋል። በዚህ ሁሉ ክርስቶስን መስለዋል። ክርስቶስ ቤተክርስ ቲያንን ለመቀደስ ራሱን ለመሰዉ አሳልፎ እንደሰጠ (ኤፌ.፭ ÷፭ ፭)

ቤተክርስቲያንም የቅዱሳንን ውለታ አትረሳም። በእጸደ ሥጋ ያሉትን ቅዱሳንን ማገልገል ያረፉትን ደግሞ ማክበር እንደሚገባ ከእግዚአብሔር ተምራለችና። "እግዚአብሔር ቅዱሳንን ለላንሰገላችሁ፣ እስከ አሁንም ስለምታገለግሏቸው፣ ያደረጋችሁትን ሥራ ሰስመም ያላቸሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዐመጸኛ አምላክ አይደለምና" ዕብ.፮ ÷ ፲ እንዲል። ስለ ቅዱሳን ተርካ ቤተክርስቲያን አትሰለችም። "ስለነቢያት ሁሉ እንዲልተርከ ጊዜ ያጥረኛል. . . ." ዕብ.፲፩ ÷፴፪ እንዲል። በስንክሳር፣ በተአምረ ማርያም፣ በገድላት፣ በድርሳናት የተዘረዘረው ለትምህርት እንዲሆን ከብዙ ባጥቂቱ ነው እንጂ ገድለ ቅዱሳን ተጽፎ አያልቅም። ቅዱሳን በእጸደ ሥጋ (በዚህ ዓለም ሳለ) በእጸደ ነፍስ ከቤተክርስቲያን አይለ ዩም። ሁሉም ሥራ ይሠራሉ። ይህንን ሥራቸውን ጽፎ መጨረስ አይቻልም።

መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል. . .› ማቴ.፳፮ ÷ ፲፫ እንዲል። የቅዱሳን ልደታቸው፣ ዕረፍታቸው፣ ተጋድሎአቸውና ያደረጉት ሁሉ መታሰቢያ እንዲሆናቸው በእግዚአብሔር መንፈስ አጋዥነት በአንድ በሉላም መልክ በመጽሐፍ ይጻፋል። ስለቅዱሳን ሰመተረክ ጊዜና ቦታ አይ በታም። ጊዜ ያጥርብኛል. . .› ዕብ.፲፩ ÷፴፪ እንደሚለው። በተለምረ ማርያም ስለ እመቤታችን፣ በድርሳናት ስለመላእክት፣ በገድላት ስለ ጻድቃን ሰማዕታት፣ በሐዋርያት ሥራ ስለ ሐዋርያት በሃይማኖተ አበው፣ በስንክላር፣ ወዘተ የተጻፈውን ከብዙ በጥቂቱ ነው እንጂ ተጽፎ አያልቅም። በአጸደ ሥጋም በአጸደ ነፍስም በቤተክርስቲያን ሁሉ ሥራ ይሠራሉና።

የተጻፉ የመታሰቢያ መጻሕፍትን ቤተክርስቲያን አክብራ ትጠብቃለች። ገስትምህርት፣ ለጸሎት፣ በሽተኞችን ለመፈወስ፣ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን ለማግኘት ትጠቀማባቸዋለች። ፪ጢሞ.፫ ÷ ፲፮ "ሃእግዚአብሔር መንፈስ ያሰበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል" የጽድቅ ጉዳናን እንዴት መሔድ እንዳለብን በግልጽ ያስተምሩናልና ለትውልዱ ሁሉ የቅዱሳን ታሪክ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ። የቅዱሳን ብቻ ሳይሆን የቤተክርስቲያን ታሪክ ምንጭ፣ የሀገርም ቅርስ ናቸው።

ሐ. <u>የተሰያዩ መታሰቢያዎችን በመሰየም</u>

በእግዚአብሔር ቤትና በቅጥሩ ለየት ያለ ስም ከማግኘታቸውም በላይ በቤቱ የሚኖሩ ምእመናን፣ መንፈሳውያት ማኅበራት፣ የፀበል ቦታዎች፣ ቀናትና ዓመታት በቅዱሳን ስም ይሰየማሉ። ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ወልደማርያም፣ ኃይለሚካኤል፣ ማኅበረ ማርያም፣ የቅዱስ ሚካኤል ፀበል፣ ወዘተ እንደሚባል። መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተቋማት በስማቸው ሊጠሩ ይችላሉ። ከማቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ፣ በተለያዩ ቦታዎች የወደቁ የሰማዕታትን ዐፅም ሰብስባ (አፍልሳ) በክብር ትጠብቃለች። ዐፅማቸው ሥራ እንደሚሠራ ታስተምራለች። ሙት ያስነሣውን የኤልሳዕን ዐፅም አብነት በማድረግ። ፪ነገሥ.፲፫ ÷፳

፪. የቅዱሳን መታሰቢያ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ገድለ ጊዮርጊስ
ሰ. ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን
ሐ. የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጠበል
መ. ወሰተ ማርያም
ረ. ጸናጽል

መመሪያ ፲. <u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ስጥ/ጭ/።</u>

፩. አንድ ሰው "ቅዱስ ተብሎ ለመሰየም ምን ምን መሥፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል?

፪. ቅዱሳንን ቅዱስ ብሎ በቀናና ቤተክርስቲያን መመዘን ለምን አስፈለገ?

፫. የሚከተሉትን ሁለት ሐሳቦች በማየት ትክክለኛውን በመምረጥ "ምክንያትህን /ሽን/ ስጥ/ጭ/።
ሀ. "አንድ ሰው ምንም ጽድቅ ቢሠራ በሕይወተ ሥጋ እያለ በቅድስና መዓርግ ፈጽሞ ሊጠራ አይገባውም"
ለ. "አንደ ፈቃደ እግዚአብሔር ጸንቶ የሚኖር፣ ድንቅ ተዓምራትን የሚሠራና ጸጋ እግዚአብሔር የወረሰ ሰው ከዕለተ ሞቱ አስቀድሞ በቅድስና መዓርግ ሊጠራ ይችላል"

ቅዱሳን ለቅድስና የበቁባት ቤተክርስቲያን ናትና። እነርሱ ስለቤተክርስቲያን ሁሉን ትተዋል። "እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ . . .› ማቴ. ፲፱ ÷፳፯ እንዲል። የቤተክርስቲያን አምላክም በቤቱ በቤተክርስቲያንና በሰማያዊት ኢየሩሳሌምም እንግሶአቸዋል። ብዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብር ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ. . .› ማቴ. ፲፱ ÷፳፰ እንዲል። በዙፋን የሚቀመጥ ንጉሥ ነው። ቅዱሳን በእግዚአብሔር ቤት ነገሥታት ናቸው። በእግዚአብሔር ቤትና በትጥሩ ባለ ነገር ሁሉ ይከበራሉ፣ ይነግሣሉ። ቤተክርስቲያንም ወደ ቅድስና የጠራቻቸውን፣ በቅድስና ሕይወት የተንከባከበቻቸውንና ተጋድሎአቸውን ሲፈጽሙ በተናና መዝና መዓርገ ቅድስና ትሰጣለች። ቅዱሳንም በግሉት ሰይግ ታከብ ራቸዋለች። በእግዚአብሔር ቤት ና በትጥሩ ባለ ነገር ላይ ታነግ ግሰች። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በተናና መዝና ከላይ በተገለጹ መንገዶች የምታከብራቸው በርካታ ቅዱሳንን አፍርታለች። በኢትዮ ጵያ ቤተክርስቲያን በዋናነት ቅዱሳን ተብለው የሚከበሩ በምዕራፍ ሂስት ላይ ተርዝዋል።

መመሪያ ፯. <u>ስሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ/።</u>

፩. ከሚከተሉት ውስጥ በተናና ቅዱሳን ቅድስናን ለማረጋገጥ የሚያስ ፈልገው ለየትኞቹ ነው?
ሀ. የቅዱሳት መጻሕፍትን ቅድስናን ለመወሰን
ለ. የቅዱሳንን አርኢያነት ለመከተል
ሐ. የቅዱሳንን ብዛት ለመወሰን
መ. ለቤተክርስቲያን ታሪክ ጥናት
ሠ. ከቅዱሳን ቃል ኪዳን ለመጠቀም
ረ. ከሐሰተኞች ቅዱሳን ለመጠበቅ

ምዕራፍ ሦስት

፫. <u>በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዐበይት የሚባሉ ቅዱሳንና ታሪካቸው</u>

፫.፩. <u>ከሮዲት በፊት የነበሩ ቅዱሳንና ታሪካቸው</u>

ሀ. <u>ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ (በቀሲ ዓ.ም)</u>

ኢትዮጵያውያን ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሕገ እግዚአብሔር ይመሩ፣ በሥርዓተ አሪት ይተዳደሩ እንደነበር አያሌ የጽሑፍና የአርኪዎሎጂ ምስክሮች ተርዝዋል። ከሁሉም በላይ ምስክሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ኢትዮጵያዊቱ ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገችው ጉዞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቧል። ፩ኛነገ ፲፥ ÷ ፩፣ ፪ኛዜና. ፱ ÷ ፩ ከዐርባ ስድስት ጊዜ በላይ ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ የሠፈረላት ሀገር ኢትዮጵያ ናት። ዘመነ ብሉይን ከዘመነ ሐዲስ ያገናኙ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪክም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመዝግቧል። ከእነዚህም መካከል ኢትዮጵ ያዊው ጃንደረባ አንዱ ነው። የሐዋ. ሥራ ፰ ÷፳ ይ-፴፰።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን እንደ አስራኤላውያን ልማድ በየዓመቱ ለበዓለ ፋሲካ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር። ጃንደረባውም ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰገድ የመጣው በአባቶቹ ሥርዓት መሠረት ነው። በዚያን ዘመን ጉዞ ኢየሩሳሌም ለመድረስ ፸፪ ማይልስ መጓዝን ይጠይቅ ነበር። በዓለ ሃምሳን አክብሮ ወደ ሀገሩ ሊመለስ የነቢዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። ኢትዮጵያውያን መኾም ቢሆን ከእግዚአብሔር መሰየት አይወጣምና የበረሃው መቀት ሳያስቅቀው በሠረገላው ውስጥ ሆኖ የነቢዩን መጽሐፍ ያነብባል። ነገር ግን የሚያነብበው የትንቢት ቃል ሊገባው አልቻለም ነበር። የተሠወረ ውን መግልጥ ልማዱ የሆነው እግዚአብሔር ወንጌላዊው ፊልጶስን ለጃንደረባው ላከለት።

"እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ። ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና። ትውልዱንስ ማን ይናገራል። የሚለውን በትንቢተ ኢሳይያስ ፶፫ ÷ ፯ የተጻፈውን ቃል አስምቶ ሲያነብ አገኘው። ፊልጶስም በውኑ የምታነበውን ታስተውሰዋ ለህን? ሲል ጠየቀው። ጃንደረባውም በተሰመደው የኢትዮጵያውያን ትሕትና ሞሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል ሲል መለሰ ለት። የፊልጶስን በሥጋ ተራ ደኅማ መሆን ሳይንት ወደ ሠረገላው እንዲወጣና አብሮት እንዲቀመጥ ጋበዘው።

ፊልጶስ ከመነሻ እስከ መድረሻ ዘርዝር ወንጌልን ሰበከለት። ጃንደረባውም አመነ። ወደ ወንዝ በደረሰም ጊዜ ጃንደረባው እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ማን ነው? ሲል ጠየቀ፣ ፊልጶስም ሞፍ ጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል አለው። ስብኩዎች ለማመን የሚያስቸግራቸው ንጽሕት እምነት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝና ሆነ እምናለሁ ሲል መሠከረ። ከኢየሩሳሌም ፹ ማይልስ ርቀት በምትገኘው በጌት ሳርን እና በከብርን መካከል ባለው ኮረብታ ሥር በሚመነጨው ወንዝ ሲደርሱም አጠመቀው።

በእንዳንድ የጥንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥራኞች ዝተጠመቀ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በዛፉ ወረደ የሚል ሐረግ ተጽፏል። /Lives of the most Eminent Fathers of the church P. 87/ ቅዱስ ጀሮም /ዮርም/ የተባለው አባት ሞኢትዮጵያ ሐዋርያ በማለት ይጠራዋል። ጃንደረ ባው ወደኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ አስተደግ ንግሥት ሕንደኬ በኋላም የቤተ መንግሥቱ ሰዎች ተጠመቁ። ከአክሱም ቀጥሎ ወደ የመን ከዚያም አልፎ ወደ ፕርሽያ ተጓዘ። በአነዚያም ሀገሮች ወንጌልን ከሰበከ በኋላ ወደ ሕንድ ተሻገረ የመጨረሻ ሀገሬ ስብኩቱ ጥንት ታፕሮባና /Taprobana/ ዛሬ ሲሎን የምትባለው ደሴት ናት። በዚያ ወንጌልን ሲያስተምር አረማውያን በጠላትነት ተነሥተውበት በሰማዕትነት ዐረፈ።

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም በተሻሞ ቆሞ ራእዩን ተረጕመላት። እንዲሁም አላት። ያሸበት ዛፍ ወንጌል ናት፣ ዛፍሞ የተተከለችባት ተራራም ኢትዮጵያ ናት፣ የዛፍሞ ፍሬ ሃይማኖት ነው፣ ምድርን ያለበሱ ቅርንጫፎችሞም መምህራን ናቸው፣ ብርሃን ለብስ መለላሱቹን በዛፍሞ ግራና ቀኝ ሲያቆማቸው ያሸሸው ሰውም ዕላማ ከግቱ ብርሃን ተብሎ የሚጠራው ፍሬምናጦስ ነው። በእጁ የያዛት የወርቅ ዘንግ ጥምቀት ናት፣ እነዚያም ሁለቱ መለላሱች ልጆችሽ ናቸው፣ በመለላሱ የሚወጡ የሚወርዱ ሰዎች ምእመናን ናቸው። የሚበሉትም ፍሬ፣ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ብሎአት ከአርሷ ተሰወረ።

በተመሳሳይ ሁኔታም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ለንጉሡ በራእይ ተገልጾ "ንጉሥ ሆይ እግዚአብሔር የሰጠህን እነዚህን ፅንቋዎች እንካ ተቀበል" ብሎት ተሰወረ። እግዚአብሔር ይሁን ብሎ የወደደውና የፈቀደው ሁሉ አይቀሬምና እግዚአብሔር ንግሥት ሶፍያንና ንጉሥ ታዜርን በዘረአት ስለጉብኝ ሶፍያ ደነሰች። የጽንስዋ ወራት በተፈጸመ ጊዜም ታኅሣሥ ፩፱ ቀን በ፲፻፲፱ ዓ.ም መንታ ልጆችን ወለደች። ሕፃናቱ ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ እንደ አዋቂ ሰው በፍትር ተጠምደው አንዱ ለሌላው በማሰብ ጡት እየያዙ እንደኛው ሰሁለተኛው ይሰጥ ነበር። እንደ ሕፃናት ፀባይ አላሰቀሰሙ። ነገር ግን "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዮ የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን እያሉ ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑ ነበር።

እንደ ሙሴ ሥርዓትም ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱአቸው እግዚአብ ሔር ተግዳሮትን /ሽመጥን/ ከእኛ አራቱ ሲሉ ስማቸውንም አዝዞት ብለው ጠሯቸው። አዝዞት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ በብፅዓት የተወለዱ ስለነበር በተወለዱ በአምስት ዓመታቸው በታላቅ ክብርና ሥነ ሥርዓት ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፣ ኑርእቸውና ዕድገታቸውም በቤተ መቅደስ ሆነ። መጻሕፍተ አሪትንም እየተማሩ አደጉ።

ለ. <u>አባቶቻ ወልደብሐ ስለሞገዱ ጉዳይ</u>

ቅዱሳን ነገሥታት አብርሃ ወአጽብሐ፣ አባታቸው ታዜር እናታቸው ሶፍያ /አህየዋ/ በቅድስና የሚኖሩና እግዚአብሔርን በቅድስና የሚያገለግሉ፣ ነገር ግን ልጅ ያላገኙ መካኖች ነበሩ። ስለሆነም ጌታ ሆይ ደስ የሚያሰኘህ በትእዛዝህም የሚኖር ልጅ ስጠን እያሉ እግዚአብሔርን ይለምኑ ነበር።

ከዕለታት በአንድ ቀን ስለእግዚአብሔር ቸርነት ሲነጋገሩ ንግሥት ሶፍያ የሐና እመ ሳሙኤልን ጸሎት በመጥቀስ እሷም እንደ ሐና ሁሉ" ንብታ ፈጣሪዋን እንድትሰማን ንጉሡን ጠየቀችው፣ ንጉሡም "አ ብኪሲቶ ሠናየ ኅለይኪ፥ አንቺ ሆይ መልካም አስበሻል" በማለት በምክርዋ ተስማምቶ ሁላኤ ንብታ ፈጣሪዋን በጸሎት እንድት ለምን ፈቀደለት። ንግሥት ሶፍያም የካቲት ፲፪ ቀን ሁላኤ ንብታ ፈጣሪዋን መለመን ጀመረች። ከጸሎትዋም ጥቂቱ ግዚፋቢል ላይ የምትኖር፣ የተሳያትንም (ጥልቅ ባሕርንም) ጥልቀት የምትመለከት ጊዮቂ ፈጣሪዬ ሆይ አቤቱ ጸሎቴንና ልመናዬን ሰማኝ፣ ልቅሶዬንም አድምጥ ቸሳ አትበለኝ የሚል ነበር።

ደግሞ ንግሥት ሶፍያ /አህየዋ/ በብዙ ጸሎትና እንባዕ (እንባ) ሁላኤን ለመፈጸም ስትታገብ፣ እንድ ራእይ ተገለጠላት፣ እሱም ከተራራ ላይ የተተከለች ረዥም ዛፍ አየች። ፍሬዋም ጫፍ እስከ ሜፍ የሞላ ነበር። ጫፎችዋም ምድርን የሚሸፍኑ ነበሩ። አንድ ሰው፣ ብርሃን ለብስ ብርሃን ተጉናጽፎ፣ በእጁም ትምህርተ መስቀል ያላት የወርቅ ዘንግ ይዞ መጣ። ሁለት መለላልም ይዞ መለላሱቹን ከዚያች ዛፍ ግራና ቀኝ አቆማቸው።

ንግሥት ሶፍያ ግን የዚህ ራእይ ምሥጢሩ አልረዳ ቢላት ተጨነቀች ምሥጢሩን ይገልጽላት ዘንድም ፈጣሪዋን ለመነች፣ የለመነችውን የማይነሳ እግዚአብሔርም የራሱ ባለሟል የሆነውን የመላ እክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልን ላከላት፣ መልአኩም ብርሃን ተጉናጽፎ ነበርና ከመልአኩ ግርማ የተነሣ የንብረቻበት ቦታ ሁሉ ብርሃን ሆነ።

* ለጠቅ ይህቡ ተገ አንበ ይላኒ መጽሐ ሰላት ጎመት

አዝዛት በተወለዱ በ፲፪ ዓመታቸው፣ ቤተ መቅደስ በገቡ፣ በሰባት ዓመታቸው አባታቸው ንጉሥ ታዜር /ሠይፈ አርዕድ/ ዓረፈ። ምንም እንኳ እናታቸው ሶፍያ /አህየዋ/ ሰጥቂት ጊዜ መንግሥቱን ስትመራ እንደቆየች ቢታወቅም፣ መንግሥቱን በዘለቂታው ሰሚመራ ማሸተላለፍ ግድ ሆነ። በዚህ ጊዜ ግን ሁለት ዐበይት ችግሮች ተከሰቱ። እነሱም "እንደኛ ልጆቹ የብፅዓት ልጆች በመሆናቸው ቤተ መቅደስ መግባታቸው፣ ሁለተኛው የንጉሥ ልጅ ይሸሞ ቢባልም ልጆቹ በአንድ ጊዜ የተወለዱ መንትያዎች በመሆናቸው ለማንኛቸው መሰጠት እንደሚቻል አለሰቢና አስቸጋሪ ጉዳይ መሰሎ ነበር። ነገር ግን ሰው የሚችለው እንደራሱ ፈቃድ እየተመራ በራሱ ውሣኔ ብቻ ሊዳዝ እንጂ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲሆን መፍትሔው ከእግዚአብ ሔር በመሆኑ ችግሩ ከቦድ አልሆነም። በዚህ መሠረት ሕዝቡ ሊቀካህናቱን ፈቃደ እግዚአብሔር ጠይቅልን አሉት።

ሊቀካህናቱ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ የአባቶቻችን አምላክ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ሆይ ሙሴን በድብረ ሲና፣ ሳሙኤልን በቤተ መቅደስ፣ እንደተነጋገርክለት ጸሎቴንና ልመናዬን ሰማኝ ፊትህንም ከእኔ አትመልስ ፈቃድህን የሚነግረኝን ደኅኖውን መልእክህን ላክልኝ ብሎ ጸለየ።

እግዚአብሔር ልመናውን ሰማና መልአኩ ሚካኤልን ላከለት፣ እንዲህም አለው። እግዚአብሔር እነዚህን ሁለቱን ልጆች አንግሥ፣ ሁለቱንም በአንድ መንበር አስቀምጣቸው ብሎሃል አለው። ልጆቹ ግን እኛስ ለእግዚአብሔር የብፅዓት ልጆች ሆነን ተሰጥተናልና መንገሥ አይገባንም፣ ለላ ንጉሥ ፈልጉ አሉ። ሕዝቡም እጅግ አዘኑ።

ነገር ግን ነገሩ ፈቃደ እግዚአብሔር ስለነበር መልአኩ መጥቶ በዘመናቸው ብዙ ሥራ ይሠራ ዘንድ አሰውና፣ በእጃቸውም አብያተ ክርስቲያናትን ይታነጻሉና እሺ በጀ በሉ፣ የሊቀ ካህናቱንም ቃል ሰሙ አላቸው። እነሱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን አሉ። ሥርዓተ ንግሥናም በታላቅ ክብርና ሥርዓት ተፈጽሞላቸው ሰመ መንግሥታቸው ዓፄ እዜ እና ሳይዛና ተብለው ነገሡ።

1 ብሎ ለጽ ለጽ መሰጠ ግን ሰሞት ነው ሰሞት ነው ሰሞት ነው

በአንድ መንበር ሁለቱም እንደ አንድ ሰው ሆነው ነገሡ በሰላምና በሚያስደንቅ ፍቅር ተስማምተው ኢትዮጵያን መምራት ጀመሩ። በክፉት የተነሣባቸውን ጠላት፣ አልተበቀሉም። በዘመናቸው ፍትሕ አልተጓደለም፣ ድሃ አልተበደለም እንደ ነገሥታት ሥርዓት በቤታቸው በር ዘብ አላቆሙም በገሬና በተገሬ መካከል ይፈርዱ ዘንድ በአደባባይ ይቀመጡ ነበር እንጂ። ኢትዮጵያ በዘመናቸው የታወቀች ሆነች /የጊዜና አገር ተብላ/ ዜናቸው በየአህጉሩ ሁሉ ተሰማ። በዘመና ቸውም ዐመፀኛ ቀማኛ አልነበረም።

ወጣቶቹ ነገሥታት አንድ ነገር ያስጨንቃቸው ነበር፣ ይህን ጭንቀታቸውንም ሲሊቀሉሁ ነገሩት። እኛን የሚያስጨንቀን ስለመን ግሥታችን አይደለም፣ ስለጌታችን ስለክርስቶስ መወለድ ነው እንጂ አሉት። እሱም ጌቶች ይህስ ምሥጢር ለእኔም ድንቅ ነው። ነገር ግን በአልዓግሊና ዘመን የመጣ ፍሬምናጦስ የሚባል አንድ ሰው አለ፣ እሱም እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች ግዘረትና እምነት ላላችሁ ጥምቀትና ቍርባን የላችሁም እያለ ይናገራል አላቸው።

እነርሱም ፍሬምናጦስን አስጠርተው ስለነገረ ትስብእቱ ምሥጢር እንዲያስረዳቸው ጠየቁት፣ እሱም ከሊያት በመንፈስ ቅዱስ ተፀንሶ (ተመርተው) አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ፣ ይወለዳል ካሉበት ጀምሮ የልደቱን፣ የትምህርቱን፣ የጥምቀቱን የስቅለቱን፣ የሞቱን፣ የትንሣኤውንና የዕርገቱን ነገር ምሥጢር አስተማራቸው። ሐዋርያትም በጌታ ተሾመው ዓለምን ዞረው ማስተማራቸውን ተረከላቸው። እነሪሱም ፍሬምናጦስ ይህን ሥርዓት በሀገራችን እንድታስፋፋ አሉት። እርሱም በወቅቱ ሥልጣን ክህነት አልነበረውምና ይህን ሥራ ለመሥራት ሥልጣን ክህነት ያስፈልጋል አላቸው።

ነገሥታቱም ደብዳቤ ጽፈው ወደ የእስክንድርያው ፓትርያርክ እንዲሾምላቸው፣ ሀገራቸውን ተዘዋውሮ እንዲያስተምርላቸው፣ ገጸ በረከት በማስያዝ ፍሬምናጦስን ከብዙ ሊቃውንት ጋር ላኩት። ቅዱስ አትናቴዎስም ደብዳቤውን ባነበበ ጊዜ እጅግ ተደስቶ ፍሬምናጦስን አቡነ ሰላማ በማለት ሹሞ ወደ ኢትዮጵያ ሰደደው።

* [illegible]

ቅዱስ አትናቴዎስ ለአቡነ ሰላማና አብረው ለነበሩት ሊቃውንት ብሉያትን፣ መጻሕፍተ ሐዲሳትንና የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን እና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳትን አስይዞ ለነገሥታቱ ደብዳቤ ጽፎ ከብዙ ገጸ በረከት ጋር በታላቅ ክብር ሸኘው።

አቡነ ሰላማ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተላከውን ደብዳቤ ለነገሥታቱ ካቀረቡና የጉዞውን ነገር ሁሉ ካስረዱ በኋላ የማጥመቅ ሥራውን ቀጠሉ። ከሁሉ በፊትም ነገሥታቱ ተጠመቁ ኢዛና አብርሃ፣ ሳይዛናም አጽብሐ ተባሉ። ቀጥሎም ሠራዊቱና ሕዝቡ ሁሉ ተጠመቁ። ሥርዓተ ቍርባንም ድንጊን አስተክለው ተፈጸመላቸው።

አብርሃ ወአጽብሐ በአክሱምና በአካባቢዋ ሕዝቡን አስተምረው ካጠመቁ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመላእክት ጋር ተገልጾ በተራራው ላይ /አሁን መከየደ እግዚእ ተብሎ በሚጠራ ቦታ/ ቆሞ ታያቸውና በዚህች ቦታ ቤተክርስቲያን ሥሩልኝ አላቸው። ነገር ግን ቦታው የውኃ መከማቻ ባህር ስለነበር ከየት እንሥራ አሉት። ጌታችንም ከገነት ትገኝ አፈር አምጥቶ በባህሩ ላይ በተነ። ያቺም ባህር እንደ በረሃ ደረቅ ሆነች ጌታችንም ከዚህ ቦታ ላይ ቤተክርስቲያኒን ሥሩ በማለት አዞአቸው ወደ ሰማይ ዐረገ።

ነገሥታቱም የቤተ መቅደስ ሥራ ወደሚችሉት ወደ ጢሮስ ንጉሥ የኪራም ልጆችን እንዲልኩላቸውና እንዲያገዙላቸው ከብዙ ወርቅና ገንዘብ ጭምር ደብዳቤ ላኩ። በዚያም ወራት የግሪክ ጥበበ ኞችና የጢሮስ ብልሃተኞች መጡ። የጠቢባኑም ቁጥር ሃያ አራት ነበር። እነሱም ፲፪ የዕርእ (የግሪክ) ጥበበኞች፣ ፲፪ የኪራም የልጅ ልጆች የሆኑ የጢሮስ ብልሃተኞች ነበሩ። ጠቢባኑም በየምድባቸው በአንዲት ቦታ የ፲፪ መቅደስ መሠረት ጀመሩ። መሠረቱን ሲያከና ውኑ ጌታችን ለነገሥታቱ ታያቸው እነሱም ባዩት ጊዜ ሰገዱለት። ይህች የምታስፈጅት ቤተ መቅደስ እንደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ያለች ናት ብሉ ባርኳቸው ተሠወረ።

አባ ይስሐቅ ለሚባል መምህር ሰጡት። በዚህ ጊዜ እድሜው ስድስት ዓመት ነበር። በዚህ ጊዜ አባቱ ሞተ። በዚያም ፊደል ለይቶ አጥንቶ መዝሙረ ዳዊት ሊማር የእናቱ ወንድም ወደሆኑት ወደ አባ ጌዴዎን /ገበዘ አክሱም/ (የቤተክርስቲያን ሰሞነኞች ቀዳሾች ሹም) ሔደ። እንዲት ቀለም እንኳ ሳይ ያዝለት በዚያ ሰባት ዓመት ተቀመጠ። አንድ ቀን ቀለም አጥፍቶ አጎቱ አባ ጌዴዎን ተቆጥተው ገረፉት፣ ለፀብ ሳይሆን ለተግ



ቅዱስ ያሬድ በዐፄ ገብረ መስቀል ፊት ሲዘምር

ሣጽ። በዚህ ምክንያት ኮብልሎ ሸሽቶ ሲሔድ መንገድ አድክሞት ዋዕየ ዐሐይ (የፀሐይ ሙቀት፣ ትኩሳት፣ ቃጠሎ) ተሰምቶት ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀመጠ። ትል ዛፉ ላይ ለመውጣት ሽታ (ፈሊጋ) ስድስት ጊዜ እየወጣች ስትወድቅ በሰባተኛው ወጥታ ትጠልዋን ስትመገብ አይቶ በዚህ ተደንቆና ከትሏ ተምሮ እኔስ እስከ መጨረሻ ብተጋ ትምህርቴ ይገለጽልኝ የለምን? ብሎ በመጸጸት ተመልሶ መምህሩን ይቅርታ ጠይቆ ትምህርቱን ቀጠለ። ከዚህ በኋላ ጌታ ኅሊናውን ንጹሕ ልቡናውን ብሩህ አድርጉለት በአንድ ቀን የሊቃውንት መጽሐፍ፣ ብሉይ ከሐዲስ ወስና (አጠናቅቆ) ተገኘቷል። በአንድ ወቅት ጌታ ሦስት አዕዋፍ፣ ከገነት ልኮለት በሰው ቃል ሲያነጋግሩት ተመስጦ

መጣበትና ጌታ በመንበረ ጸባዖት በመላእክት ዜማ ሲመሰገን ሰማ። ንጉሡ ሊቀጳጳሱ መኳንንቱና ሕዝቡ በቤተክርስቲያን ለጸሎት ተሰብስበው ሳሉ ከመላእክት የሰማው ዜማ ተገልጾለት አመሰገኗል። ከዚያ በፊት በዚህ ዓይነት ዜማ ምስጋና የለም ነበርና ሁሉም በአድናቆት ሲሰሙት ውለዋል። ይህንንም ድርሰቱን ከላይ ከሰማይ የሰማሁት ነው ሲል አርያም ብሎታል። በሚያዜም ጊዜም ከዜማው ጣዕም የተነሣ ያለፈ ያገደመው የወጣ የወረደው ሁሉ በተመስጦ ይሰማው ነበር። አዕዋፍም ታላቅነቱና ክብሩን አውቀው የፀሐይ ትኩሳት እንዳይሰማው በክንፋቸው ይጋርዱት ነበር። ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል ከፍጹም ፍቅር የተነሣ ከቤተ መንግሥታቸው ያኖሩት ነበር። ታዲያ ከዕለታት በአንድ ቀን ከፊታቸው ቆሞ ጣዕም ያለውን ዜማ ሲያሰማቸው ተመስጠው (ሳያንቀሳቅሱ በዙሪያ ያለውን ሁሉ ረስቶ ኅሊናን ወደ አንድ ነገር መሰቀል) ሲያዳምጡ ሳይታወቃቸው በያዙት ጦር እግሩን ወጉት። በእርሱም ሳይሰማው ቆይቶ ዜማውን ሲጨርስ የደምህን ካሳ ምን ልስጥህ አሉት። ወርቅ ብር አልሻም ወደ ገዳም እንድሄድ ያሰናብቱኝ አላቸው። ንጉሡም ከእርሱ መለየቱን ባይወዱም ያደርጉለት ዘንድ የፈቀደውን ይፈጽሙለት ዘንድ ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ምለውለት ስለነበር አሰናበቱት። ወደ ቤተክርስቲያን ገብቶ እጁን በመንበረ ታቦቱ ላይ ዘርግቶ ኅብዕት ነሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ ነሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያልሽ ነሽ የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል ነሽ የሚለውን አንቀጸ ብርሃን ተብሉ የሚታወቀ ውን የእመቤታችንን ምስጋና ንባቡን ከዜማው አስማምቶና አስተካክሎ ስተት አድርጉ አመስግኖቢታል። በዚህ ጊዜ አንድ ክንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብሎ ታይቷል። ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ የተከዜን ወንዝ ተሻግሮ በጸለምት ከሚገኙ ገዳማት ሰሜን እንዳ በሆነው በደብረ ሐዊ በጾም በጸሎት ተወስኖ "ያባቴን የአዳምን፣ የመምህሬ የጌዴዎንን የኔ የራሴን መታሰቢያ ያደረገ ዋጋው ምን ይሆን ብሎ ጌታን በሰባኤ ጠይቆ ጌታም በተስፋህ ያመነውን በቃል ኪዳንህ የተማፀነውን እስከ ዐሥር ትውልድ ምሬልሃለሁ ብሎ ተስፋውን ተናግሮት ተሠውሯል። የድርሰቱም ዓይነት በአምስት

ይህ ቤተ መቅደስ ሥራው ሁሉ በግሩም ሁኔታ ተከናውኖ ለ፲፫ ዓመታት ያህል አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በ፲ኛው መቶ ክፍል ዘመን በአንበሳ ውድም ዘመነ መንግሥት እርሱን ድል ነስታ ፵ ዓመታት በነገሠችው በዮዲት ጉዲት ተቃጥሏል።

አብርሃና አጽብሃ በመላው ሀገሪቱ እየተዘዋወሩ ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን ከመፈጸማቸው በተጨማሪ ፲፻ አብያተ ክርስቲያናትን ያሳነጹ ሲሆን ከእነዚህም ፺፱ኙ አስደናቂ ናቸው። ባለ ፺፱ኙት ምሰሶ ከፍልፍል ድንጋይ የተሠሩ ሲሆኑ ከእነዚህም ውስጥ በገልአርታ የሚገኘው ሰው የማይከፍተው ሰው የማይዘጋው የቀመር አርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን ይገኙበታል።

እነዚህ ጻድቃን ነገሥታት ሀገሪቱን ተከፋፍለው በወሎ፣ በሸዋ የጣ ሚካኤል /አዲስ አበባ/፣ በከፋ የቡሐ ጊዮርጊስን፣ በሰላሌ የዋሻ ሚካኤልን፣ በጎጃም የዲማ ጊዮርጊስን፣ በጎንደር ሰማእ የዋሻ ሚካኤልን ቤተ ቤተክርስቲያን አሳንጸው እየተዘዋወሩ እያገለገሉ ነበርና ታላቁ አብርሃ በ፫፻፳፪ ዓ.ም ጥቅምት ፬ ቀን ዕለተ እሑድ ዐረፈና ተቀበረ። ወንድሙ አጽብሐ ደግሞ ጥቅምት ፬ ቀን ፫፻፴፬ ዓ.ም ዐረፈ። ሁለቱም ነገሥታት ልደታቸውም ሆነ ሞታቸው አንድ ቀን ነበር። ዓመተ ምሕረቱ ግን ይለያያል። በሞቱም ጊዜ በመቃብራቸው ላይ ለ፴ ቀናት ብርሃን ደመና ተተክሎ ታይቷል። እነዚህ ነገሥታት ለሀገራችን ብርሃን የገለጹ ባለውለታዎቻችን ሲሆኑ የኦሪትን ሥርዓት በሐዲስ ሥርዓት የለወጡ ቅዱሳን ናቸው።

ጌታችንም ለእነዚህ ቅዱሳን ነገሥታት ቃልኪዳን ገብቶላቸዋል። ዝክራችሁን የዘከረ፣ ስማችሁን የጠራ እምርላችኋለሁ። በስማችሁ ቀዝቃዛ ውኃ ያጠጣ እኔ የሕይወት ውኃ አጠጣዋለሁ። ለተራበ እንጀራ ያበላ እኔ የሕይወት እንጀራ አበላዋለሁ። በስማችሁ ቤተክርስቲያን ያሳነጸ በመንግሥተ ሰማያት ቤት እሰጠዋለሁ። በስማችሁ ማኅሌት የቆመ የመላእክትን ማኅሌት አሰማዋለሁ በማለት ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል።

ሐ. አፄ ካሌብ (ከ፬፻፹፯-፭፻፴፮ ዓ.ም)

የከበረ ጻድቅ የኢትዮጵያ ንጉሥ ካሌብ እግዚአብሔርን የሚፈራና በፍጹም ልቡ የሚወደው ሃይማኖቱም የቀና ነው። በናግራን አገር ያሉ ክርስቲያኖችን አይሁድ ከሀዲ ወንጀለኛ በሚሆን ፊንሐስ መሪነት እንደ በጎች በማረድና በእሳት በማቃጠል እንደሚገድሏቸው በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ መንፈሳዊ ቅንዓትንም ቀና። ከዚህም በኋላ ተነሣ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ገብቶ በመሠዊያው ፊት ቆሞ ዓይኑንም ወደ ሰማይ አቅንቶ በሐሳቡ ሁሉ ይረዳው፣ ምእመናንን ነፃ ያወጣቸው ያስችለው ዘንድ በቅን ኅሊና በትሑት ሰብእና ጸሎት አቅርቦ ከሀገረ መንግሥቱ ወጥቶ ሔደ። የናግራንን ሀገር ያጠፉ አይሁድንና መሪያቸውንም ገደላቸው። ብዙ ተአምራትም ስለ አደረገለት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ሀገረ መንግሥቱ በታላቅ ክብር በታላቅም ደስታ ተመለሰ። ለእግዚአብሔር ምን ዋጋ እከፍለ ዋለሁ ለጌትነቱና ፍጹም ለሆነ ገናንነቱ ነፍሴንና ሥጋዬን መባዕ አድርጌ ከማቀርብለት በቀር አለ። ከዚህ በኋላ ይህን ዓለም ንቆ መንግሥቱን ትቶ ደጋጎች መነኮሳት ወደሚኖሩበት ወደ አባ ጸንጠሌዎን ገዳም ደረሰ። ወደ ዋሻ ውስጥም ገብቶ ሰው እንዳያየውም የዋሻውን በር ዘግቶ ከዚያችም ወጥቶ ዳግመኛ ዓለምን እንዳያይ ማለ። ከምንጣፍ ከሸከላ ጽዋና ከለበሳት የምንኩስና ልብስ በቀር ምንም ምን ለራሱ አልያዘም። ምግቡም እምባሻና ጨው፣ የሚጠጣውም ውኃ ነበር። የነገሠበትንም ዘውድ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር መስኮት ላይ ይሰቅልለት ዘንድ ለኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ ለአባ ዮሐንስ ላከለት፣ ወደ ዋሻም ከገባ በኋላ ከማንም ጋር ሳይነጋገር እግዚአብሔርንም ደስ አሰኝቶ በፍቅር በአንድነት ግንቦት ሃያ ቀን በክብር አረፈ። /ምንጭ፡- መጽሐፈ ስንክሳር/

መ. ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ ትውልድ ሀገሩ አክሱም ነው። ትውልዱ ከዘርዐ ሌዋውያን ነው። አባቱ አዳም እናቱ ታውክልያ ይባላሉ። አባቱ ካህን ነበር። የተወለደውም ፭፻፭ ዓ.ም ነው። ለትምህርት ሲደርስ

ይከፈላል። እነዚህም ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ፣ መዋሥዕት ናቸው። ከዚህም ሌላ ማይ ኪራሁ በሚባል ቦታ ባለ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለውን ውዳሴ ማርያም በአራራይ የእሑድን በዕዝል ዜማ ቅዳሴ ማርያምን በግእዝና በዕዝል ዜማ አድርሶታል። ከዚህ በኋላ ግንቦት ዐሥራ አንድ ቀን በተወለደ በስድሳ ስድስት ዓመቱ በ፭፻፸፩ ዓ.ም ደብረሐዊ በተባለው ተራራ ተሰውሯል። በስሙም በኢትዮጵያ ፰ አብያተ ክርስቲያናት ታንጸዋል።

ረ. አቡነ ሰላማ /ከሣቴ ብርሃን/ /ከ፫፻፳፰-፫፻፶ ዓ.ም/

ስሙ ሜሮጵዮስ የሚባል አንድ ነጋዴ ሰው ነበር። ወደ ሕንድ አገር ለንግድ ሥራ ለመሄድ ከጢሮስ ሀገር /ግሪክ/ ወደ ኢትዮጵያ ባሕር ጠረፍ አዱሊስ በደረሰ ጊዜ ወንበዴዎች ድንገት ደርሰው በእርሱና እርሱ ጋር በነበሩ ሰዎች ላይ አደጋ ጥለው ገደሉት። በዚያም ከዘመዶቹ ወገን የሆኑ ሁለት ወጣቶች ነበሩና እነኛን ማርከው ወስደው በዘመኑ የአክሱም ንጉሥ ለነበረው ለታዜር በእጅ መንሻ መልክ ሰጡአቸው። የነዚህ ሁለት ወጣቶችም ስም ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ ይባል ነበር። ንጉሡም ተቀብሉአቸው መልካም ሥነ ምግባራቸውን ጽንዐ (ብርታታ ጥንካሬ ጥናት) ኃይላቸውን አይቶ ኤዴስዮስን ከቤተ መንግሥቱ ጋሻ ጃግሬነት (መጣሪያ አንጋች) ፍሬምናጦስን ከቤተ መዛግብት በጅሮንድነት አስገባቸው። ለንጉሡ ሁለት ልጆች ነበሩት እነርሱም አብረሃና አጽብሐ የተባሉት ኢዛናና ሳኢዛና ነበሩ። ታዲያ ፍሬምናጦስ እነዚህን ልጆች አካለ መጠን እስኪደርሱ ድረስ በክርስቶስ ማመን ሲያስተምራቸው ቆይቷል። በኋላም ወንድሙ ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ፍሬምናጦስ ግን ከገበዘ አክሱም ከአንበረም ብሉይ ሲማር ቆይቷል። አንድ ቀን ፍሬምናጦስ ለአንበረም የሀገራችሁን ሥርዓት ስመለከት እምነትን አምናችኋል፣ ተገዝራችሁማል። ጥምቀትና ቁርባን ግን የላችሁም አለው። ግዝረትንማ አባቶቻችን ሌዋውያን አምጥተውልናል፣ እምነትንም የሕንደኬ ጃንደረባ አስተምሮን አምነናል። ለጥምቀትና ለቁርባን ግን አስተማሪ ሐዋርያ አልተላከልን ማንስ ይሰጠናል አለው። ምነው

እስክንድርያ ቅርብ አይደለችምን ሄዳችሁ ከመንበረ ማርቆስ ጠይቃችሁ አታመጡምን? ብሎ ፍሬምናጦስ ቢመክረው ከቤተ መንግሥት መክረው በነገሥታቱ በአብርሃና አጽብሐ ፈቃድ ደብዳቤና እጅ መንሻ ሰጥተው አንተ ባወቅህ አምጣልን ብለው አምስት መቶ ወቄት ወርቅ ሰጥተው ሰደዱት። እስክንድርያም በደረሰ ጊዜ ሊቀጳጳሱ አባ እለእስክንድሮስ አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ ጉባኤ ለመገኘት ሄዶ ስለነበረ በዚያው በእስክንድርያ ትምህርት ቤት ገብቶ እየተማረ መቆየት ግድ ሆነበት። አርዮስን አውግዘው እንደተመለሱም እለእስክንድሮስ ዐረፈ። በመንበሩም ቅዱስ አትናቴዎስ ተተካ። ፍሬምናጦስም ነገሩን ለእርሱ አቀረበ። ቅዱስ አትናቴዎስም የኢትዮጵያውንን ሃይማኖትና ምግባር ጠይቆ ከተረዳ በኋላ የኢትዮጵያውያንን ባህላቸውን የለመደ ቋንቋቸውን ያወቀ ከአንተ ሌላ ወዴት ይገኛል ብሎ የሐዲሳት ትርጓሜን አስተምሮ፣ አባ ሰላማ ጳጳስ ዘአክሱም ወዘኩላ ኢትዮጵያ ብሎ የነጻ ሕዝብ ሀገር ለሆነችው ለኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጉ ሾሞ በታላቅ ክብር ጋር ወደ ሀገሩ ሰብከቱ ላከው። በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግሥትም ወደ ኢትዮጵያ በደረሰ ጊዜ በእክብሮት ተቀበሉት። በመላዋ ኢትዮጵያም የቀናች የጸናች እርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ሰበከ። የክርስቶስን የጌትነቱን ብርሃን በአገሪቱ ስብከቱ ሁሉ ገለጸ። ስለዚህም ብርሃን ገላጭ በመሆኑ ከሣቴ ብርሃን ተብሉ ተጠራ። ከዚህ በኋላ ከአንበረም ጀምረው ቀሳውስትን ዲያቆናትን ሾሞ መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከጽርዕ፣ ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ ተርጉሞ ዙር አስተምሮ ሐዋርያዊ ተልእኮውን በትጋት ፈጽሞ በተጋድሎና በመልካም ምግባር ኑሮ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፫፻፶ ዓ.ም ዐርፎአል።

ፈ. የተሰዐቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልእኮ መቅድም

ተሰዓቱ ቅዱሳን ወደኢትዮጵያ የመጡት አልአሜዳ በነገሠ በአምስት ዓመት ነው። እንደመጡም እንደአንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው በአክሱም ዐሥራ ሁለት ዓመት ኖረዋል። ተሰዐቱ ቅዱሳን በስም አሌፍ፣ አረጋዊ፣ ጰንጠሌዎን፣ ገሪማ፣

ጽሕማ፣ አፍጼ፣ ሊቃኖስ፣ ይምዓታ፣ ጉባ ይባላሉ:: እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዜ ጀምር ዝም ብለው አልተቀመጡም:: ለሥራቸው በር ከፋች የሆነውን ቋንቋ፣ የሕዝቡን ባህል ጠንቅቀው ካወቁ በኋላ በአንድ ላይ አንድ አካባቢ ከመኖር ይልቅ መንፈስ ቅዱስ በመደባቸው ቀጥታ ማስተማርን መርጠው መንፈሳዊ ዓላማቸውንም ለማሳካት የአክሱም ነገሥታት እርዳታና ድጋፍ አልተለያቸውም ነበር:: የተሰዐቱ ቅዱሳን ሐዋርያዊ ተልእኮን በ፭ ከፍሎ ማየት ይቻላል::

፩. ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ማጽናት፣
፪. መጻሕፍትን መተርጎም፣
፫. ስብከተ ወንጌልን ማስፋፋት፣
፬. ገዳማትን መመሥረት፣
፭. ሥርዓተ ምንኩስናን ማደራጀት ናቸው::

እነዚህ ሥራዎቻቸው ወቅታቸውን እየጠበቁ ተፈጽመዋል:: በዚህ በኩል የመጀመሪያ ሥራቸው ባዕድ አምልኮ የሚፈጸምበትን ቦታ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራበት አድርገዋል::

ሁለተኛው መጽሐፍ በመተርጎም በኩል አስተዋጽኦቸው በጣም የላቀ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ በአባ ሰላማ የተጀመረውን መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም ሥራ ተከፋፍለው ለፍጻሜ አድርሰውታል:: ይህም ለግእዝ ሥነ ጽሑፍ መስፋፋት በጣም ጠቅሟል:: እንዲያውም የመሠረት ድንጋይ ነው ማለት ይቻላል:: የቤተክርስቲያንን ትምህርት የሚያጠናክር ጽሑፎችን ለምሳሌ የቄርሎስንና የሌሎችን የታወቁ አበው ተግሣጽና ድርሰት ወደ ግእዝ እየተረጎሙ ለየአድባራቱና ለገዳማቱ እንዲዳረሱ አድርገዋል:: በዚህ መሠረት ይህ የተሰዐቱ ቅዱሳን ዘመንና ቅዱስ ያሬድ የተነሣበት የአፄ ገ/መስቀል ዘመን የመጀመሪያው የሥነ ጽሑፍ ዘመን በመባል ይታወቃል::

በሦስተኛ ደረጃ ስብከተ ወንጌልን አስፋፍተዋል:: በአንድ ሀገር ወንጌል ተሰበከ ሲባል በአንድ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ክርስቲያን ሆነ ማለት አይደለም:: ክርስትና በአባ ሰላማ ተሰብኳል ሲባል በመላው ኢትዮጵያ ወንጌል ተዳረሰ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ስለዚህ ከአባ ሰላማ በፊትም ሆነ በኋላ የቤተ ክርስቲያን ዜጐች መሆን ዕድል ያልገጠማቸው ኢትዮጵያዊያን ነበሩ:: አሁንም አሉ:: ስለዚህ ሀገራችን ክርስትናም ባዕድ አምልኮ የሚከተሉ ሰዎች ነበሩባት:: በዚህ መሠረት በሀገራችን አንዳንድ ክርስትና ያልተዳረሰባቸው ቦታዎች ስላሉ እግዚአብሔር በሚያውቀው እነዚህ ተሰዐቱ ቅዱሳን ለሀገራችን መምህርነት መጥተዋል ማለት ነው:: በዚህ መሠረት የክርስቶስን ወንጌል በሚገባ አስተምረዋል:: ሐዋርያዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል::

በዐራተኛ ደረጃ ገዳማትን መሥረተዋል:: ቅዱሳን አባቶች በዓትን (ዋሻ) መሥርተው የመናንያን ማኅበር እንዲስፋፋ በሀገራችን ጥሩ መሠረት አኑረዋል:: ይህም ሥርዓትን የተከተለ ነው:: ተሰዐቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ከማነጽና ገዳማትን ከመመሥረታቸው ሌላ በስማቸው እስከ አሁን ድረስ የሚጠሩ ገዳማት አሏቸው:: የሁሉም ገዳማቸው የሚገኘው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ነው::

በአምስተኛ ደረጃ ሥርዓተ ምንኩስናን አደራጅተዋል:: ምንኩስና በግብፅ በረሃ በሊና የተጀመረ ጠንከር ያለ የክርስትና ሕይወት አኗኗር ነው:: የመጀመሪያዎች መነኮሳት ተራ ምእመናን ነበሩ:: ብዙ ለገዳሙ ቅዳሴ አገልግሎት የሚያገለግሉ ከመካከላቸው አንዳንዶች ለቅስና መዓርግ ይሾማሉ:: ምንኩስናን ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ተሰዐቱ ቅዱሳን ሲሆኑ የምንኩስና ሥርዓት ጀማሪ የሆኑት ከአቡነ እንጦንስ አራተኛ ትውልድ የሆኑት አቡነ አረጋዊ ይህን ሥርዓት በኢትዮጵያ አስፋፍተዋል:: ይህን በራሳቸው ታሪክና በሐዋርያዊ ተግባራቸው ላይ እንመለከታለን::

ሰ. <u>ተሰዓቱ ቅዱሳን</u>

፩. <u>አቡነ አረጋዊ ዘደብረዳሞ</u>

ሀገራቸው ሮም ነው:: አባታቸው ይስሐቅ የሮም ንጉሥ ነበር:: እናታቸው ንግሥት እድና ትባላለች:: የመጀመሪያ ስማቸው ዘሚካኤል ነው:: ጥበብ መንፈሳዊ ሲማሩ አድገው ወደ እስክንድርያ ኮብልለው ገዳም ገቡ:: አበምኔቱ አባ ጳኩሚስ በፈቃደ እግዚአብሔር የመጡ መሆናቸውን አው ቀው መዓርገ ምንኩስና ሰጥተዋቸዋል::



አቡነ አረጋዊ በዘንዶ ታዝለው ወደ ደብረ ዳሞ ሲወጡ

ከዘመዶቻቸውም ሰባቱ ዜናቸውን ሰምተው መንፈሳዊ ቅንዓት አነሣሥቷቸው እንደሳቸው ዓለምን ትተው ገዳም ገብተው በምንኩስና ተወስነዋል:: እሳቸውንም መንጋውን እንደሚንከባከብ መልካም እረኛ ወደ ዜች የሕይወት መንገድ ስለመራኸን ብፁዕ አረጋዊ መባል ይገባሃል ብለዋቸዋል:: አረጋዊ የተባሉት ከዚያ ወዲህ ነው:: በገዳሙ ዳውናስ ሰባት ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደ ሮም ተመልሰው ሲያስተምሩ የሀገራችንን ዜና ሰምተው ለመምጣት መንገድ ጀመሩ:: ቅዱስ ሚካኤል በክንፉ ተሸክሞ አክሱም አድርሷቸዋል:: ተመልሰው ሄደው ሀገር ይሉአችኋል ኢትዮጵያ ናት:: ሐዋርያ ሳይላክላት በሃይማኖት በምግባር ጸንታ ትኖራለች ብለው ለሰባቱ ዘመዶቻቸው አበው መነኮሳት ነገሯቸው:: ስምንቱ ሁሉ ዓላቸውን ጠቅልለው በሮም ነግሦው የነበሩ ይስሐቅን (አባ ገሪማ) ጨምረው ንጉሥ አልአሜዳ በነገሡ በአምስተኛ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ራሳቸውን ዘጠኝ ሆነው መጥተዋል:: አባ አረጋዊ እናታቸው ቅድስት እድናን ደቀመዝሙራቸውን ማትያስን አስከትለው እግረ መንገዳቸው እያስተማሩና ድውያንን እየፈወሱ ደብረ ዳሞ ደረሱ:: ከእግረ ደብር ሆነው አሁን ያህንን ተራራ በምን ልወጣው እችላለሁ እያሉ ሲያወጡ ሲያወርዱ የታዘዘ ዘንዶ መጥቶ ስድሳ ክንድ በሚያህል ጅራቱ ጠምጥሞ ቅዱስ ሚካኤል ሰይፈ እሳት ይዞ እየጠበቃቸው ከተራራው አናት አድርሷቸዋል:: ወዲያውም ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ብለው አመስግነዋል:: ቦታውም ደብረ ሃሌ ሉያ ተብሏል:: በዚህ ዕለት ግማሽ ኀብስት በልተው ጠገቡ:: ከዚህ በኋላ ግን ምድራዊ ኀብስት አልተመገቡም:: በሰንበተ ክርስቲያን ከቅዳሴ በኋላ መላእክት ኀብስት ሰማያዊ እያመጡላቸው ይመገቡ ነበር እንጂ:: ኋላም ዜና ጽድቃቸውን ሰምተው ከስድስት ሺህ ያላነሱ ደቀመዛሙርት ተሰብስበውላቸዋል:: ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሲሞላቸው ጌታ (በመንፈቀ ሌሊት ተገልጾ ምድራዊ መንግሥትህን ትተህ ስላገለገልከኝ ሕልፈት ሽረት የሌለባት ሰማያዊ መንግሥቴን አወርስሃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጣቸው፤ በስምህ የተማፀነውን እስከ ዐሥራ አምስት ትውልድ ድረስ እምርልሃለሁ:: አንተንም ከሞት ገጽ ትሰወራለህ ብሎ ተስፋቸውን ነገራቸው:: እሳቸውም መነኮሳቱን ሰብስበው ከእንግዲህ በሥጋ አታዩኝም ብለው ነገሯቸው አበምኔት (የገዳም አባት (አለቃ)) ሾመውላቸው ጥቅምት ዐሥራ አራት ቀን በዚያው በደብረ ዳሞ ተራራ በስተምሥራቅ አቅጣጫ እንደሔኖክ እንደ ኤልያስ ተሰውረዋል::

፪. <u>አባ ጰንጠሌዎን (በ፬፻፹ ዓ.ም)</u>

ሀገራቸው ሮም ሲሆን ትውልዳቸው ከቤተመንግሥት ነው:: ቀጥራቸው ከተሰዓቱ ቅዱሳን ነው:: አንድነቱ ለጽሙና (ጭምትነት፣ ጸጥታ የገዳም ሥርዓት) ለብሕትውና የማይመቻቸው ሲሆን ተለያይተው የራሳቸውን በዓት ሠርተው ገዳም አትንተው የሚኖሩ ሆነዋል:: አባ ጰንጠሌዎን በፊት ከነበሩበት ሁለት ምዕራፍ ያህል ርቀው በልካቸው በዓት ሠርተው እህል ውኃ ሳይቀምሱ በጾም በጸሎት በስግደት ዐርባ አምስት ዓመት ኖረዋል:: ብዙ ተአምራት አድርገዋል:: ዛፍ ተከለው ዕለቱን አሳድገውና አድርቀው ፈልጠውና አከስለው ለማዕጠንት የሚሆን ፍሕም በማፋም በልብሳቸው አፍነው ወስደው ቤተክርስቲያን አጥነዋል:: ሁለተኛም ንጉሡ እጼ ካሌብ የሰማዕታተ ናግራንን ደም ለመበቀል ወደ የመን ሲዘምቱ አባቴ መርቀህ አሰናብተኝ አሏቸው:: መርቀው አሰናበቷቸው:: ጠላቶቻቸውን ድል አድርገው የተዘረፉትን ንዋየ ቅድሳት መልሰው በተደረገላቸው ረድኤት እየተደነቁ ሲመለሱ ሠራዊቶቻቸው አባ ጰንጠሌዎን የእሳት ሠይፍ ይዞ በመካከላቸው እየተመላለሰ ሲፈጃቸው አይተናል አሏቸው:: በዚህ ምክንያት ንጉሡ መንግሥታቸውን ትተው ከጻድቁ መዓርገ ምንኩስና ተቀብለው በጽሙና የሚኖሩ ሆነዋል:: የአባ ጰንጠሌዎን ዕረፍታቸውም ሲደርስ ጌታ በኪዳንህ የተማፀነውን መካንህን የተሣለመውን ከሞተ ነፍስ እድንልሃለሁ ብሎ ተስፋቸውን ነገራቸው ጥቅምት ስድስት ቀን ዐርፈዋል::

፫. <u>አባ ይምዓታ</u>

አባ ይምዓታ በተለይ ብዙ የቆዩት በትግራይ ውስጥ ገርአልታ በሚገኘው ልዩ ስሙ ጉሕ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው:: የአካባቢው አሰያየም ከእኝህ ጻድቅ አባት ታሪክ ጋር የተገናኘ መሆኑ ይነገራል:: አቡነ ይምዓታ ከአክሱም ተነሥተው /አብ ጎሕ፣ ወልድ ጎሕ፣ መንፈስ ቅዱስ ጎሕ/ ብለው ቅዳሴ ማርያምን እያዜሙ በዛሬው የጎሕ መንደር ነጋባቸው:: በዚህ የተነሣ የመንደራቸውን ስም ‹ይኩን ስምኪ መካነ ጎሕ› ብለው ሰየሟት::

የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን ከሐውዜን ፲፫ ኪ.ሜ. በመኪና ከተጓዙ በኋላ የግማሽ ሰዓት መንገድ ተጉዞ የሚገኝ ነው:: ቤተክርስቲያኑ ሰማይን እንደ ምሰሶ ደግፈው የቆሙ ከሚመስሉት ረጃጅም የገርአልታ ተራራዎች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እጠገቡ ካልደረሱ የማይታይ የተደመጠ አበው ድንቅ የመንፈሳዊነትና የብርቱነት ውጤት ነው:: ይህ ከባህር ጠለል በላይ ፪ ሺህ ሁለት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኘውን የዓለት ተራራ መውጣት አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም ለመወጣጫ የእጅ መያዣ ለእግር መቆንጠጫ የሚያገለግሉ ጉድጓዶች ብቻ ያሉት ከ፪፻፶ እስከ ፫፻ ሜትር ርዝመት ያለው ገደል ቁልቁል ሲመለከቱት እጅግ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነው:: ይህን ቤተ ክርስቲያን ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ የሆነው ደግሞ የበርካታ ሰዎች ዐፅም የተቀበረበት ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራ የመቃብር ሥፍራ መኖሩ ነው::

ቤተ ክርስቲያኑ ከዓለት ተፈልፍሎ የተሠራ ሲሆን ከውስጥ ራሳቸውን ችለው የቆሙ ዐራት ዓምዶች አሉት:: ጠቅላላ ስፋቱ ስድስት በዘጠኝ ሜትር ከወለል ወደ ጣሪያ ያለው ከፍታ ደግሞ ፫ ሜትር ነው:: ቤተክርስቲያኑ ድንቅና ልዩ እንዲሆን ያደረገው ከድንጋይ ተፈልፍሎ መሠራቱ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ያሉት ቅዱሳት ሥዕሎች ናቸው::

በቅኔ ማኅሌቱ ጣሪያና ግድግዳ የሚታዩት ደማቅ ሥዕሎች ተከታታይ ታሪክ የያዙ ናቸው የአቤል፣ የኖኅ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ ሥዕሎች ደምቀው ይታያሉ:: በተጨማሪ የ፱ኙ ቅዱሳን ሥዕል ይታያል:: ሦስቱ መስቀል፣ ፭ቱ መጻሕፍት እንደያዙ ሲሆን አንደኛው ግን ባዶ እጃቸውን ናቸው::

አቡነ ይምዓታ በፈረሳቸው ላይ ተቀምጠው እና አቡነ አሮን፣ አቡነ ማትያስ፣ የአቡነ ብንያም እና የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሥዕሎች የቤተክርስቲያኑ የዘመናት ጌጦች ናቸው:: ሥዕሎቹ በጣም ደማቅ በመሆናቸው ብዙ ክፍለ ዘመናት አልፈው የመጡ ድንቅ ቅርሶች አይመስሉም:: የአቡነ ይምዓታ ቤተክርስቲያን አገራችንን በዓለም ካሳወቁት የውቅር ዓለት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ነው::

፬. <u>አባ ጽሕማ</u>

አባታችን ጻድቁ አባ ጽሕማ ከተሰዓቱ ቅዱሳን አንዱ ሲሆኑ አገራቸው አንጾኪያ (ሶርያ) ሲሆን አባታቸው አንቲጦስ እናታቸው ሣራ ይባላሉ:: ከሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ በ፬፻፹ ዓ.ም በኤርትራ አድርገው አክሱም ገቡ:: ከተሠዓቱ ቅዱሳን ጋር ፲፪ ዓመት ተቀመጡ ከዚህ በኋላ ለአገልግሎት ለመፋጠን በየዕጣቸው ወደ ተፈቀደላቸው ቦታ በተበተኑ ጊዜ አባ ጽሕማን፣ አቡነ አረጋዊና አቡነ ገሪማ አድዋን አልፈው ማይሚሻም እስከሚባል ቦታ ሸኝተዋቸው ተመልሰዋል:: አባ ጽሕማ ክፍለ ዕጣቸው ወደ ሆነችው ዐድያ ወደምትባል ቦታ ለመሔድ ፈልገው ሳለ ይህች ሀገር በትልቅ ተራራ ተ.ጋርዳ ማለፊያ ቢያጡ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ:: በዚህ ጊዜ ዘወትር የማይለያቸው ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ በያዘው መስቀል አማትቦበት አላቸው:: ቢያማትቡ ተራራው እንደ ሰማይ ነጎድጓድ ጮኾ ከሁለት ተከፈለ:: በዚያ መካከል አልፈው ወደ ፀደያ (ጸቀያ) ሔደዋል:: የተከፈለው ተራራ ፩ኛው ደብረ ኃይላይ ፪ኛው ደብረ ሐተታ ይባላሉ:: ስሙንም ያወጡለት እርሳቸው ናቸው:: በጸቀያም ሕዝበ ክርስቲያኑን ሰብስበው ጹሙ፣ ጸልዩ፣ ንስሐ ግቡ እያሉ ሲያስተምሩ ሽፍቶች በቅናት ተነሣስተው ጥር ፲፮ ቀን ደብድበው ገድለዋቸው ሔዱ:: በዚያም ለ፫ ቀን ከቆዩ በኋላ ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ ተነሣና ወደ ደብረ ሐተታ ውጣ ዕረፍትህ በዚያ ነው ብሎ አስነሥቶ ወደ ተራራው ልኳቸዋል:: ከዚያም የገደሏቸው ሽፍቶች ተከትለዋቸው መጥተው እርሳቸውንና መነኮሳቱን እያገለገሉ ኖረው እዚያው ዐርፈዋል:: አባታችንም ሽፍቶቹን ማርልኝ እያሉ ዘወትር ይጸልዩ ነበር:: እግዚአብሔርም ለገደሉህ ለምን ምሕረትን ትለምናለህ? ቢላቸው አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብለህ በወንጌል ተናግረህ የለምን? ቢሉት ምሬልሃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጣቸው:: አባ ጽሕማ ወደ ተራራው የወጡበት የእግራቸው ዱካ እስከ ዛሬ እንደሚታይ ይነገራል:: በተጨማሪም ጻድቁ ዕፅ ተክለው በአንድ ቀን በቅለና ለምልሞ፣ ያንን አክስለው ፍሕም አፍነው ለሠርክ ቅዳሴ አድርሰዋል:: የእረፍታቸው ቀን በተቃረበ ጊዜ እግዚአብሔር ተገልጾላቸው በድንህ እስከ ዕለተ ምጽአት አይቀበርም ዝም እንደ ትኩስ ሬሳ ይሆናል ብሎ ቃል ኪዳን ገባላቸው:: ከዚህም የተነሣ ከመቃብራቸው አካባቢ የሚወጣው ሙቀት አሁን ድረስ አለ፣ በስማቸውም የፈለቀ ማየ ሕይወት ጸበልም ብዙ ሕሙማን ሲፈወሱ በት ይኖራል:: ከሀገራቸውም አምጥተው የተከሏት ዕፅ ጸድቃና ለምልማ አሁንም ትገኛለች:: የገዳማቸው አካባቢ አውሬና አባብ የበዛበት ቢሆንም በሰው ላይ ምንም ዓይነት ጉዳትና መተናኮል እንደማያደርግ በገድላቸው ላይ ባለው ቃል ኪዳናቸው ተጽፎአል:: በዚህ ሁኔታ አባ ጽሕማ ብዙ ተጋድሎ ከፈጸሙ በኋላ ጥር ፳፯ ቀን ዐርፈው በደብረ ሐተታ ተቀብረዋል::

፭. <u>አባ አፍጼ</u>

አባ አፍጼ ከተሰዓቱ ቅዱሳን አንዱ ሲሆኑ ሀገራቸው እስያ ነው:: ከአባታቸው ከአቡሊዲስና ከእናታቸው ከአቅሌስያ በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ተወለዱ:: የሃይማኖት ትምህርት እየተማሩ ካደጉ በኋላ ወደ ገብፅ በመሔድ በገዳመ አስቄጥስ ከአባ መቃርስ እጅ መዓርገ ምንኩስና ተቀበሉ:: ለሰባት ዓመታት በዚሁ ገዳም ቆዩ:: አባ አፍጼ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በአክሱም ወንጌል ለማስተማር ከብዙ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር መጡ:: በወቅቱ ንጉሥ አልአሜዳና አቡነ ሚናስ የተባሉ ጳጳስ በክብር ተቀብለው ወደ አክሱም በሚገኝ ቤተ ቀጢን ወደ ተባለ ሥፍራ ወሰዷቸው:: በዚያም ከተሰዓቱ ቅዱሳን ወንድሞቻቸው ጋር ለሰባት ዓመታት ያህል በአንድነት አብረው ከኖሩ በኋላ እግዚአብሔር ወደ መራቸውና እግዚአብሔር ወደ ፈቀደላቸው ቦታ ሔደው ወንጌል እንዲያስተምሩ ሃይማኖት እንዲያስፋፉና አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ ተስማምተው ተለያዩ:: አባ አፍጼም ከአክሱም ወደ የሐ መጡ:: በዓድዋ ዓስማ አካባቢ አርፈው ወንጌል እያስተማሩና ልዩ ልዩ ተአምራትን እየሠሩ ቆዩ:: ከዚያም ማይ ደናን በተባለች ቦታ መካከል ቁሽት ይሐና ገንደብታ አካባቢ በሚገኝ ዋሻ ገብተው ለዐሥራ ሁለት ቀናት በስብሐት ቆዩ በዚህ ዋሻ ያመነጩት ውኃ እስከ አሁን ድረስ የአባ አፍጼ ማይ (ውኃ) ትባላለች:: ከዚች ዋሻ ወጥተው በከተማ መካከል ወደ ታሪካዊው የሲማውያን ሕንፃ ገቡ:: ከእርሳቸውም ጋር ፫፻፸፯ መነኮሳት ነበሩ:: ከቦታው እንደደረሱ በአካባቢው የቤተ ክርስቲያን እጥረት እንዳለ ከተመለከቱ በኋላ በደመና ተጭነው ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ ውኃ ከዮርዳኖስ፣ አፈር ከተራራ ይዘው መጥተው ቦታውን በመባረክ ታቦተ ማርያምን ከመሐል፣ ታቦተ ሚካኤልን በቀኝ፣ ታቦተ ገብርኤልን በግራ አድርገው ተከሉ:: በዚህ መልክ ወንጌል እያስተማሩና ሃይማኖት እያስፋፉ አንድ መቶ ስምንት ዓመት ያህል የገዳሙ መሪ ሆነው ቆይተው በፈጸሙት ታላቅ የሃይማኖት ተጋድሎ ከአምላካቸው ቤተክርስቲያንህን ያሳነጸ፣ የተሳለመ፣ ተዝካርህን ያደረገ፣ በማኅሌት ምስጋና ያቀረበውን ዐርባ አምስት ትውልድ እምርልሃለሁ:: ቦታህን ለመሳለም በልቡ ያሰበውን እስከ

ዐሥር ትውልድ እምርልሃለሁ የሚል ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል። ከዚህ በኋላ በ፲፫፻፱ ዓ.ም ግንቦት ፳፱ ቀን ዛሬ የእግራቸው ተረከዝና የእ ውራ ጣታቸው ምልክት ካለበት ዓለታማ ሥፍራ ላይ ቆመው ጸሎት ሲያደርሱ ተሠውረዋል። ጻድቁ በቦታው ላይ ከአደረጉት ታላላቅና ድንቅ ተአምራት አንዱ የሚከተለው ነው። አንዲት ሴት ከሌላ ሰው በዝሙት የፀነሰችውን ፅንስ በውሸት አባ ይስሐቅ ከሚባል መነኩሴ ነው የፀነስኩት ብላ አስወራች። አባታችን አስጠርተው እምነት ከሀዲቷን ሲጠይቋት እርሷ ከአባ ይስሐቅ ነው ብላ በውሸቷ ጊዜ በማኅፀኗ ያለው ፅንስ ከአባ ይስሐቅ ሳይሆን ከሌላ እንደ ተፀነሰ መስክሮ አጋልጧታል። ይህም የሆነው በአባታችን ጸሎት ነው።

፮. አባ ሊቃኖስ

አባ ሊቃኖስ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አክሱም ከቆዩ በኋላ ለስብከት በየሐ ክፍላቸው ሲሰማሩ አቡነ ጰንጠሌዎንና አቡነ ሊቃኖስ ርቀው እንዳይሄዱ ሕዝቡ ስለተማፀናቸው ከከተማው ሳይርቁ አምስት ምዕራፍ ርቀት ገዳማቸውን መሠረቱ። አቡነ ሊቃኖስ ከአክሱም በስተ ሰሜን ከሚገኘው ደብረ ቆናጽል ከሚባለው ኮረብታ መቀመጫቸውን አድርገው የከተማውን ሕዝብ እያስተማሩ ለ፹፩ ዓመታት ቆይተዋል።

የአባ ሊቃኖስ ገዳም ደብረ ቆናጽል በመባል ይታወቃል። ደብረ ቆናጽል ማለት ጥቀበር ተራራ ማለት ነው። ከአባ ጰንጠሌዎን በዓት ምግዕት ከሚባለው የ፩ ኪ.ሜ ርቀት አለው። ደብረ ቆናጽል ከላይ እስ ከታች ድረስ በተፈጥሮ ልምላሜ የማይለየው ቦታ ሲሆን ተራራማ ሆኖ ኩሬያው ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈነ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ አስቄጥ ሳዊ ሥርዓት ያለው ገዳም በኢትዮጵያ የተመሠረተው በዚሁ በደብረ ቆናጽል ነው። በዚህ ገዳም ውስጥ ባህታውያን በደኑ ውስጥ ይኖሩበታል።

ይህ ገዳም ለአባ ጰንጠሌዎን ገዳምና ለአክሱም ከተማ በጣም ቅርብ ስለሆነ ወደ ጽዮን ማርያም ለመሳለም የሚሔዱ መናንያን በዚሁ ገዳም ዙሪያ ሱባኤ እየገቡ ወራትና ዓመታትን ያሳልፉ ነበር። የአክሱምና የአካባቢው ክርስቲያኖች ንዋያተ ቅድሳቱን የሚጠብቅላ ቸውና ጽላተ ሙሴን የሚያጥንላቸው መነኩሴ የሚመርጡት ከዚሁ ከአባ ሊቃኖስ ደብረ ቆናጽል ገዳም ነበር። አመራረጡም በምንኩስና ሕይወት በሚያሳየው ቅድስና ነው።

የአክሱም ሕዝብ ይህን የተመረጠውን መነኩሴ ንዋያተ ቅድ ሳት ጠባቂ! አጣኝ ብቻ ሳይሆን ከጳጳስ በበለጠ መንፈሳዊ አባትነቱን ይቀበሉታል። ደብረ ቆናጽልን የአካባቢው ነዋሪዎች ቅዱስ ቦታ ነው ስለሚሉ እጅግ ሰፋት ባለው ተራራ ዙሪያ አንዲት ቅጠል እንኳ አይበጥሱም ከብቶቻቸውንም ወደዚያ አያሰማሩም።

በዚህ አኳኋን እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ድረስ ተጠብቆ የኖረውን ገዳም ፋሽስት ኢጣልያ ሀገራችንን በግፍ ሲወር ይህን ገዳም እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ አጉሳቆለው! ቤተክርስቲያኑን ማደሪያቸውና የጦር መገልገያ ተሽከርካሪዎች የእጋሰሶች ማጉሪያ አደረጉት። ገዳሙ ከፋሽስት ኢጣልያ ወረራ ጀምሮ ጠፍ (ምድረ በዳ) ሆኖ ሲኖር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ጥቂት መነኮሳት በቦታው መቀመጥ ጀምረዋል።

ይህን ገዳም የመሠረቱት ከተስዐቱ ቅዱሳን አንዱ የሆኑት አባ ሊቃኖስ ለአክሱም ሲታይ ቅርብ በሆነ ቦታ ስለተቀመጠ ከአጼ ካሌብና ከአጼ ገ/መስቀል ጋር ስመገናኘት ዕድል ስለነበራቸው ለሐዋርያዊ ተግባራቸው እገዛ አድርጉላቸዋል። በዚህ መሠረት ደግሞ ከዐርዕ፣ ከሱርስት ቋንቋዎች መጽሐፈ ሐዲሳትን በከፊል ወደ ግእዝ እንደተረ ጐሙ ይነገራል። ዕረፍታቸው ኅዳር ፳፰ ቀን ነው።

፯. አባ አሌፍ

አቡነ አሌፍ ሀገራቸው ቂሳርያ ሲሆን አባታቸው አውሱግዮን እናታቸው አትናስያ ይባላሉ። የአቡነ አሌፍ ወላጆች ደግ ልጅ ከአብራካቸው የሚገኝ መሆኑን መልአክ እግዚአብሔር በራእይ ተገልጾ እንደነገራቸው ገድሉ ይናገራል። አቡነ አሌፍ ከሕፃንነታቸው አንሥቶ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ ገዳም እንዲሔዱ ስለአነሳሳቸው ወደ አባ እንጦንስ ገዳም ሔደው የገዳሙን ማኅበር እየረዱ በዚያው ገዳም መንኩሰዋል።

ከዚህ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በአክሱም ቤተ ቀጢን በሚባለው ቦታ በመቀመጥ የኢትዮጵያን ባህል ቋንቋ አጥንተዋል። ንጉሥ አልአሜዳ በክብር ተቀብሏቸዋል። አቡነ አሌፍ ገዳም መሥር ተዋል። ይህ ገዳማቸው የተመሠረተው በአጼ ገ/መስቀል ዘመነ መንግ ሥት ነው። አቡነ አሌፍ ወደ ሀገረ ስብከታቸው "ብኅዘት" ወደ ተባለው ቦታ ከአክሱም ተነሥተው በሚሔዱበት ጊዜ ከዚያ እስኪ ደርሱ ድረስ ስድስት ቦታ በጸሎት ውኃ አፍልቀዋል።

ይህ ብኅዘት ተብሎ የሚጠራው ተራራ በጣም ትልቅ ስለሆነ ዘንዶ ነበረበት። ይህ ዘንዶ ተራራውን በመስቀላቸው በሚባርኩበት ጊዜ ተራራውን ስለሰቀቀ በዚሁ ቦታ ገብተው ተቀመጡ። አቡነ አሌፍ በዚያ ተራራ ያሉትን ዕፅዋት ሁሉ አይተውና ተመልክተው ስላስደሰ ቷቸው ወደ እግዚአብሔር አመልክተው ይህቺን ተራራ "ደብረ ማነው" ብለው ጠርተዋታል። ገድላቸውም፡- "ወለይእቲ ደብረ ሰማያ ደብረ ማነው . . ." ይላታል።

• በዚህ ቦታ ጻድቁ አምስት መቶ መነኮሳትና ዐራት መምህራን እንደነበሯቸው ይነገራል። ገድላቸው እንደሚናገረው አቡነ አሌፍ በገዳማቸው ታላላቅ ተአምራትን ሠርተዋል። በዚያ ቦታ በገቡ በሰባ ዓመታቸው መጋቢት ፲፩ ቀን ቃል ኪዳን ተቀብለው ዐርፈዋል።

፰. አባ ጉባ

አቡነ ጉባ ከአባታቸው ጌርሎስና ከእናታቸው ቴዎዶክስያ መጋቢት ፳፱ ቀን ፫፻፹፰ ዓ.ም ተጸንሰው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፫፻፹፱ ዓ.ም መንፈቀ ሌሊት ተወለዱ። በተወለዱበት ጊዜ ብርሃን ከሰማይ ወርዶ ለሰባት ቀን ያህል ሲያበራ ሰነበተ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እልፍ አእላፋት መላእክትን አስከትሉ መጥቶ ባረካቸው። ይህ ሕፃን ንጽሕናው ቅድስናው እንደ መላእክት ይሆናል ብሎ ተናገረ። አባ ጉባም ከእናታቸው ማኅፀን እንደወጡ ሃሌሉያ ለአብ! ሃሌሉያ ለወልድ! ሃሌሉያ ለመንፈስ ቅዱስ! አሐዱ አብ ቅዱስ! አሐዱ ወልድ ቅዱስ! አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው አመስግነዋል። በተወለዱ በ፵ ቀናቸውም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጢሞቴዎስ አጥምቀዋቸው ስመ ክርስትናቸውን ጉባ ብለው ሰየሟቸው ጉባ ማለትም አፈወርቅ አፈመዓር ማለት ነው። በ፲፩ ዓመታቸው ከእነሁ ካጠመቋቸው አባት ዲቁናንና ቅስናን ተቀብለው መዓልወ አልባብ ወደሆነችው ወደ ግዳመ አስቄጥስ ሔዱ። ከዚያም ከአባ መቃርስ ምንኩስናና ብሕትውና እየተማሩ ሰባት ዓመት እንደተቀመጡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከፍልህ እዚህ ስላልሆነ ወደ ኢትዮጵያ ሒድ ብሎ ስለነገራቸው ከገዳመ አስቄጥስ ወጥተው ወደ አቡነ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሔዱ። ከእርሳቸው ጋርም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከተቀመጡ በኋላ በደመና ተጭነው ወደ አክሱም መጡ። ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀጥለው በአክሱም ኢጲስ ቆጶስነት የተሾሙ አባ ሚናስም በክብር ተቀበሏቸው። በአክሱም በቤተ ቀጢን ከ፰ቱ ቅዱሳን ጋር በአንድነት እየኖሩ እያለ እግዚአብሔር በሌሊት ቀስቀሳቸውና መኖሪያህ እዚህ ስላልሆነ ና በታህን ላሳይህ ብሎ ወደ ሀገረ ጠቃራ ደቡብ ትግራይ አመጣቸው። ይህችን ቦታ በዐራቱ ማዕዘን ካስጉበኛቸው በኋላ በ፲፱ ቀናቸው ወደ አክሱም መለሳቸው። ወንድሞቻቸው ስምንቱ ቅዱሳንም ለሁለት ሱባኤ ከነርሱ መካከል በመጥፋታቸው አዝነው ሰንብተው ነበርና በመመለሳቸው በጣም ደስ አላቸው። ከስምንቱ ቅዱሳን ጋር በአክሱም ፲፪ ዓመት በአንድነት ከተቀመጡ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር ሁሉም ወደ ተፈቀደላቸው ቦታ ተለያዩ። አባ ጉባም ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስከትለው ከአክሱም ወደ አድዋ ተጉዘው መሸባቸውና ከአድዋ ትንሽ ወጣ ብሎ በሚገኝ ተራራ ሰሎዳ በተባለ ቦታ አደሩ። በዚያም የብርሃን ድንኳን ስለተተከለላቸው የአካባቢውን ሕዝብ እያስተማሩና በሽተኞችን እየፈወሱ ከተማሪዎቻቸው ጋር ብዙ ቀን ቆዩ። በተለይም ስለገን በተባለ ቦታ አንድን ያላመነ ሰው ከሞት አስነሱ። ከዚህ በኋላ በደመና ተጭነው ወደ ሀገረ ጠቃራ መጡ ከተማሪዎቻቸው ጋር በዚህ ቦታ መኖር ሲጀምሩ ወደ ገነት ተወስደው ከአራቱ የገነት ፈሳሾች ውኃ ቀድተው በማምጣት ቦታይቱን አጠጧት። እመቤታችንም ከብዙ መላእክት ጋር በመምጣት ባርካቸው እንደ ዕንቁ የሚያበራ መስቀል ሰጠቻቸውና በዚያ መስቀልም ቦታይቱን ባረኳት። እንደገና በቀላል ደመና ተጭነው ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ ቅዱሳት መካናትን ከተሳለሙ በኋላ፥ ከዮርዳኖስ ጠበልና ከጌታ መቃብር አፈሩን ይዘው መጥተው በቦታቸው ላይ ነስነሱት። በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለነበረው ለአጼ ገ/መስቀልም መልእክት ላኩበት። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ወደ አባ ጉባ ሔዶ መባረክ እንዳለበት ስለነገረው ከብዙ ሠራዊት ጋር ከአክሱም! እርሳቸው ካሉበት ደረሰ። እሳቸውም የሠራዊቱን ብዛት በማየትና ስለመስተንገዶው በመጨነቅ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ቢጮኹ ኅብስተ መና አወረደላቸው! እንደማር ወለላ የሚጣፍጥ ውኃ አፈለቀላቸው! በዚያ ንጉሡና ሠራዊቱን መገቡ ቸዋል። አባ ጉባ በዚችው በዓታቸው ታቦተ ማርያምን አስገብተው ከመሬት ሦስት ክንድ ከፍ ብለው በመቆደስ ሕዝቡንና ንጉሡን አቆርበዋቸዋል። ንጉሡም በዚህ ተደስተው ትልቅ ገብርና ገብር በማድረግ ደብረ መድኃኒት ገነተ ጽባሕን ገደሙላቸው። በዚህ ገዳምም ጻድቁ በሱባኤ ላይ ሳሉ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ዞብል ሐድኖ በዚያም ትልቅ ክብርና ሞገስ ጸጋም ታገኛለህ ስለአላቸው ከአቡነ ገሪማ ጋር በመሆን ወደ ራያ ዞብልና የጁ በመሔድ ለ፲፩ ዓመታት ያህል እየዞሩ በማስተማር ብዙ ሕዝብ አሳምነው አጥምቀዋል! በሽተኞችን ፈውሰዋል ሙታንንም በተአምራት አስነስተዋል። በዚህ ወቅት አባ ጉባ የራማ ኪዳነ ምሕረትን ገዳምም እንደመሠረቱ ይነገራል። አቡነ ጉባ በጾም በጸሎት በሰጊድ በማስተማር ብዙ ዓመታት ተጋድሎአቸውን ከፈጸሙ በኋላ ጊዜ እረፍታቸው ስለደረሰ በተቀደሰች ገዳማቸው በደብረ መድኃኒት ገነተ ጽባሕ ጠቃራ ሳሉ ግንቦት ፳፰ ቀን ትንሽ ሕመም አደረባቸው! በዚህም ምክንያት ከሩቅም ከቅርብም የመጡ ብዙ ባሕታውያን ከበዋቸው ሳለ ጌታችን በግርማ መለኮቱ ተገልጾ አጽናናቸው። ስምህን የጠራ ዝክርህን የዘከረ! ቤተ ክርስቲያንህን የተሳለመ መጽሐፈ ገድልህን የጻፈ! ያጻፈ ያነበበ! የተረጐመ! በበዓልህ ማኅሌት የቆመ! እስከ ፲፭ ትውልድ ምሬልሃለሁ። ገድልህ የተነበበትን ማየ ጸሎት እንደዮርዳኖስ! ገዳምህን እንደ ኢየሩሳሌም አድርጌልሃለሁ! በማለት ቃልኪዳን ሰጥቷቸው ግንቦት ፳፱ ቀን ዐረፉ። ተማሪዎቻቸውና የጠቃራ ሰዎችም በጣም አለቀሱላቸው። እግዚአብሔር በበረከትና በቅደሳት በገደሉ ሥር ባለች ዋሻ ቀበሯቸው። እንደበረዶ ነጭ የሆነ ውኃም ፈለቀ! በእምነትም በውኃው የተረጨ የታመመ የጠማ ሰው ሁሉ ከበሽታው ፈጥኖ ይድናል። ከፍታው በግምት ፬ ሜትር ከሚሆን ገደል እየተንጠባጠበ የሚወርድ የዓይን ጠበል! ወደ ጆር የሚንቀረቀር ጠበል! ለልብ ሕመም የሚጠጣ ጠበል! በግንባርና በጀርባ የሚታሹበት ዓለት! በዚሁ ቦታ ይገኛል። አባ ጉባ ይጠቀሙበት የነበረ ከበረት የተሠራ በትረ መስቀል ከቤተ መቅደሱ ተቀምጦ ይገኛል። ጥንታዊው የዋሻ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገኘውም ቤተ ክርስቲያን ቅኔ ማኅሌት ቅድስትና መቅደስ ያለው ሲሆን ከመቅደሱ ጣራ ትንሽ ፈቅ ብሎ የጻድቁ መቃብር በጥቁር ጨርቅ ተጋርዶ ይታያል እስከ ፲፱፻፶ ዓ.ም ድረስ በበቁ አባቶች ይታጠን እንደነበረና ዛሬ ግን ታጥኖ እንደማያውቅ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ።

፱. አባ ገሪማ ዘመደራ

ትውልደ ሮማዊ ጻድቅ ነው። አባታቸው ሰፍንያስ ንጉሠ ሮም ነው። ከልጅነታቸው ጀምረው በመንፈሳዊ ትምህርት ታንጸው አድገው ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ ኖረዋል። ኋላም የአባታቸውን ዙፋን ወርሰው ለሰባት ዓመት ገዝተዋል። ከዚህ በኋላ አባ ጰንጠሌዎን፦ ምድራዊ መንግሥት ያልፋል ይጠፋል ፥ የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደኔ ና ብለው ላኩባቸው። ቅዱስ ገብርኤልም ከእግዚአብሔር ታዞ በክንፉ ነጥቆ በአንድ ቀን አክሱም አድርሷቸው ተገኙ። መንግሥት ምንኩስና ተቀብለው ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው እስኪቆጠር እየጾሙ! ሰውነታ ቸው ገሎ መቃብ እስኪያልቅታቸው ድረስ እያጠሙ እየሰገዱና እየፀለዩ ይጋደሉ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን መቁነን (ለገዳማውያን በዕለት የሚሰጥ ምግብ) ተቀብለው ከወንድሞች ጋር ወደ መንገድ ሲሔዱ ቤተክርስቲያን አግኝተው እጅ ሲነሡ ካህናት እየተጋዩ መጥተው፥ ቅዳሴ ሊያጉላቡን ነውና ከእናንተ የሚቻለው አንድ ሰው ይርዳን አሏቸው፥ የተናት መቁነናቸውን ተቀበው ነበር። እሳቸው ግን ቋጥረው ይዘዋት ስለነበር ከትከሩ ወዉ አኑረው ገብተው ቀድሰዋል! እኒያም በልተው የቀደሱ መስሏቸው ለአባ ጰንጠሌዎን ሔደው ነገሯቸው። እሳቸውም ሲመጡ መነኮሳቱን፦ "አድርጉት እንደሆን እንዳያፍር ጥቂት እልፍ በሉ" አሉአቸው። አባ ገሪማ ይህንን አውቀው እንጨቶችና ድንጋዮችም ይወገዱልን እንጂ አሉ። በዙሪያ ቸው የነበሩ እንጨቶችና ድንጋዮች ሦስት ምዕራፍ ያህል ሸሽተዋል። አባ ጰንጠሌዎንም ያዩትና የሰሙት ሁሉ ደንቋቸው፦ "ገሩም ድንቅ ልጄ ይስሐቅ አስገረምከኝ አስደሰትከኝ ሲሉ "ኦ ወልድየ ገሩም ገሪማ ገረምከኒ አሉአቸው።" ገሪማ የተባሉት ከዚህ በኋላ ነው። መነኮሳቱም አጥፍተናል ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል። ኋላም መደራ ገብተው በዓት ሠርተው ሃያ ሦስት ዓመት በትኅርምት (በጾም) ኑረዋል። ጌታም ሀብተ ተአምራት ሰጥቷቸዋል። በነግህ ስንዴ ዘርተው ዕለቱን ለመሥ ዋዕት አድርሰዋል። ከመሥዋዕት የተረፈውንም በጠፍጣፋ ድንጊያ ቢፈጩት በርክቶ ሰባ ሰባት ቁና ዱቄት ሆናላቸዋል። ከዓለት ላይም ወይን ተክለው አብቅለዋል። ከዚህ በኋላ ብዙ ተአምራትን ሲያደርጉ ኖረው በሰኔ ፲፯ ቀን በሠረገላ ብርሃን ተሠውረዋል። ወደ ኢትዮጵያም የመጡት በንጉሥ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት በ፬፻፹ ዓ.ም ከተስዐቱ ቅዱሳን አንዱ ሆነው ነው።

ስማቸው	የመጡበት ሀገር	የተቀመጡበት ቦታ	የዕረፍት በዓላ ቸው ቀን
አቡነ አረጋዊ	ሮም	ደብረ ዳሞ	ጥቅምት ፲፬
አቡነ ጰንጠሌዎን	ሮም	ከአክሱም ሰሜን ምሥራቅ	ጥቅምት ፮
አቡነ ይምአታ	እስያ	ገርአልታ	ጥቅምት ፳፰
አቡነ ጽሕማ	አንጾኪያ	እንደ አባ ጽሕማ ፀዲያ	ጥር ፲፮
አቡነ አፍጼ	እስያ	የሐ	ግንቦት ፳፱
አቡነ ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ	ደብረ ቆናጽል ከአክሱም በስተሰሜን	ኅዳር ፳፰
አቡነ አሌፍ	ቂሳርያ	ደብረ ሃሌሉያ አሕሳው አክሱም ሰሜን ምሥራቅ	መጋቢት ፲፩
አቡነ ጉባ	ኪልቅያ	እንደ አባ ገሪማ አጠገብ	ግንቦት ፳፱
አቡነ ገሪማ ዘመደራ		መደራ	ሰኔ ፲፯

ጢሞቴዎስ አጥምቀዋቸው ስመ ክርስትናቸውን ጉባ ብለው ሰየሟቸው ጉባ ማለትም አፈወርቅ አፈመዓር ማለት ነው። በ፲፩ ዓመታቸው ከእነሁ ካጠመቋቸው አባት ዲቁናንና ቅስናን ተቀብለው መዓልወ አልባብ ወደሆነችው ወደ ግዳመ አስቄጥስ ሔዱ። ከዚያም ከአባ መቃርስ ምንኩስናና ብሕትውና እየተማሩ ሰባት ዓመት እንደተቀመጡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከፍልህ እዚህ ስላልሆነ ወደ ኢትዮጵያ ሒድ ብሎ ስለነገራቸው ከገዳመ አስቄጥስ ወጥተው ወደ አቡነ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ሔዱ። ከእርሳቸው ጋርም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከተቀመጡ በኋላ በደመና ተጭነው ወደ አክሱም መጡ። ከአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ቀጥለው በአክሱም ኢጲስ ቆጶስነት የተሾሙ አባ ሚናስም በክብር ተቀበሏቸው። በአክሱም በቤተ ቀጢን ከ፰ቱ ቅዱሳን ጋር በአንድነት እየኖሩ እያለ እግዚአብሔር በሌሊት ቀስቀሳቸውና መኖሪያህ እዚህ ስላልሆነ ና በታህን ላሳይህ ብሎ ወደ ሀገረ ጠቃራ ደቡብ ትግራይ አመጣቸው። ይህችን ቦታ በዐራቱ ማዕዘን ካስጉበኛቸው በኋላ በ፲፱ ቀናቸው ወደ አክሱም መለሳቸው። ወንድሞቻቸው ስምንቱ ቅዱሳንም ለሁለት ሱባኤ ከነርሱ መካከል በመጥፋታቸው አዝነው ሰንብተው ነበርና በመመለሳቸው በጣም ደስ አላቸው። ከስምንቱ ቅዱሳን ጋር በአክሱም ፲፪ ዓመት በአንድነት ከተቀመጡ በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር ሁሉም ወደ ተፈቀደላቸው ቦታ ተለያዩ። አባ ጉባም ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስከትለው ከአክሱም ወደ አድዋ ተጉዘው መሸባቸውና ከአድዋ ትንሽ ወጣ ብሎ በሚገኝ ተራራ ሰሎዳ በተባለ ቦታ አደሩ። በዚያም የብርሃን ድንኳን ስለተተከለላቸው የአካባቢውን ሕዝብ እያስተማሩና በሽተኞችን እየፈወሱ ከተማሪዎቻቸው ጋር ብዙ ቀን ቆዩ። በተለይም ስለገን በተባለ ቦታ አንድን ያላመነ ሰው ከሞት አስነሱ። ከዚህ በኋላ በደመና ተጭነው ወደ ሀገረ ጠቃራ መጡ ከተማሪዎቻቸው ጋር በዚህ ቦታ መኖር ሲጀምሩ ወደ ገነት ተወስደው ከአራቱ የገነት ፈሳሾች ውኃ ቀድተው በማምጣት ቦታይቱን አጠጧት። እመቤታችንም ከብዙ መላእክት ጋር በመምጣት ባርካቸው እንደ ዕንቁ የሚያበራ መስቀል ሰጠቻቸውና በዚያ መስቀልም ቦታይቱን ባረኳት። እንደገና በቀላል

ደመና ተጭነው ወደ ኢየሩሳሌም በመሔድ ቅዱሳት መካናትን ከተሳለሙ በኋላ፥ ከጎርጎርዮስ ጠበልና ከጌታ መቃብር አፈሩን ይዘው መጥተው በቦታቸው ላይ ነስነሱት። በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለነበረው ለአጼ ገ/መስቀልም መልእክት ላኩበት። መልእክቱ ቅዱስ ገብርኤልም ወደ አባ ጉባ ሒዶ መባረክ እንዳለበት ስለነገረው ከብዙ ሠራዊት ጋር ከአክሱም፣ እርሳቸው ካሉበት ደረሰ። እሳቸውም የሠራዊቱን ብዛት በማየትና ስለመስተንገዶው በመጨነቅ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ቢጮኹ ኅብስተ መና አወረደላቸው፣ እንደማር ወለላ የጣፈጠ ውኃ አፈሰሰላቸው፤ በዚያ ንጉሡና ሠራዊቱን መገቡቸዋል። አባ ጉባ በዚችው በዓታቸው ታቦተ ማርያምን አስገብተው ከመሬት ሦስት ክንድ ከፍ ብለው በመቀደስ ሕዝቡንና ንጉሡን አቁርበዋቸዋል። ንጉሡም በዚህ ተደስተው ትልቅ ግብዣና ግብር በማድረግ ደብረ መድኃኒት ገነተ ጽባሕን ገደሙላቸው። በዚህ ገዳምም ጻድቁ በሱባኤ ላይ ሳሉ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ዞብል ሒድ፥ በዚያም ትልቅ ክብርና ሞገስ ጸጋም ታገኛለህ ስለአላቸው ከአቡነ ገሪማ ጋር በመሆን ወደ ራያ ዞብልና የጁ በመሔድ ለ፲፰ ዓመታት ያህል እየዞሩ በማስተማር ብዙ ሕዝብ አሳምነው አጥምቀዋል፤ በሽተኞችን ፈውሰዋል ሙታንንም በተአምራት አስነስተዋል። በዚሁ ወቅት አባ ጉባ የራማ ኪዳነ ምሕረትን ገዳምም እንደመሠረቱ ይነገራል። አቡነ ጉባ በጾም በጸሎት በስግድ በማስተማር ብዙ ዓመታት ተጋድሎአቸውን ከፈጸሙ በኋላ ጊዜ እረፍታቸው ስለደረሰ በተቀደሰች ገዳማቸው በደብረ መድኃኒት ገነተ ጽባሕ ጠቃራ ሳሉ ግንቦት ፳፱ ቀን ትንሽ ሕመም አደረባቸው፤ በዚህም ምክንያት ከሩቅም ከቅርብም የመጡ ብዙ ባሕታውያን ከበዋቸው ሳለ ጌታችን በግርማ መለኮት ተገልጾ አጽናናቸው። ስምህን የጠራ ዝክርህን የዘከረ፣ ቤተ ክርስቲያንህን የተሳለመ መጽሐፈ ገድልህን የጻፈ፣ ያጻፈ፣ ያነበበ፣ የተረጎመ፣ በበዓልህ ማኅሌት የቆመ፣ እስከ ፲፭ ትውልድ ምሬልሃለሁ። ገድልህ የተነበበትን ማየ ጸሎት እንደዮርዳኖስ፣ ገዳምህን እንደ ኢየሩሳሌም አድርጌልሃለሁ፤ በማለት ቃልኪዳን ሰጥቷቸው ግንቦት ፳፱ ቀን ዐረፉ። ተማሪዎቻቸውና የጠቃራ ሰዎችም በጣም

ቀድሰዋል፣ እኒያም በልተው የቀደሱ መስኳቸው ለአባ ጰንጠሌዎን ሐደው ነገሯቸው። እሳቸውም ሲመጡ መነኩሳቱን፦ 'አድርጉት እንደሆን እንዳያፍር ጥቂት እልፍ በሉ' አሉአቸው። አባ ገሪማ ይህንን አውቀው እንጨቶችና ድንጋዮችም ይወገዱልን እንጂ አሉ። በዙሪያቸው የነበሩ እንጨቶችና ድንጋዮች ሦስት ምዕራፍ ያህል ሸሽተዋል። አባ ጰንጠሌዎንም ያዩትና የሰሙት ሁሉ ደንቋቸው፦ ማሩም ድንቅ ልጄ ይስሐቅ አስገረምከኝ አስደሰትከኝ ሲሉ 'ኦ ወልድየ ግሩም ገሪማ ገረምከኒ አሉአቸው።' ገሪማ የተባሉት ከዚህ በኋላ ነው። መነኩሳቱም አጥፍተናል ብለው ይቅርታ ጠይቀዋል። ኋላም መደራ ገብተው በዓት ሠርተው ሃያ ሦስት ዓመት በትኅርምት (በጾም) ኑረዋል። ጌታም ሀብተ ተአምራት ሰጥቷቸዋል። በነግህ ስንዴ ዘርተው ዕለቱን ለመሥዋዕት አድርሰዋል። ከመሥዋዕት የተረፈውንም በጠፍጣፋ ድንጋይ ቢፈጩት በርክቶ ሰባ ሰባት ቁና ዱቄት ሆኖላቸዋል። ከዓለት ላይም ወይን ተክለው አብቅለዋል። ከዚህ በኋላ ብዙ ተአምራትን ሲያደርጉ ኖረው ሰኔ ፲፯ ቀን በሠረገላ ብርሃን ተሠውረዋል። ወደ ኢትዮጵያም የመጡት በንጉሥ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት በ፬፻፹ ዓ.ም ከተሰዓቱ ቅዱሳን አንዱ ሆነው ነው።

ስማቸው	የመጡበት ሀገር	የተቀመጡበት ቦታ	የዕረፍት በዓላቸው ቀን
አቡነ አረጋዊ	ሮም	ደብረ ዳሞ	ጥቅምት ፲፬
አቡነ ጰንጠሌዎን	ሮም	ከአክሱም ሰሜን ምሥራቅ	ጥቅምት ፮
አቡነ ይምአታ	እስያ	ገርአልታ	ጥቅምት ፳፰
አቡነ ጽሕማ	አንጾኪያ	እንደ አባ ጽሕማ ፀዲያ	ጥር ፲፮
አቡነ አፍጼ	እስያ	የሐ	ግንቦት ፳፱
አቡነ ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ	ደብረ ቆናጽል ከአክሱም በስተሰሜን	ኅዳር ፳፭
አቡነ አሌፍ	ቂሳርያ	ደብረ ሃሌሉያ አሕሳ አክሱም ሰሜን ምሥራቅ	መጋቢት ፲፩
አቡነ ጉባ	ኪልቅያ	እንደ አባ ገሪማ አጠገብ	ግንቦት ፳፱
አቡነ ገሪማ ዘመደራ		መደራ	ሰኔ ፲፯

አስቀሱላቸው። እግዚአብሔር በባረካትና በቀደሳት በገደሉ ሥር ባለች ዋሻ ቀበሯቸው። እንደበረዶ ነጭ የሆነ ውኃም ፈለቀ፤ በእምነትም በውኃው የተረጨ የታጠበ የጠጣ ሰው ሁሉ ከበሽታው ፈጥኖ ይድናል። ከፍታው በግምት ፴ ሜትር ከሚሆን ገደል እየተንጠባጠበ የሚወርድ የዓይን ጠበል፣ ወደ ጆሮ የሚንቆረቆር ጠበል፣ ለልብ ሕመም የሚጠጣ ጠበል፣ በግንባርና በጀርባ የሚታሹበት ዓለት፤ በዚሁ ቦታ ይገኛል። አባ ጉባ ይጠቀሙበት የነበረ ከበረት የተሠራ በትረ መስቀል ከቤተ መቅደሱ ተቀምጦ ይገኛል። ጥንታዊው የዋሻ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገኘውም ቤተ ክርስቲያን ቅኔ ማኅሌት ቅድስትና መቅደስ ያለው ሲሆን ከመቅደሱ ጫፉ ትንሽ ፈቅ ብሎ የጻድቁ መቃብር በጥሞ ጨርቅ ተጋርዶ ይታያል እስከ ፲፱፻፶ ዎቹ ድረስ በበቁ አባቶች ይታጠን እንደነበረና ዛሬ ግን ታጥኖ እንደማያውቅ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ።

ሰ. አባ ገሪማ ዘመደራ

ትክክለኛ ስማቸው ይስሐቅ ነው። አባታቸው ሰፍንያስ ንጉሠ ሮም ነው። ከልጅነታቸው ጀምረው በመንፈሳዊ ትምህርት ታንጸው አድገው ቤተክርስቲያንን ሲያገለግሉ ኖረዋል። ኋላም የአባታቸውን ዙፋን ወርሰው ለሰባት ዓመት ገዝተዋል። ከዚህ በኋላ አባ ጰንጠሌዎን፦ ምድራዊ መንግሥት ያልፋል ይጠፋል፣ የማያልፈውን ሰማያዊ መንግሥት ትወርስ ዘንድ ፈጥነህ ወደኔ ና ብለው ላኩባቸው። ቅዱስ ገብርኤልም ከእግዚአብሔር ታዞ በክንፉ ነጥቆ በአንድ ቀን አክሱም አድርሷቸው ተገኙ። መንግሥት ምንኩስና ተቀብለው ሥጋቸው አልቆ አጥንታቸው እስኪቆጠር እየጾሙ፣ ሰውነታቸው ዝሎ መቆም እስኪያቅታቸው ድረስ ሰግደው እየሰገዱ እየፀለዩ ይጋደሉ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን መቁነን (ለገዳማውያን በዕለት የሚሰጥ ምግብ) ተቀብለው ከወንድሞች ጋር ወደ መንገድ ሲሔዱ ቤተክርስቲያን አግኝተው እጅ ሲነሱ ካህናት እየተቻኮሉ መጥተው፣ ቅዳሴ ሊቀድሱ ነውና ከእናንተ የሚቻለው አንድ ሰው ይርዳን አሏቸው፣ የቆረቡ መቁነናቸውን ቀምሰው ነበር። እሳቸው ግን ቆጥረው ይዘዋት ስለነበር ከቅርፉ ውጪ አኑረው ገብተው

ሸ. ዐፄ ገብረ መስቀል

ዐፄ ገብረ መስቀል ዘአክሱም ንጉሠ ኢትዮጵያ የተባለው ጻድቅ ትውልድ ሀገሩ አካለ ጉዛይ፣ ልደቱ ኅዳር ፩ ቀን ሲሆን የመነኮሰው አቡነ እንጦንዮስ ዘደብረ መዓር ነው። የአቡነ ክርስቶስ ቤዛነ ልጅ ነው። ይህ ጻድቅ ዳግማዊ ኤልያስ የሚል የቅፅል ስም አለው። እፀ (ከቆዳ የተሠራ ልብሱ) እንደ ክንፍ ሆኖ በአየር ላይ እየተንዘ ስብከተ ወንጌልን እያስፋፋ፣ ደመና እየጠቀሰ ዝናብን ያዘንብ የነበረ፣ ክፉ ቀን ሆኖ የተከዜን ወንዝ ባርኮ ወተት ያደረገ፣ ከአንዱ ገዳም ወደ አንዱ ገዳም ሲዘዋወር በነፋስ ተጭኖ ይጓዝ የነበረ፣ ንፋስ የተገዛለት ባሕሮች ወተት የሆኑለት አባት ነው። ይህ ጻድቅ በራስጌው ወንጌልን፣ በግራ ተአምረ ማርያምን፣ በግርጌው ድርሳነ ሚካኤልን፣ በግራው መጽሐፍ ቅዱስን፣ ደረቱ ላይ ሃይማኖተ አበውን አድርጎ የሚፀልይ አባት ስለነበረ፥ ቅዱሳን ይህንን ሲያዩ፦ ለምንድነው ብለው ሲጠይቁት "ሰይጣን በአራቱ ማዕዘን እንዳይቀርበኝ፣ ከልቤ ከደረቴ ላይ ያደረኩትም ቃሉን ማመኔን ለማረጋገጥ እና የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ እነዚህ መጽሐፍት መሆናቸውን ለመመስከር ነው" ብሎ ይናገር ይመልስላቸው ነበር።

ዐፄ ገብረ መስቀል ጊዜ ሞቱም ሲደርስ መነኩሳቱን ሰብስቦ ትንሽ ልጸልይ ብሎ ከእነርሱ ተለይቶ በጸሎት ላይ እንዳለ አርፏል። ነፍሱ ከሥጋው ሲለይ እናብስት ተሰበሰቡና አስከሬኑን እየጠበቁ አገኙአቸው። መነኩሳቱም እየተደነቁ ዐፅሙን ወስደው በአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም ከመንበሩ ሥር ቀብረውታል። በስሙ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ምዕራባዊ ትግራይ ሀገረ ስብከት ደብረ ዓባይ አጠገብ የሚገኝ ሲሆን፤ ገዳሙም አቡነ ገብረ መስቀል ዘአክሱም ይባላል። እረፍቱም መጋቢት ፳ ቀን ነው።

፫.፪. ከዮዲት እስከ አሕመድ ግራኝ

ሀ. ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ /በ፲፩ኛ ዓ.ም/

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ አባቱ ግርማ ስዩም ይባላል። ቅዱስ ላሊበላ ከገርን ስዩም የሚወለድ ሲሆን ለቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የአጎት ልጅ ነው። ከቅዱስ ላሊበላ በፊት የነገሠው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ነው። መጋቢት ፳፱ ቀን ተወለደ። የነገሠውም ዐርባ ዓመት ነው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እጅግ መልከ መልካም ፆግረ ደም ግባቱ የተወደደ በመሆኑ በሕፃንነቱ የተመለከቱት ጠቢባት ሁሉ የተለየ ሀብት እንዳለው እንደሚነግሥም ተናግረውለት ነበር። እናቱ ለጥምቀተ ክርስትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትወስደውም ሊቀ ጳጳሱን አገኙ። ሊቀ ጳጳሱም ሕፃኑን ሲመለከተው ክብረ ጸጋው ተገለጸለት ሕፃኑን አጥምቆ፣ ቀድሶ አቆርቦታል። ለእናቱና ለሕዝቡም ስለ ሕፃኑ ታላቅነት መሰከረ።

ሕፃኑም በጸጋ እግዚአብሔር ከመከበሩ የተነሣ የእናቱን ጡት ሳይጠባ ቢውልም፣ እናቱ ምን ሆነ ብላ አብዝታ ስለተጨነቀች በዘጠኝ ሰዓት ስለ እናቱ ሲል ጠብቷል።

በወቅቱ የነበረው ንጉሥ የይምርሐነ ክርስቶስ አጎት ጠጠውድም ከእኔ በኋላ ሥልጣኔን የሚረከበኝ ዙፋኔን የሚወርስ ማን ነው? እያለ ሲጨነቅ በሕልም ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እንደሚወርስ ተነገረው። በዚህ ምክንያት ንጉሡ እንደ ሄሮድስ በክፉ መንፈስ ተሞልቶ መንግሥቱን የሚወርሰው ደገኛ ሕፃን እርሱ ነውና ሕፃኑን ልየው ብሎ ወደ እናቱ መልእክተኛ ልኮ አስመጣው። ሕፃኑም አፍንጫው የነገተ ተክል የመሰለ፣ ከአፉ የሚወጣው መዓዛ የሚጣፍጥ፣ ዓይኖቹ ያማሩ፣ ውብ ልጅ መሆኑን ሲመለከት ከቅንዓት ሥጋዊ የተነሣ ሊገድለው አሰበ።

አማካሪዎቹንም ጠርቶ በዚህ ሕፃን ምን ላድርገው? ብሎ ቢጠይቃቸው አትግደለው፣ ብትገድለው በእግዚአብሔር ዘንድ በነፍስ ትጠየቃለህ፣ ነገር ግን መንግሥትህን እንዳይወርስ ትምህርት አቃስ ተምረው እረኛ ሆኖ ይኑር ብለው መከሩት። ንጉሡም ሰምነት ከእርሱ ጋር ካስቀመጠው በኋላ ወደ እናቱ መለሰው። ንጉሡ ጥቂት ቀናት ከሰነበተ በኋላ መካሪዎቹ እንደገና ሕፃኑ ተማረም አልተማረም ፈቃደ እግዚአብሔር ስለሆነ ያገኘው ሕልም ሳይፈጸም አይቀርምና

ነገራትና ፈቃደኛ ከሆንሽ ወደ ሀገሬ አብረን እንሒድ አላት። እሷም እሺ ብላው አብረው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በወሎ ክ/ሀገር በላስታ አውራጃ በምትገኘው በአንዲት ቦታ ተቀመጠ። ንጉሡ ጠጠውድም ሞቶ ስለነበር ያለምንም ችግር ነገሠ። በዚያች ቦታ ለ፲፰ ዓመት መና ከሰማይ እየወረደለት በድንኳን እየቀደሰ ምእመናኑን ያቆርብ ነበር። አንድ ቀን ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በዚያች ቦታ ሕዝቡን ግብር አብልቶ ነበርና አዋቂ ነን ባዮች ከቤቱ ገብተው ንጉሥ ሆይ ዛሬ አንድ ምክር ልንመክርህ መጥተናል እንድትሰማን አሉት። አንተ ልበ አምላክ ከተባለው ከቅዱስ ዳዊት፣ ሦስት ሴቶች አግብቶ ከነበረው ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ስለዚህ ሌላ ሚስት አግባ ብለው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስን መከሩት። እርሱም እናንተ የሰይጣን መልእክተኞች፥ አመንዝር ብላችሁ የምትመክሩኝ ለምንድን ነው? ከእኔ ሒዱ፤ ብሎ አሳፍሮ ላካቸው።

ሌሊት ግን ለምን ይህን ሐሳብ እንዳቀረቡለት በሃሳቡ ሲያሰላ ስል አደረ። በቁጣ ስላባረራቸው ምነው ምን ፈልገው ይሆን ብሎ መገረሉ ተጨነቀ። በበነጋው ቅዳሴ ቢገባ በቅዳሴ ጊዜ የሚወርድለት የእርሱ ምግብ ሥጋ የተለመደው ሰማያዊ መና ሳይወርድለት ቀረ። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ግራ ገብቶት ወደ ፈጣሪው ፊቱም አለቀሰ። ያን ጊዜ ጌታ ከአእላፍ መላእክት ጋር ወረደ ከእናትህ ማኅፀን የመረጥኩህ ወዳጄ፣ ልጄ ይምርሐነ ክርስቶስ እንዲህ የምታለቅሰው ምን በደልኩህ? ቢለው ጌታዬ ማልቀስ ይበዛብኛልን? ያስለመድከኝን ስታስቀርብኝ ከዚህ ሌላ ምን የሚሆን አለና? መኖርስ ለእኔ ከእንግዲህ ወዲህ ምን ትርጉም አለው? ቢለው ጌታም ያሰብከውን አንተ ታውቀዋለህ፣ ያስለመድኩህ + የቀረብህ በክፉ ሐሳብህ ነው አለው።

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ደንግጦ ጌታ ሆይ እኔስ በሐሳብ እንጂ በግብር አላደረኩትም። በዚህ አዘንብኸኝን? ብሎ በግንባሩ ተደፋ። ጌታም ካሰብከው ምን ቀረህ? ቢለው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ታዲያ እንደነሳኸኝ ትቀራለህ ወይስ ትሰጠኛለህ? አለው። ጌታም በዚህ

ሕፃኑን ገደለው አሉት። ንጉሡም ወታደሮች ላከ። በዚህ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ለእናቱ ተገልጸው ምንም ሲደርስበት እንደማይችል ነገሬውና አጽናንተው እርሱን ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት። በዚያም ትምህርት ተምሮ፣ ዲቁና ተቀብሎ በእስራኤልና በግብፅ እየተዘዋወረ ቅዱሳት መካናትን በመሳለምና ሕሙማንን በመፈወስ፣ ወንጌልንም በማስተማር ቆየ።

ከዕለታት በአንድ ቀንም ጌታ ተገልጾ፦ ሚስት አግብተህ ቅስና ተቀብለህ አገልግለኝ አለው። እርሱ ግን ጌታ ሆይ ሚስትስ አላገባም፣ እኔ በድንግልና ሕይወት ተወስኜ አንተን እያገለገልኩ መኖር እፈልጋለሁና አባክህ ፈጣሪዬ ይህን ሐሳብ ይቅር በለኝ ብሎ ከጌታ ጋር ክርክር ገጠመ። ጌታም የምታገባት ሴት እንዳንተ ቅድስት፣ ድንግል ናት። የምታገባትም በሐሳብ እንድትረዳህ ነው አለው። ይምርሐነ ክርስቶስም ሴት ከእኔ ጋር ሆና እንዴት በድንግልና ልኖር እችላለሁ? ብሎ ጌታን ቢጠይቀው በሥጋዊ ፈቃድ እንዳይፈልጋት ቃል ተገብቶለት ከነገደ ሌዊ ከካህናት ወገን የተወለደችውን ቅድስት ሕዝባን አግብቶ ቀሰሰ።

አንድ ቀን ይምርሐነ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ኪዳን ሲያደርስ እግዚአብሔር አብ ወሀቢ ብርሃን ሲል /ብርሃን የሚሰጥ አምላክ/ ጌታም፦ 'አቤት' አለው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ምነው በሰው ሀገር ረሃብና ፈቃድህ ቢሆን ወደ ሀገሬ መልሰኝ አለው። ጌታም የወለደች እናት ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? እንዴት እረሳሃለሁ? አንተ ለእኔ ልጅ አይደለህምን? በል አሁን ወደ ሀገርህ ሒድ፣ እኔም ካንተ ጋር ነኝ፤ ጠባቂ መልአክ ሩፋኤል ይከተልሃል። ያሳድድህ የነበረው ንጉሥ ሞቷል አለው።

በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ተሰብስበው ኪዳን ያስደርሱ የነበሩት ምእመናን ኪዳኑን አቋርጠህ ወደ የምታወጋው ደከምህ ነውን? አሉት። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም የሆነውን ሳይገልጽላቸው እንቅልፍ እንደሰመመኝ ወሰድ አድርጎኝ ነው ያቋረጥኩት ብሎ ኪዳኑን ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሔደ። ለቅድስት ሕዝባ የሆነውን ሁሉ

ሸ. ዐፄ ገብረ መስቀል

ዐፄ ገብረ መስቀል ዘአክሱም ንጉሠ ኢትዮጵያ የተባለው ጻድቅ ትውልድ ሀገሩ አካለ ጉዛይ፣ ልደቱ ኅዳር ፩ ቀን ሲሆን የመነኮሰው አቡነ እንጦንዮስ ዘደብረ መዓር ነው። የአቡነ ክርስቶስ ቤዛነ ልጅ ነው። ይህ ጻድቅ ዳግማዊ ኤልያስ የሚል የቅፅል ስም አለው። እፀ (ከቆዳ የተሠራ ልብሱ) እንደ ክንፍ ሆኖ በአየር ላይ እየተንዘ ስብከተ ወንጌልን እያስፋፋ፣ ደመና እየጠቀሰ ዝናብን ያዘንብ የነበረ፣ ክፉ ቀን ሆኖ የተከዜን ወንዝ ባርኮ ወተት ያደረገ፣ ከአንዱ ገዳም ወደ አንዱ ገዳም ሲዘዋወር በነፋስ ተጭኖ ይጓዝ የነበረ፣ ንፋስ የተገዛለት ባሕሮች ወተት የሆኑለት አባት ነው። ይህ ጻድቅ በራስጌው ወንጌልን፣ በግራ ተአምረ ማርያምን፣ በግርጌው ድርሳነ ሚካኤልን፣ በግራው መጽሐፍ ቅዱስን፣ ደረቱ ላይ ሃይማኖተ አበውን አድርጎ የሚፀልይ አባት ስለነበረ፥ ቅዱሳን ይህንን ሲያዩ፦ ለምንድነው ብለው ሲጠይቁት "ሰይጣን በአራቱ ማዕዘን እንዳይቀርበኝ፣ ከልቤ ከደረቴ ላይ ያደረኩትም ቃሉን ማመኔን ለማረጋገጥ እና የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ እነዚህ መጽሐፍት መሆናቸውን ለመመስከር ነው" ብሎ ይናገር ይመልስላቸው ነበር።

ዐፄ ገብረ መስቀል ጊዜ ሞቱም ሲደርስ መነኩሳቱን ሰብስቦ ትንሽ ልጸልይ ብሎ ከእነርሱ ተለይቶ በጸሎት ላይ እንዳለ አርፏል። ነፍሱ ከሥጋው ሲለይ እናብስት ተሰበሰቡና አስከሬኑን እየጠበቁ አገኙአቸው። መነኩሳቱም እየተደነቁ ዐፅሙን ወስደው በአቡነ ጰንጠሌዎን ገዳም ከመንበሩ ሥር ቀብረውታል። በስሙ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ምዕራባዊ ትግራይ ሀገረ ስብከት ደብረ ዓባይ አጠገብ የሚገኝ ሲሆን፤ ገዳሙም አቡነ ገብረ መስቀል ዘአክሱም ይባላል። እረፍቱም መጋቢት ፳ ቀን ነው።

፫.፪. ከዮዲት እስከ አሕመድ ግራኝ

ሀ. ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ /በ፲፩ኛ ዓ.ም/

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ አባቱ ግርማ ስዩም ይባላል። ቅዱስ

ላሊበላ ከገሮን ስዩም የሚወለድ ሲሆን ለቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ የአጎት ልጅ ነው። ከቅዱስ ላሊበላ በፊት የነገሠው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ነው። መጋቢት ፳፱ ቀን ተወለደ። የነገሠውም ዐርባ ዓመት ነው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እጅግ መልከ መልካም ያማረ ደም ግባቱ የተወደደ በመሆኑ በሕፃንነቱ የተመለከቱት ጠበብት ሁሉ የተሰየ ሀብት እንዳለው እንደሚነግሥም ተናግረውለት ነበር። እናቱ ለጥምቀተ ክርስትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ስትወስደውም ሊቀ ጳጳሱን አገኘች። ሊቀ ጳጳሱም ሕፃኑን ሲመለከተው ክብረ ጸጋው ተገለጸለት ሕፃኑን አጥምቆ፣ ቀድሶ አቁርቦታል። ለእናቱና ለሕዝቡም ስለ ሕፃኑ ታላቅነት መስክሯል:

ሕፃኑም በጸጋ እግዚአብሔር ከመከበሩ የተነሣ የእናቱን ጡት ሳይጠባ ቢውልም፣ እናቱ ምን ሆነ ብላ አብዝታ ስለተጨነቀች በዘጠኝ ሰዓት ስለ እናቱ ሲል ጠብቷል።

በወቅቱ የነበረው ንጉሥ የይምርሐነ ክርስቶስ አጐት ጠጠውድም ከእኔ በኋላ ሥልጣኔን የሚረከበኝ ዘውዴን የሚወርስ ማን ነው? እያለ ሲጨነቅ በሕልም ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ እንደሚወርስ ተነገረው። በዚህ ምክንያት ንጉሡ እንደ ሄሮድስ በክፉ መንፈስ ተሞልቶ መንግሥቱን የሚወርሰው ደገኛ ሕፃን እርሱ ነውና ሕፃኑን ልየው ብሎ ወደ እናቱ መልእክተኛ ልኮ አስመጣው። ሕፃኑም አፍንጫው የገነት ተክል የመሰለ፣ ከአፉ የሚወጣው መዓዛ የሚጣፍጥ፣ ዓይኖቹ ያማሩ፣ ውብ ልጅ መሆኑን ሲመለከት ከቅንዓት ሥጋዊ የተነሣ ሊገድለው አሰበ።

አማካሪዎቹንም ጠርቶ በዚህ ሕፃን ምን ላድርገው? ብሎ ቢጠይቃቸው አትግደለው፥ ብትገድለው በእግዚአብሔር ዘንድ በነፍስ ትጠየቃለህ፤ ነገር ግን መንግሥትህን እንዳይወርስ ትምህርት አታስ ተምሮው እረኛ ሆኖ ይኑር ብለው መከሩት። ንጉሡም ሳምንት ከእርሱ ጋር ካስቀመጠው በኋላ ወደ እናቱ መለሰው። ንጉሡ ጥቂት ቀናት ከሰነበተ በኋላ መልዕክቶቹ እንደገና ሕፃኑ ተማረም አልተማረም ፈቃደ እግዚአብሔር ስለሆነ ያየከው ሕልም ሳይፈጸም አይቀርምና ሕፃኑን ግደለው አሉት። ንጉሡም ወታደሮች ላከ። በዚህ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ለእናቱ ተገልጸው ምንም ሊደርስበት እንደማይችል ነገሯ ውና አጽናንተው እርሱን ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት። በዚያም ትምህርት ተምሮ፣ ዲቁና ተቀብሎ በእስራኤልና በግብፅ እየተዘዋወረ ቅዱሳት መካናትን በመሳለምና ሕሙማንን በመፈወስ፣ ወንጌልንም በማስተማር ቆየ።

ከዕለታት በአንድ ቀንም ጌታ ተገልጾ፦ ሚስት አግባህ፣ ቅስና ተቀብለህ አገልግለኝ አለው። እርሱ ግን ጌታ ሆይ ሚስትስ አላገባም፣ እኔ በድንግልና ሕይወት ተወስኜ አንተን እያገለገልኩ መኖር እፈልጋለሁና አባክህ ፈጣሪዬ ይህን ሐሳብ ይቅር በለኝ ብሎ ከጌታ ጋር ክርክር ገጠመ። ጌታም የምታገባት ሴት እንዳንተ ቅድስት፣ ድንግል ናት። የምታገባትም በሐሳብ እንድትረዳህ ነው አለው። ይምርሐነ ክርስቶስም ካሉት ከእኔ ጋር ሁና እንዴት በድንግልና ልኖር እችላለሁ? ብሎ ጌታን ቢጠይቀው በሥጋዊ ፈቃድ እንዳይፈልጋት ቃል ተገብቶለት ከነገደ ሌዊ ከካህናት ወገን የተወለደችውን ቅድስት ሕዝባን አግብቶ ቀሰሰ።

አንድ ቀን ይምርሐነ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ኪዳን ሲያደርስ "እግዚአብሔር አብ ወሀቤ ብርሃን ሲል /ብርሃን የሚሰጥ አምላክ/ ጌታም "አቤት" አለው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ምነው በሰው ሀገር ረሳኸኝ ፈቃድህ ቢሆን ወደ ሀገሬ መልሰኝ አለው። ጌታም የወለደች እናት ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? እንዴት እረሳሃለሁ? አንተ ለእኔ ልጅ አይደለህምን? በል አሁን ወደ ሀገርህ ሒድ፣ እኔም ካንተ ጋር ነኝ፣ ጠባቂ መልአክ ሩፋኤል ይከተልሃል። ያሳድድህ የነበረው ንጉሥ ሞቷል አለው።

በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኑ ተሰብስበው ኪዳን ያስደርሱ የነበሩት ምእመናን ካህናት አቁርጠህ የምታወጋው ደክሞህ ነውን? አሉት። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም የሆነውን ሳይገልጽላቸው እንቅልፍ እንደሰመመን ወሰድ አድርጎኝ ነው ያቋረጥኩት ብሎ ከሸኛቸው ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሔደ። ለቅድስት ሕዝባ የሆነውን ሁሉ ነገራትና ፈቃደኛ ከሆንሽ ወደ ሀገሬ አብረን እንሒድ አላት። እሷም እሺ ብላው አብረው ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በወሎ ክ/ሀገር በላስታ አውራጃ በምትገኘው በአንዲት ቦታ ተቀመጠ። ንጉሡ ጠጠውድም ሙቶ ስላገኘው ያለምንም ችግር ነገሠ። በዚያች ቦታ ለ፲፭ ዓመት መና ከሰማይ እየወረደለት በድንኳን እየቀደሰ ምእመናኑን ያቆርብ ነበር። አንድ ቀን ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በዚያች ቦታ ሕዝቡን ግብር አብልቶ ነበርና አዋቂ ነን ባዮች ከቤቱ ገብተው ንጉሥ ሆይ ዛሬ አንድ ምክር ልንመክርህ መጥተናል እንድትሰማን አሉት። አንተ ልበ አምላክ ከተባለው ከቅዱስ ዳዊት፣ ሦስት ሴቶች አግብቶ ከነበረው ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ስለዚህ ሌላ ሚስት አግባ ብለው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስን መከሩት። እርስዎም እናንተ የሰይጣን መልእክተኞች፥ አመንዝር ብላችሁ የምትመክሩኝ ለምንድን ነው? ከእኔ ሒዱ፣ ብሎ አሳፍሮ ላካቸው።

ለሚስት ግን ለምን ይህን ሐሳብ እንዳቀረቡለት በሃሳቡ ሲያስብ ስል አደረ። በቀጣ ስላባረራቸው ምንው ምን ፈልገው ይሆን ብሎ መንፈሱ ተጨነቀ። በበነጋው ቅዳሴ ቢገባ በቅዳሴ ጊዜ የሚወርድለት የእርሱ ምግብ ሥጋ የተለመደው ሰማያዊ መና ሳይወርድለት ቀረ። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ግራ ገብቶት ወደ ፈጣሪው ፊቱን አለቀሰ። ያን ጊዜ ጌታ ከእልፍ መላእክት ጋር ወረዶ ከእናትህ ማኅፀን የመረጥኩህ ወዳጄ፣ ልጄ ይምርሐነ ክርስቶስ እንዲህ የምታለቅሰው ምን በደልኩህ? ቢለው ጌታዬ ማልቀስ ይብዛብኝን? ያስመረጥከኝን ስታስቀርብኝ ከዚህ ሌላ ምን የሚሆን አለና? መኖርስ ለእኔ ከእንግዲህ ወዲህ ምን ትርጉም አለው? ቢለው ጌታም ያሰብከውን አንተ ታውቀዋለህ፣ ያስመረጠከሀ፥ የቀረብህ በክፉ ሐሳብህ ነው አለው።

ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ደንግጦ ጌታ ሆይ እኔስ በሐሳብ እንጂ በግብር አላደረኩም። በዚህ አዘንክብኝን? ብሎ በግንባሩ ተደፋ። ጌታም ካሰብከው ምን ቀረህ? ቢለው ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ታዲያ እንደነሳኸኝ ትቀራለህ ወይስ ትሰጠኛለህ? አለው። ጌታም በዚህ ቦታ ክፉ አስበህበታልና አልሰጥህም፣ ነገር ግን ሥጋህ በሚቀበርበት እኔ ባዘጋጀሁልህ ቦታ ግር ሳትፈልግ በድንጋይ የተከደነች እስከ ዕለተ ምጽአት የማትፈርስ ቤት መቅደስ ትሠራለህ በዚያች ቦታ የለመድከውን አወርድልሃለሁ አለው።

ትውልድ ሁሉ የአንተን መቅደስ ያስቡት ዘንድ የእኔም ረቂቅነትና ጥበብ ይታወቅበት ዘንድ ለቤተ መቅደሱ ሥራ አትጨነቅ አለው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ጌታ ሆይ ይህች ቦታ አወዳታለሁ አትናቅብኝ በዚህ ልቀመጥ ብሎ አምላኩን ተማፀነ። ጌታም አንተ የወደድከውን ንቄብህ አይደለም። ነገር ግን የማነግሠው አረመኔ ንጉሥ ስለእለ ይህቺን ቦታ ያቃጥልብሃል። እኔ በፈቀድኩት ቦታ ግን የምትሠራው ቤተ መቅደስ እስከ ዕለተ ምጽአት ማንም አይነካትም አለው። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ጌታ ሆይ ከአንተ ከአባቱ ፈቃድስ እንዳልወጣ ዕውቃለሁና ግን ወደ ቦታዋ ይመራኛል ቢለው ቅዱስ ሩፋኤልን አዘዘለት።

ቀድሶ ሕዝቡን አቁርቦ እግዚአብሔር አምላክ ወዳመለከተው ቦታ ተጓዘ። ወደተባለው አካቢ በደረሰ ጊዜ ሕዝቡ ወደዚያች ሥፍራ እንዳይሔድ አጥብቀው ተማፀኑት። በምትሔድበት ቦታ አጋንንት ያደረበት ባለ ውቃቢ አለ። የዚያም ሰው ውሾች ሰው አያስጠጉም፣ ክፉዎች ናቸው፣ ይተናኮሉሃልና አባክህ እንዳትሔድ ብለው ለመኑት። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ወደተባለው ቦታ ተጓዘ እንደተባለውም ውሾቹ በአስፈሪ ሁኔታ እየጮኹ መጡበት። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ደነገጠ፣ ፈራ። ያን ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ተገልጾ አትፍራ፣ አትደንግጥ ብሎ አጽናናው። ውሾቹም ፊታቸውን አዙረው ፊት ፊት እየመሯቸው ቤት አስገቧቸው።

የባለ ውቃቢው ሚስት የአየር ጋኔን የያዛት ነበረችና ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስን ስታይ አስገራት፣ መሬት ላይም ጣላት። ቦታው ለአጋንንት የሚገበርበት፣ አጋንንት የሰፈሩበት ቦታ ነበርና ውሾች ሳይተናኮሏቸው እየመሩ ከቤት ሲያደርሷቸው የተመለከቱት የጠንቋዩ አገልጋዮች ከጌታችን የበለጠ ጠንቋይ መጥቷል እያሉ እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ጠንቋዩ ከቤቱ ቢገባ አስደናቂ ነገር ጠበቀው። በቤቱ ውስጥ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ተቀምጦ እነዚያ ክፉ ውሾች እግሩን ሲልሱት ተመለከተ። ይህን የሰሙ የአካባቢው ሰዎች ሲተናኮሏቸው ፈሩ። ለአጋንንቱና ለጠንቋዩ የተገዙ ነበሩና ሁከት ሲፈጥሩባቸው ቢኖሩም ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ሰዎቹን አስተምሮ፣ አሳምኖና አጥምቆ ጣዖታቱንም አጥፍቶ ሥራውን ጀምሯል።

ከዚህ በኋላ ለቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ጌታ ተገልጾ ባቤተ መቅደሱ መሥሪያ የሚያገለግሉ ማገኛውንም ቁሳቁስ ከኢየሩሳሌም በሠረገላ እያመጣህ ሥራ። አሠራሩም በባሕር ላይ /ባሕሩ አጋንንት ሰፍረውበት የነበረው/ ይሁን አለው። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በቀን ፭ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም እየተጓዘ ለቤተ መቅደሱ የሚውሉ ቁሳቁሶችን በደመና ሠረገላ ያመላልስ ነበር። በዚህ ሁኔታ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን መስከረም ፲፫ ቀን ጀምሮ ሰኔ ፳፩ ቀን በእግዚአብሔር ቸርነት ሥራውን ፈጸመ። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በሚቀድስበት ጊዜ ተጨማሪ ቁም ሆነ ሊያቆም የለውም። ብቻውን ሥርዓተ ቅዳሴ በሚያከናውንበት ሰዓት ቅዱስ ሩፋኤል ሰማያዊ ኅብስት በቀኝ እጁ፣ ጽዋውን በግራ እጁ እየሰጠ ይራዳው ነበር። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በዚህ ዓይነት ለ፵ ዓመታት በቅዳሴ አገልግሏል።

በዚያው ሀገር ባሕር ውስጥ ገብቶ የሚጸልይ መነኩሴ ነበር። ቅዱስ ሩፋኤል ሰማያዊ ኅብስተ መና ከሰማይ ይዞ ሲወርድ ተመልክቶ ለእርሱ የወረደለት መስሎት ሊቀበል ከሚጸልይበት ባሕር ወጥቶ ወደ ቅዱስ ሩፋኤል ቢቀርብ ፥ መልአኩ እኔ ለንጉሥ እንጂ ለመነኩሴ ቁርባን አልታዘዝኩም አለው። መነኩሴውም እንዴት ያለ ንጉሥ ነው? ጠጅ እየጠጣ ሥጋ እያማረጠ ሰማያዊ መና የሚወርድለት? ይህ አምላክ ግን እንደሚያገለግለው አላወቀም፣ በማለት ወደ ባሕሩ ሊወረወር ሲል የእግዚአብሔር መልአክ ገሠጸው። ይህ ንጉሥ ሥጋ ይበላ፣ ጠጅ ይጠጣ አይደለምን? ስለ እርሱ ሥራስ የምታውቀው አለህን? በል ከዛሬ ጀምር አስተምር። ማስተማር ትልቅ ሥራ ነውና ስለባሪያዬ ስለይምርሐነ ክርስቶስ ያየኸውን መስክርለት አለው። በምድረ ግብፅና በእስራኤል ለሚገኙ ሕዝቦች ቅድስናውን ንገራቸው። አንተም በምድር ሳይሆን በሰማያዊ ቦታ ከእርሱ ጋር ትገናኛለህ፤ በክብር ከእርሱ ጋር ትቀመጣለህ አለው። መነኩሴውም እንደታዘዘ አደረገ። ይህን ታሪክና ዜና የሰሙ ሰዎች ወደ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ይመጡ ነበር። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም ስለ እኔ ሁኔታ ማን ነገራችሁ? ቢላቸው አንድ መነኩሴ ነገረን መጣን አሁን ቀድሰህ አቁርበን አሉት። ከሕዝቡ ብዛት የተነሳ ሥጋ ወደሙን ሲያቀብላቸው ጀንበርዋ ልትጠልቅ ስትል ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ ፈጣሪውን ለምኖ እንዳትጠልቅ አድርጓታል።

ጌታም ከዚያ በኋላ ለቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ በታህን ረግጠ የጸለየ እኔ ኃጢአቱን ይቅር እለዋለሁ፤ በዚህች ቦታ የተማፀነ፣ የተሳለ እኔ ስለቱን እሰማዋለሁ፤ አንተን ብሎ የሚመጣ እንግዳ ሁሉ ካሰበበት ቦታ ሳይደርስ በመንገድ ላይ አላሳድርበትም፤ ከዚህ ቦታ የሚያድረውን እኔ እባርከዋለሁ፤ ያንተን በረከት አሳድርበታለሁ፣ ብሎ ቃል ኪዳን ገባለት። ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስም በተወለደ በመቶ ዓመቱ በጥቅምት ፲፱ ቀን አርፎ እርሱ ባሳነጸው በቤተ ገብርኤል በወርቅ ሳጥን ተቀብሮአል።

ሊ. ቅዱስ ሐርቤ /በ፲፪ኛ መቶ ክፍለ ዘመን/

ሐርቤይ ኢትዮጵያዊ አባቱ ጃን ስዩም እናቱ አቴኔ ዑፅፍተ ልብሰ ወርቅ ይባላሉ። ሀገሩ ላስታ ቡግና ሲሆን የላሊበላ ወንድም ነው። ስመ መንግሥቱ ገብረ ማርያም ነው። ጃን ስዩም ዑፅፍተ ልብሰ ወርቅ ከሞተች በኋላ ኪራ ወይላን አግብቶ ሐርቤንና ራሐልን ወለደ። በእናቱ ከቅዱስ ላሊበላ ጋር አይገናኙም። በእህቱ ምክር ተመርቶ መንግሥቱን ያዘ። ወንድሙን ላሊበላን አይወደውም ነበር። ይህም ስለ ሥልጣን መንግሥት ነው።



በራቱ ቀለፉን ነገሥታት

በኋላም ተጸጽቶ ቅዱስ ላሊበላን ይቅርታ ጠይቆ መንግሥቱን እንደሚያስረክበው ቃል ገብቶለት አንድ ዓመት ከቆየ በኋላ ንጉሥ ሐርቤይ /ገብረ ማርያም/ ቅዱስ ላሊበላን ከግብፅ ሀገር አስመጣው። ቅዱስ ሐርቤይ ሥልጣነ መንግሥቱን ለቅዱስ ላሊበላ አስረክቦ ዐርባ ዓመት በንግሥና ከቆየ በኋላ የካቲት ፲፯ ቀን በተወለደ በ፹ ዓመቱ ዐርፎ እራሱ በሠራው ቤተ መቅደስ ተቀበረ። በእርሱ ስም የታነጹ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አሉ።

ሐ. ቅዱስ ላሊበላ

ቅዱስ ላሊበላ አባቱ ጃን ሥዩም እናቱ ኪርወርና ይባላሉ። መጋቢት ፳፱ ቀን ተፀንሶ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ተወለደ። በተወለደም ጊዜ በንብ ስለተከበበ እናቱ ማር ይበላል ለማለት "ላል ይበላል" ብላዋለች። በአገውኛ "ላል" "ማር" ማለት ነውና። ከዚህም የተነሣ ስሙ ላሊበላ ተባለ። ቅዱስ ላሊበላ በአባቱ በንጉሡ ቤት አባ ዳንኤል የተባለ መምህር ተቀጥረውለት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቁም ጽሕፈቱን ሳይቀር ጠንቅቆ ተምሯል። አባቱ ከሞተ በኋላም ካለው ጽኑ የትምህርት ፍላጎት የተነሣ ወደ ጎጃም ወርዶ የብሉያትንና የሐዲሳትን ትርጓሜያት ጠንቅቆ ተምሮ ተመልሷል። ትርጓሜ መጻሕፍትንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ተምሮ ወደ ትውልድ ሀገሩ ወደ ሮሃ ሲመለስ ንጉሡ የአባቱ ልጅ ታላቅ ወንድሙ ሐርቤ (ገብረ ማርያም) ተቀብሎ ሥርዓተ መንግሥትን እያስተማረ ከእርሱ ጋር አስቀመጠው

ይሁን እንጂ መኳንንቱና ሹማምንቱ ስለቅዱስ ላሊበላ የተነገረውን ትንቢት የሚፈጽም መሆኑን ለንጉሡ እየነገሩ በጥላቻ እንዲመለከተው አደረጉ። ንጉሡ ከሀገር ለማባረር ካሰበሊዚያም ለመግደል በሚያወጣ በሚያወርድበት ጊዜ ለንጉሡ የእናትም የአባትም ልጅ የሆነች ለቅዱስ ላሊበላ ግን የአባቱ ልጅ ብቻ የሆነች ዮዲት ቅዱስ ላሊበላን ለመግደል ተንኰል መጠንሰስ ጀመረች። ቅዱስ ላሊበላ ደግሞ ጌታችን በዕለተ ዓርብ የጠጣውን ሐሞትና ኮምጣጤ ለማሰብ ሁልጊዜ ዓርብ ዓርብ ኮሶ ይጠጣ ነበርና እንደተለመደው ኮሶውን አዘጋጅተሽ ላኪልኝ ሲላት ለተንኰሏ ስለተመቻት ደስ አላት። ስለዚህ መርዝ ቀላቅላ ላከችለት። ተልኮ ያመጣውም ቀምሼ እሰጣለሁ ብሎ አንዴ ቢጎነጭለት ወዲያውኑ ሞቶአል። ላሊበላም ይህ ሁሉ የሆነ በኔ ምክንያት አይደለምን? ብሎ የተረፈውን ጨለጠው። ቅዱስ ገብርኤልም ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ከሥጋው ሙቀት ልምላሜ ሳይለይ ከጌታ መንበር ፊት አደረሰው። ሰባቱ ሰማያትንም አስጎበኘው። ጌታችንም ኢየሩሳሌም ለመሔድ ተነሥተው በበርሃ የሚቀኑ ወገኖችን አስቢያለሁና፤ በተወለድክበት በርሃ ኢየሩሳሌምን ትሠራለህ፤ አንተ የምትሠራውንም ማንም አይሠራውም አለው። ከትሕትና የተነሣ ብዙ ቢከራከርም ጌታችን አስረድቶት፤ ቃል ኪዳንም ተቀብሎ ተመልሷል። ከዚህ በኋላ በሦስተኛው ቀን ወደ ሥጋው መለሰው። ከእንቅልፉም እንደሚነቃ አፈፍ ብሎ ተነሣ። ሙቀት ሳይለይ አይሆንም ብለን እንጂ ገንዘን ልንቀብርህ ነበር፤ ወዴት ደር

መጣህ? አሉት ፍቅር እንደሞት የጸናች እንደሆነች አታውቁምን? ወንድሜ ጥፋቴን! እንቴ ሞቴን ከተመኙልኝ ከእንግዲህ እዚህ ምን ያስተምጠኛል ብሉ ቅሉን ጨርቄን ሳይል ከሰው ይልቅ ከአራዊት ጋር መኖርን መርጦ በረሃ ገብቶ በዓት ሠርቶ ተቀመጠ፡፡ ከዚህ በኋላ መልአክ እግዚአብሔር ተገልጦ በፈቃደ እግዚአብሔር እንዲት ብትቴና ወደ አንተ ዘንድ ትመጣለችና ተቀበላት የሚል ቃል አሰምቶት ተሠወረ፡፡ በማግሥቱ መስቀል ክብራ በዱር ውስጥ እንጨት እየለቀመች ሳለች ድንገት አጠገቡ ደረሰች፤ መልአክ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ስለ እንቺ ነገረኝ ባለት ጊዜ ያንን ወስዶ ለባቷ ነገረችው፤ አባቷም ሐዴሽ ጥሪው አለት፡፡ ጠራችውና መጣ አባቷም የመልኩን ቀናነት የቃሉን ጥዑምነት አይቶ ልጁን መስቀል ክብራን በሕገ በሥርዓት አጋባቶታል፡፡ እነርሱም እንደ አብርሃምና እንደ ሣራ ተዋድደው ምግባር ትሩፋት እየሠሩ የሚኖሩ ቢሆኑ ለዘማን በሐሰተኞች እንደበት ሰባል የታጨችውን ሴት ገድ ብሉ ደፈራት ብሉ ከንጉሥ ፊት አሳጣው፡፡ ንጉሡም አስጠርቶ ጠየቀው ቅዱስ ላሊበላ እውነቱን ቢገልጽም ከሰሾቹ የሐሰት ምስክር ስለአስመሰከሩበት እርባ ጅራፍ አስገርፈው፡፡ በዚህ የተነሣ ዳግመኛ በዚህ ዓለም መኖር በቃኝ አስመርርት ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሦ በበረሃ መኖርን መርጦ በተነሣ ጊዜ ትከተለው ዘንድ መስቀል ክብራን ጠየቃት፡፡ እሷም ፈቃደኛ በመሆኗ ተያይዘው በረሃ ገብተው በዓት ሠርተው ተቀመጡ፡፡ በዚያም ሳለ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተገልጸ ኢየሩሳሌም ሐዶ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነሥቶ ይመለስ ዘንድ ነገረው፡፡ እርሱም ይህች እሁቴስ ከኔ ተለይታ እንደምን ትሆናለች ባለ ጊዜ ለእርሷስ ቅዱስ ሚካኤል አለላት ብሎት በአምሳለ ወሬዛ ሠናየ ላህይ (በመልከ መልካም ወጣት ተመስሎ) ሆኖ ቅዱስ ሚካኤል አክሱም ከሴቶች ገዳም ወስዶ አደራ ሰጣት፡፡ ላሊበላንም ቅዱስ ገብርኤል በክንፉ ነጥቆ ወስዶ ኢየሩሳሌም አደረሰው፡፡ በዚያም ቅዱሳት መካናትን አይቶ እጅ ነስቶ በሬስን የርዳኖስ ተጠምቆ በደስታ ተመስጦ ሳለ ጌታ በብሩህ ደመና ተገልጸ በተስፋህ የጸናውን! በኪዳንህ የተማፀነውን! ከርደተ ገሃነም አድንልሃለሁ፡፡ መቃብርህን

የተሳለመ መቃብሬ ጎልጎታን እንደተሳለመ ይሆንለታል ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡፡ ከዚህም በኋላ ቅዱስ ገብርኤል ዳግመኛ በክንፉ ነጥቆ መስቀል ክብራ ካለችበት ገዳም አድርሶት ተሠወረ፡፡ በዚያችም ሌሊት እግዚአብሔር በሕልም ለንጉሡ መንግሥትህን ለወንድምህ ለላሊበላ ስጥተህ ኀልፈት የሌለባትን መንግሥተ ሰማያትን ፈልግ ብሎት መንግሥቱን ለላሊበላ አስረክቦ ከበረሀ ወድቆ ከፍጹምነት ደርሶ አርፏል፡፡ ቅዱስ ላሊበላም መንግሥቱን ከያዘ በኋላ በከተማው በደብረ ሮሃ ዐሥራ አንድ አብያተ ክርስቲያናትን ከዳገኝ አስፈልፍሎ አሠርቷል፡፡

መ. <u>ቅድስት መስቀል ክብራ</u>

የቅዱስ ላሊበላ ሚስት፤ በ፲፫ኛው ምዕት የነበረች የዓረቡ ትብጣዊ ጸሐፊ መስቀል ገብራት ይላታል፡፡ በገድለ ላሊበላ እንደ መጣን ሲመለከታት፤ የገብጽ ምንጭ ከላሊበላ ሁለት ልጆች እንዳሏት ይነገራል፡፡ እነዚህ ከመስቀል ክብራ አብራክ የወጡ እንደሆነ ገልጸ አይናገርም፡፡ በአንዳንድ የሕፈ ታሪክ እንደሚነገረው ይትባረክ ልጇ ሳይሆን አይቀረም፡፡

በላሊበላና በአፄ ሐርቤ መካከል ጠብ በተነሣ ጊዜ ከባሏ ጋር ተሰዳለች፡፡ ላሊበላም ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመራ እርሷን መጸበይ ከሚባል አክሱም አጠገብ ከሚገኝ ሥፍራ ትቷት ሄደ፡፡ ሲመለስ አብረው ወደ ላስታ መጥተው ሁለቱም በዙፋን ላይ ተቀመጡ፡፡

ባለቤቷን በምግባረ ሠናይ ትወዳደረው ስለነበረ ለገዳማቱ እርሷም ጉልት ትሰጥ ስለነበረ ከአፄ ላሊበላ ጋር ስሟ ተመዝግቧል፡፡ በሕንፃም በኩል ከ፲፩ አንዱን የድንጋይ ፍልፍል ቤተ ክርስቲያን የሠራች እርሷ እንደሆነች ይነገራል፡፡

ከባለቤቷ ሞት በኋላ እንደገና ወደ መጸበይ ተመልሳ በጸሎት በስጊድ ተጠምዳ ስትኖር ዐርፋ እዚያው ተቀብራለች፡፡ ከዕረፍቷ በኋላ ታቦት ተተርጉሞላታል መታሰቢያዋ ሐምሌ ፯ ቀን ይከበራል፡፡

እንድታገባቸው አመላከቷት ይዛቸው ገባች፡፡ እፍኝ የስንዴ ዱቄት ያለበት እንቅብ ነበር፡፡ እጃቸውን ቢጭኑበት ምልቶ ፈሰሰ በዚህ ዓይነት ሌላውንም የሚያስፈልጋትን ሁሉ በእጃቸው እየዳሰሱ አበርክተውላታል፡፡ እሷም መጋቢት ፲፪ ቀን በቅዱስ ሚካኤል ስም ደግሣ ስታበላ ስታጠጣ ውላለች፡፡ ያንንም በረከት የወሰደው ሁሉ የረሀቡ ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ሲመገበው ኑሯል፡፡ ጻድቁ በተወለዱ በዐሥራ አምስት ዓመታቸው በወላጅ አባታቸው በካህኑ ጸጋዘአብ ግብረ ዲቁናንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ ጌርሎስ /ቄርሎስ/ ከተባሉት ግብፃዊ ጳጳስ ዲቁናን ተቀበሉ፡፡ በሃያ ሁለት ዓመታቸውም ቅስናን ተቀብለው ከጓደኞቻቸው ጋር ወደ አደን ሄደው ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጸ ከዚህ በፊት በደማስቆ ቅዱስ ጳውሎስን ለሐዋርያነት እንደመረጠው እርሳቸውንም ለኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በሐዋርያነት መርጦ ከአውሬ አዳኝነት ሰውን በትምህርተ ወንጌል እያደኑ ለመንግሥተ ሰማያት እንዲያበቁ ጠራቸው፡፡ የሐዋርያነት ስማቸውንም ተክለ ሃይማኖት ብሎ ሰየመው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተክለሃይማኖት ተብለው መጠራት ጀመሩ ሁሉን ትተው ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን ለማስተማር በምናኔና በሐዋርያነት ተልእኮ ለኢትዮጵያውያን ሐዲስ ሐዋርያ በመሆን የማስተማር ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በተከታታይ ሦስት ዓመት ወንጌልን አስተማሩ፡፡ ተጥለውም በሮፋት ለዘጠኝ ወር አገልግሎታቸውን ፈጽመዋል፡፡ ምድረ ዳሞት /ወላይታ/ በተባለውም ሀገር በሐዱ ጊዜ ንጉሡ ሞተሎሚ ከወዴት መጥተሃል? አላቸው፤ እርሳቸውም አማልክትህን እንዳጠፋ ከጌታ ተልኬ መጥቻለሁ አሉት፡፡ አንተን እንድናመልክህ መጥተሃል! ብሎ በቀኛ አድርጎ ጠመ ግራር ከሚባል ገደል አስጣላቸው፡፡ ቅዱስ ሚካኤልም ነጥቆ አወጣቸው፡፡ ሁለተኛም ይህ መሠርይ ብሉ ሰይፉን ቢወረውርባቸው ከእጁ ተጣብቃ ቀረች፡፡ በዚህ ጊዜ አባታችን ያድኑኛል! ይጠብቁኛል! የምትላቸው ካህናተ ጣዖትህ አያድኑህምን? አሉት፡፡ አስጠርቶ አድኑኝ አላቸው አልቻሉም፡፡ አባታችንም እኔ ካዳንኩህ እነርሱ ካላዳኑህ እነርሱን እንድትቀጣ፤ እነርሱ ካዳኑህ እኔ ካላዳንኩህ እኔን እንድትቀጣ

ቃል ግባልኝ! አሉት፡፡ ቃል ገባላቸው፡፡ ይህም ከሃያ አምስት ዓመት በፊት እናታቸው እግዚእኀረያን አገባለሁ ብሉ ከጣዖቱ ፊት ባቆማት ጊዜ በተፈጸመው ግሩም ተአምራት ልቡን ነስቶት አንድ ጊዜ ገደሉት፤ አንድ ጊዜ አድኑት፤ ከአየር ቤት ሥሩልኝ፤ ከምድር በታች ዘር ዝሩልኝ ሲል ይኖር ነበርና ከዚህ ሁሉ ፈውሰውታል፡፡ ካህናተ ጣዖቱን በሰይፍ አስፈጅቶ እርሱ አምኖ ተጠምቋል፡፡ ከዚያም በእግዚአብሔር ትእዛዝና ፈቃድ ወደ አማራ ሳይንት በመሄድ ከአባ በጸሎተ ሚካኤል ገዳም እህል እየፈጩ ውኃ እየቀዱ እንጨት እየሰበሩ፤ ይልቁንም ሕሙማን እየፈወሱ፤ አጋንንትን እየደመሰሱ፤ ዐሥር ዓመት ኑረዋል፡፡ ቀጥሉም አባ ኢየሱስ ሞዐ ከሚገኙበት ሐይቅ ገዳም በመሄድ ባሕሩን እንደ ደረቅ መሬት በእግራቸው በመርገጥ ወደ ደሴቲቱ በመግባት የንጽሕና ምልክት ልብሰ ምንኩስና ተቀብለው ለዐሥር ዓመት የረድእነት ሥራ በመሥራት ገቢረ ተአምራትን በማሳየት ቆይተው በ፩ሺ፪፻፶፱ ዓ.ም አቡነ አረጋዊ ወደ አቀኑት ደብረ ዳሞ ገዳም በመሄድ ከአበምኔቱ ከአባ ዮሐኒ ቆብና አስኬማ ተቀብለው በገድል በትሩፋት መንፈሳዊ ተጋድሎአቸውን ቀጠሉ፡፡ በመጨረሻም ወደ ሌላ ሥፍራ ለመሄድ በተነሡ ጊዜ ገደሉን መውረድ እንደጀመሩ ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ይመት በቃ ብሉ የሚወርዱበትን ገመድ ከሥሩ ቆረጠባቸው፡፡ ጌታም ስድስት የብርሃን ክንፎች ሰጥቷቸው እየበረሩ ሦስት ምዕራፍ ያህል ሄደው ከዚያ ከገዳመ ዋሊ ገብተዋል፡፡ በዚያም ተሠውረው ከሚኖሩት አበው ጋር ተገናኝተው እህል ውኃ ሳይቀምሱ ፵፰ ቀን ቆይተዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ኢየሩሳሌም ደርሺ ቅዱሳት መካናትን እጅ ነሥቼ ልምጣ ብለው በሠረገላ ብርሃን ተጭነው ሲሄዱ በኤርትራ በረሃ አንድ ሰው ሞቶ አገኙ፡፡ አንተ ምውት ክርስቲያን ከሆንክ በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥ ቢሉት ተነሥቷል፡፡ ከዚያም አስከትለውት ሄደው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ከኢየሩሳሌም ሊቀጳጳሳት ተገናኝተው በረከት ተቀበሉ፡፡ ሊቀጳጳሱም መነኩሴ በዓት ሠርቶ ብዕዓት ገብቶ በጽሞና በብሕትውና ይኖራል እንጂ ይዞራልን? አንተም እንዲህ ሆነህ መኖር ይገባሃል ብሏቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ከኤርትራ ጀምረው እያስተማሩ

ሠ. <u>ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ /በ፩ሺ፪፻፩ ዓ.ም/</u>

ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ የላሊበላ የወንድም ልጅ ሲሆን አባቱ ሐርቤይ እናቱ መርኬዛ ይባላሉ፡፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ታኅሣሥ ፫ ቀን ማክሰኞ ዕለት ተወለደ፡፡ እንደ ዮሐንስ በድንግልና የኖረ የመንፈስ ቅዱስ መንኮራኩር ሠረገላ ተሰጥቶት እንደፈለገው እየሄደ የሚንቀሳቀስ የበቃ ጻድቅ ነበር፡፡ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ የጌታን መከራ እያሰበ በቁመቱ ልክ ጉድጓድ አስቆፍሮ በዙሪያው ጦር አስበጅቶ ጦሩ እንዲወጋው ዓርብ ዓርብ ዕለት ደሙ እየፈሰሰ እልፍ ይሰግድ ነበር ይህን ዐርባ ዓመት አድርጎታል፡፡

አንድ ቀን ጌታችን በአካል በቤተ መቅደስ ተገልጾለት ወዳጄ፤ ልጄ ነአኩቶ ለአብ ሆይ የዚህች የቅጣት ዓለም ጊዜ በቃህ እኔ ለሰው ልጆች ስል ደሜን ያፈሰስኩት መከራውን የተቀበልኩት አንድ ቀን ነው፡፡ አንተ ግን ዐርባ ዓመት ሙሉ ደምህን፤ እንባህን እያፈሰስክ አቴዘን በአንተ ቤተ መቅደስ ተገኝተው በአንተ አማላጅነት አምነው የተማፀኑትን! ቦታህን ሳይረግጥ ዝክርህን ሳይዘክር ዝናህን ሰምቶ ያሰበህን እንኳ እምርልሃለሁ፡፡ አንተም እስከ ዕለተ ምጽአት ተሰውረህ ስለሰው ልጅ ኃጢአት እየጸለይህ ኑር ብሉታል፡፡

ጌታችንም ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ይጸልይበት የነበረችውን ቦታ /ቤተ መቅደስ/ ልጄ ዐርባ ዓመት ደሙን እንባውን በዚህች ቦታ እንዳፈሰሰ አንተም ድንጋይ ስትውልድ ትታይ ዘንድ እያነባህ ኑር፡፡ እስከ ዕለተ ምጽአት በዚህ ቦታ ለሚመጡ ሕሙማን ስትፈውስ ቆይ አለው፡፡ ዛሬም ከጣራው ፀበሉ ይንጠባጠባል፤ በጋ ከክረምት አይደርቅም፡፡ እንዲያውም ክረምት ይቀንሳል፤ በጋ መጠኑ ይጨምራል፡፡

ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ሲወለድ እናቱ ምጥ ይዟት ካህናት ቅዳሴ ገብተው ሳለ ዲያቆኑ ነአኩቶ ሲል ስለ ተወለደ ስሙ ነአኩቶ ለአብ ተባለ፡፡ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ያሳነጻት እሽተን ማርያም የተባለች ቤተ መቅደስ አለች፡፡ እሽተን የተባለችበት ምክንያት ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ አንጿት ሲያበቃ ማዕጠንት ሲያጥን ብዙ ቅዱሳን ቤተ መቅደሱ

ገብተው ጥትጥቅ ብለው ቆመው ሲመለከት እናንተ ደግሞ እንዴት መጣችሁ ብሉ ቢጠይቃቸው ማዕጠንቱን አሽተን መጣን ስላሉ ዛሬም ስሟ አሽተን ማርያም ትባላለች፡፡ ይህቺን ቤተ ክርስቲያን በ፩ሺ፪፻፲፩ ዓ.ም አነፃት፡፡

የላሊበላ ልጅ ይትባረክን አሳድጎ መንግሥቱን ለእርሱ አውርሶ በሞት ፊንታ ከነሥጋው ኅዳር ፫ ቀን እንደነ ሄኖክ ተሰውሯል፡፡ ወደፊት በሕይወት ይመጣል የተሰወረውም በተወለደ በ፹ ዓመቱ ነው፡፡ በስሙ ሦስት ቤተ ክርስቲያን ተሠርተዋል፡፡ በዚህ ጻድቅ ገድል ለ፹፭ ቀናት የታሽ በአማላጅነቱ ያመነ ዕድሜው እንደሚረዝም ጌታ ቃል ኪዳን ገብቶላታል፡፡

ረ. <u>አቡነ ተክለ ሃይማኖት /ከ፩ሺ፻፺፯ - ፩ሺ፪፻፺፮ ዓ.ም/</u>


አቡነ ተክለ ሃይማኖት በደብረ ሊባኖስ

የትውልድ ሀገራቸው ቡልጋ ጽላልሽ /ዞረሬ/ ነው፡፡ አባታቸው ጸጋ ዘአብ እናታቸው እግዚእኀረያ ይባላሉ፡፡ ቀዳሚ ስማቸው ፍስሐጽዮን ነው፡፡ መጋቢት ፳፬ ቀን ተጸንሰው ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ተወልደዋል፡፡ አንድ ዓመት ከሦስት ወር ሲሆናቸው በምድረ ሸዋ በጽላልሽ ብርቱ ረሀብ ሆነ፡፡ የሚቀመስ እህል ውኃ ታጣ፡፡ በዚህ ጊዜ እናታቸው የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በየወሩ ታዘክር ነበር፡፡ ያ ሊታጉልብኝ ነው ብላ ታለቅስ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ሕፃኑ ፍስሐ ጽዮን ወደ ቤት

በደብረ ሊባኖስ በዓት ሠርተው፤ አጋንንትን በኃይለ እግዚአብሔር ድል ነስተው፤ አሕዛብን በሃይማኖት ወልደው በምግባር አሳድገው የሚኖሩ ሆነዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በቁመታቸው ልክ ጉድጓድ ቆፍረው ከፊት ከኋላቸው ከግራ ከቀኛቸው ስምንት ጦር ተክለው ሱባኤ ያዙ፡፡ ከቁመት ገድል የተነሣ አንድ እግራቸው ጥር ፳፬ ቀን ፩ሺ፪፻፹ ዓ.ም ተቆርጦ ወድቋል፡፡ ከዚህ በኋላ በአንድ እግራቸው ቆመው ፯ ዓመት ኑረዋል፡፡ ጊዜ እረፍታቸው ሲደርስ ጌታ ቅዱሳንን በመላ አስከትሎ መጥቶ ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ሆይ! ልመናህን ሰምቼ ከድካም ላሳርፍህ መጥቻለሁ፡፡ መንፈሳዊ ደስታም ካለበት አሳርፍሃለሁ፡፡ በተስፋህ ያመነውን! በጸሎትህ የተማፀነውን! ሥጋህ ያረፈበትን! ወዝህ የተንጠፈጠፈበትን ቦታ የተሳለመውን በኪዳንህ ተማፅነው በገድልህ ጸንተው የሚኖሩ ልጆችህን! እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ አበዛልሃለሁ፤ ብሉ ተስፋቸውን ነገራቸው እርጓል አሳቸውም ስትገሽ ቀን ታመው በተወለዱ በ፺፱ ዓመት ከ፲ ወር ከ፲ ቀን ነሐሴ ፳፬ ቀን ፩ሺ፪፻፺፮ ዓ.ም ዐርፈዋል፡፡

ሰ. <u>አቡነ ኤዎስጣቴዎስ (፩ሺ፪፻፸፫ - ፩ሺ፫፻፶፫ ዓ.ም)</u>

አባታቸው ክርስቶስ ሞአ እናታቸው ሥነ ሕይወት ይባላሉ፡፡ በብሥራተ መልአክ ወልደዋቸዋል፡፡ ዘካርያስ ለሚባል መምህር ሰጥተዋቸው ሲማሩና ሲያገለግሉ አደጉ፡፡ ኋላም መዓርገ ምንኩስና ተቀብለው በትጋርምት (በጾም) የሚኖሩ ሆነዋል፡፡ አንድ ቀን የንግሀ ተግባራቸውን አድርሰው በመካነ ተግባራቸው (የሥራ ቦታ) ተቀምጥው ሳሉ ጌታ ተገልጸ ለኢትዮጵያና ለአርማንያ መምህር እንድትሆን መርጬሃለሁና ዙረህ አስተምር፤ አንተን የሰማ እኔን ሰማ፤ አንተን ያልሰማ እኔንም አልሰማም፤ አላቸው፡፡ ከዚያም መዓርገ ቅስና ተቀብለው ማስተማር ጀመሩ አንድ ጊዜም ቅዱሳት መካናትን እጅ ለመንሳት ስድስቱን ቀን እየተጓዙ ሰንበትን እያረፉ ኢየሩሳሌም ደርሰው ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን ወደ አርማንያ ሲሄዱ ባሕረ ኢያሪኮ ደረሱ፡፡ መርከበኛ አግኝተው እንዲያሳፍራቸው ጠይቀውት ትቷቸው ሄደ፡፡ በዚህ ጊዜ የለበሱትን የቆዳ አጽፍ ከባሕሩ ላይ

አንጽፈው ልጆቼ! ጥበበ እግዚአብሔርን እመረምራለሁ ሳትሉና ሳትጠራጠሩ ተሳፈሩ ብለው በዚያ ላይ ተሳፍረው ሲሄዱ ተጠራጥሮ የነበረ አንድ ደቀመዝሙር የመርፌ ቀዳዳ በምታህል ቀዳዳ ሾልኮ ሰጠመ በዚህ ጊዜ ያን ደቀመዝሙር በጸሎታቸው ከሞት አድነውታል፡፡ እሳቸውን ግን ከቀሩት ደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር ቅዱሳን መላእክት በገሪ በቀኝ ሆነው እየቀዘፉ አሻግረዋቸዋል፡፡ ወደ አርማንያም ሀገር ደርሰው አሕዛብን አስተምረው ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ፤ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር መልሰዋል፡፡ ብዙ ገቢረ ተአምራትና ገድላትን ፈጽመው መስከረም ፲፰ ቀን ዐርፈዋል፡፡ መቃብራቸውም በገዳመ መርምህናም ይገኛል፡፡

ሸ. <u>አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ /በ፩ሺ፫፻፶፯ ዓ.ም/</u>

የተወለደው በወሎ ክፍለ ሀገር በረና ወረዳ ሸግላ የምትባል መንደር ነው፡፡ በ፩ሺ፫፻፶፯ ዓ.ም አባቱ ሕዝበ ጽዮን በቤተመንግሥት አካባቢ ያገለግሉ ከነበሩት ካህናት ወገን ሲሆን እናቱ እምኃ ጽዮን ደግሞ በደግነቷ የታወቀች ሴት ነበረች፡፡

አባ ጊዮርጊስ ለወላጆቹ አንድ ብቸኛ ልጅ ነበር፡፡ በተወለደ በሰባት ዓመቱ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያን ይማር ዘንድ በዚያ ዘመን በመምህራንና በመጻሕፍት ወደ በለጸገው ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ት/ቤት አስገቡት፡፡ ነገር ግን ለሰባት ዓመታት ያህል ትምህርት ቀርቶ ፊደል ሊገባው አልቻለም፡፡ በዚህም የተነሣ መምህሩ አባ ሠረቀ ብርሃን ያዝኑ ነበር፡፡ አባ ጊዮርጊስ ትምህርት አልገባው ስላለ መነኮሳቱን እህል በመፍጨት ያገለግል ነበር፡፡ የፈጨበት ወፍጮ ዛሬ ድረስ በሐይቅ ገዳም ይገኛል፡፡

ለብዙ ዘመናት ያዝን የነበረው አባ ጊዮርጊስ አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብና በቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ፊት ተንበርክኮ አለቀሰ፡፡ እመቤታችንም ዕንባውን ተቀብላ ቅዱስ ዑራኤልን ወደ እርሱ ዘንድ ላከችለት፡፡ ጽዋዐ ልቡናም አጠጣው፡፡ በዚህም የተነሣ ያን ያጣውን ትምህርት በጥቂት ጊዜ ውስጥ ይዋኝበት ጀመር፡፡

አባ ጊዮርጊስ የእመቤታችን ፍቅሯ ያደረበት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። በዚህም የተነሣ መጽሐፈ አርጋኖን፣ እንዚራ ስብሐት፣ ሕይወተ ማርያም፣ መዓዛ ቅዳሴ የተባሉና ሌሎችም ድርሰቶች ጽፎላታል። አባ ጊዮርጊስ የያሬድን ትምህርት በጥልቀት ከሚያውቁት ሊቃውንት አንዱ ነው። ስለዚህም አጼ ዳዊት ደብረ ነጐድጓድ የድጓ ማስመስከሪያ ሲያደርግ አባ ጊዮርጊስን መራሒ አድርጐ ሾሞት ነበር። ለዚህም ነው ከያሬድ ጀምሮ በሚወርደው የድጓ መምህራን ሐረግ ውስጥ ስሙ የሚጠቀሰው።

አባ ጊዮርጊስ ታላቅ የቅኔ ሰው ነበር። አብዛኛዎቹ መጻሕፍቱ የተጻፉት በግጥም መልክ ነው። የአባ ጊዮርጊስን የቅኔ ጥበብ ለማየት መጽሐፈ ሰዓታትን መመልከት ብቻ ይበቃል። በዚያ ዘመን አባ ኢየሱስ ሞዓ ካቋቋሙት የሐይቅ ቤተ መጻሕፍትና ከሊቃውንት አበው ያገኘው ጥልቅ የሃይማኖት እውቀት እንደነበረው ባለ ፴ ምዕራፍ መጽሐፈ ምሥጢር ምስክር ነው። የሥነ ፍጥረትን፣ የነገረ መለኮትን፣ የመጻሕፍትን ታሪክና የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ብሉም የነገረ ማርያም እውቀቱን አጉልቶ ይመሰክርለታል።

አባ ጊዮርጊስ የቤተ ክርስቲያን አፈ ጉባኤ ነበር። በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የነበሩት ጳጳስ አቡነ በርተሎሜዎስ "ሥላሴ አንድ ገጽ ናቸው።" ይላሉ እየተባለ ይናፈስ የነበረውን ወሬ ለማጣራት ከተላኩት ሊቃውንት አንዱ አባ ጊዮርጊስ ነበር። በኋላም ነገሩ ውሸት መሆኑን አረጋግጦ ተመልሷል።

የትምህርቱ ጥልቀትና ስፋት የነገሥታቱን ልቡና ሳይቀር መስጧቸው ነበር። አፄ ዳዊት ስምንቱን ልጆቹን /ቴዎድሮስ፣ ይስሐቅ፣ ቴዎፍሎስ፣ እንድርያስ፣ ሀብተ ኢየሱስ፣ ሕዝቅያስ፣ ኢዮስያስ፣ ዘርዓ ያዕቆብና ዕሌኒ/ የተባሉትን ያስተምርለት ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥት አስጠራው። አባ ጊዮርጊስም ልጆቹን ሁሉ በዕውቀትና በምግባረ ሠናይ ቀርጿቸው እንደነበር ታሪኩ ያስረዳል። ከሁሉም ደግሞ የመጀመሪያው ቴዎድሮስና የመጨረሻው ዘርዓ ያዕቆብ ታላቅ ቦታ አላቸው። ንጉሥ ቴዎድሮስ በሕይወት ዘመኑ ወደ ዋልድባ ሲመጣ መነኮሳቱ ከሥራ ብዛት የተነሣ በቀን ሰባት ጊዜ ብቻ ይጸልዩ ነበርና አባ ጊዮርጊስ የልቡ ሊደርስለት ስላልቻለ እንደገሠጻቸው ታሪኩ ያወሳል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ፳፬ ሰዓት የሚፈጅ የምሥጋና መጽሐፍ ሰዓታትን ያዘጋጀው።

ከድርሰቱ ጋር የማስተማር ሥራን አጣምሮ ያካሂድ ነበር። በተለይም የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በተመለከተ ጉባኤ ሲደረግ የእርሱ መኖር አስፈላጊ ነበር። በዚያ ዘመን በሸዋ በተለይም በእንኮበር አካባቢ በኦሪት የሚያምኑና ራሳቸውን ቤተ እስራኤል ብለው የሚጠሩ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ ከክርስቲያኖች ጋር በሃይማኖት ይከራከሩ ነበር። አንድ ጊዜ በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግሥት የኦሪታውያኑ ምሁር ከክርስቲያኖች ጋር ለመከራከር ጉባኤ ጠራ። አጼ ዳዊትም ካህናቱ ሁሉ እንዲሰበሰቡ ዐወጀ። አንድ ትልቅ አባት ግን በሕመም ምክንያት አልጋ ላይ ስለ ዋሉ አልተገኙም ነበር። እርሱም አባ ጊዮርጊስ ነው።



አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ [illegible]

ካህናቱ አባ ጊዮርጊስ የሌለበት ጉባኤ ጨው የሌለው ወጥ መሆኑን ስለተረዱ እንዲጠራ ንጉሡን ተማፀኑ። ንጉሡም አባ ጊዮርጊስን ከነአልጋው በቃሬዛ አስመጣው። በአልጋ ተኝቶ ሕመሙን እየቻለ ኦሪታውያኑን ተከራክሮ መርታቱን ገድሉ ይተርክልናል።

በአንዲት ሴት ጸንቶ ሃይማኖቱን በሚገባ በመጠበቁ ቤተ ክርስቲያን የቅድስና መዓርግ ሰጥታ ሰኔ ፳፱ ቀን በዓሉን ታከብራለች።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ደግሞ በሥነ ጽሑፍ ረገድ መምህሩን የተከተለና መልክአ ማርያም፣ መጽሐፈ ባሕርይ፣ ክህደተ ሰይጣን፣ መጽሐፈ ምዕላድ፣ እግዚአብሔር ነግሠ እና መጽሐፈ ስብሐት የተሰኙ መጻሕፍትን ለቤተ ክርስቲያን አበርክቶላታል።

አባ ጊዮርጊስ በአጼ ዳዊት ቤተ መንግሥት እያለ አልመነኮሰም ነበር። ንጉሡ በትምህርቱ አባ ጊዮርጊስን ስለወደደው ሴት ልጁን አግብቶ ተሹሞ እንዲኖር ጠይቆት ነበር። አባ ጊዮርጊስ ግን ምንኩስናን ስለመረጠ ጋብቻውንም ሆነ ሹመቱን ሳይቀበለው ቀረ።

በመምህርነት እያለ ወደ አቡነ በርተሎሜዎስ ዘንድ በመሄድ ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጽሞለት ቅስናን ተቀበለ። ከምንኩስናውም በኋላ የአባ ጊዮርጊስ ሊቅነትና መምህርነት በመላ ኢትዮጵያ መሰማት ጀመረ። ከሁሉ ያስወደደው ደግሞ ለእግዚአብሔር ቤትና ለሥርዓቱ ቀናዒ መሆኑ ነው። በጥንት ዘመን ንግሥቲቱ ሥጋውንና ደሙን የምትቀበለው ከመቀመጫዋ ሳትነሣ ካህናቱ ወደርሷ ሄደው ነበር። አባ ጊዮርጊስ ይህንን በመቃወም የአጼ ዳዊት ሚስት ተነሥታ እንድትቀበል አድርጓታል። በዚህ ሥራው ክብሯ የተነካባት የመሰላት ንግሥት ዕድሜ ልኳን ጠልታው እንደኖረች ይነገራል። አጼ ዳዊት በሁለቱ መሐል ያለውን ጥል ለመፍታት የገብረ ዕድነት መዓርግ ሰጥቶት በዳሞት /ጎጃም/ ወንጌልን እንዲሰብክ ልኮታል። በዚያውም ወደ ዋልድባ በመጓዝ ከአቡነ ሳሙኤል ጋር ተገናኝቷል።

አባ ጊዮርጊስ አመስጋኝ በቃኝ የማይል አባት ነበር። ሲቀመጥ፣ ሲነሣ፣ ሲጓዝ ከማመስገን አንደበቱ አያርፍም። እንዲያውም አንድ ጊዜ ለመጸዳዳት ተቀምጦ እመቤታችንን ሲያመሰግን እመቤታችን ተገልጣ "አባ ጊዮርጊስ እዚህም ታመሰግነኛለህን?" ብትለው ምንስ ይህን ነገር ብትከለክይልኝ ሲል ለመናት። ከዚያ በኋላ አባ ጊዮርጊስ መጸዳዳት የሚባል ነገር እንደቀረለት ይነገራል።

ከዚህ በኋላ ነገረ ሠሪዎች አላስቀምጠው ስላሉ ወደ ደብረ ሊባኖስ ተጉዞ የአቡነ ተክለሃይማኖትን ዐፅም ተሳልሞ ወደዳሞት አመራ። እርሱ ከነገር ቢሸሽም ነገር ተከትሎት ካለበት ድረስ መጣ። በቤተ መንግሥት ዙሪያ ያለ ዕውቀት ጠምጥመው ያለ ጥበብ ከብረው የሚኖሩ ሸውከኞች /ነገር አመላላሾች/ በአጼ ዳዊት እግር ከተተካው ተማሪው ከነበረው ከቴዎድሮስ ጋር አጣሉት ። በዚህም የተነሣ ወደ በረሃ ተግዞ ንጉሡ እስኪሞት በዚያ ቆይቷል።

የአባ ጊዮርጊስ ተማሪ አጼ ይስሐቅ በነገሠ ጊዜ ስበን በሚባል ሥፍራ ጉልት (ርስት) ሰጥቶ አባ ጊዮርጊስን ከግዞት አወጣው። ነገር ግን ስደትና ችግር አድክሞት ነበርና በተወለደ በ፷ ዓመቱ ፲፬፻፲፯ ዓ.ም ሰኔ ፯ ቀን በዕለተ እሑድ ዐረፈ። አፅሙም በጋሥጫ ገዳም /ደቡብ ወሎ/ በክብር ዐረፈ።

አጼ ይስሐቅም "ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ፣ ዓምደ ሃይማኖት" ሲል ሰየመው። ቤተ ክርስቲያናችን የቅድስናን መዓርግ ሰጥታ ሰኔ ሰባት ቀን በዓሉን ታከብራለች። በተለይም ዐፅሙ ባረፈበት በጋሥጫ በታላቅ ድምቀት ይከበራል። በሕይወት ዘመኑ ከ፵ በላይ መጻሕፍት የደረሰ ሲሆን ጥቂቶቹም የሚከተሉት ናቸው።

፩. መጽሐፈ አርጋኖን
፪. መጽሐፈ ምሥጢር
፫. መጽሐፈ ሰዓታት
፬. እንዚራ ስብሐት
፭. ሕይወተ ማርያም
፮. ውዳሴ መስቀል
፯. ተአምኖ ቅዱሳን
፰. ክብረ ቅዱሳን
፱. ጸሎት ዘቤት
፲. መዓዛ ቅዳሴ
፲፩. ኆኅተ ብርሃን
፲፪. ፍካሬ ሐዋርያት
፲፫. ውዳሴ ሐዋርያት
፲፬. ውዳሴ ስብሐት

ከነዚህ መካከል ብዙዎቹ መጻሕፍት በጣልያንኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በጀርመንኛ ተተርጉመዋል። በአማርኛ የሚገኙት ግን ሦስት ብቻ ናቸው። አባ ጊዮርጊስ በሃይማኖቱ የጸና፣ በምግባሩ የቀና፣ የነገሥታትን ፊት አይቶ የማያዳላ፣ ከማስተማርና ከመጻፍ ያልቦዘነ አመስጋኝ የማይጠግብ የእመቤታችን ፍቅር የበዛለት ታላቅ አባት ነው።

ከዓለማዊ ምኞትና ሀብት ይልቅ የምንኩስናን ኑሮ የመረጠ፣ በደዌ ተይዞ እንኳን ስለሃይማኖቱ ከመመስከር ወደኋላ ያላለ የሃይማኖት ብርሃን ነው። ከርሱ የምንማረው ብዙ ነገር አለ። ያመነውን መመስከር፣ ያወቀውን መጻፍ፣ ዕውቀትን በብልጠት ሳይሆን ከእግዚአብሔር በጸሎት ማግኘት፣ ተግቶ መማርና ዝቅ ብሎ ማገልገል ደቀመዛሙሩን በምግባር በሃይማኖት ርቱዕ (ቀጥተኛ) አድርጐ ማውጣት ጥቂቶቹ ናቸው።

አባ ጊዮርጊስ አመነ፣ አስተማረ፣ ጻፈ፣ ተንገላታ፣ መከራን ተቀበለ፣ በእውነት ስለእውነት ሥጋዊ ምኞት ሳያሸንፈው ዓለማዊ ኑሮ ሳይማርከው በሃይማኖት ለሃይማኖት በተጋድሎ ኖረ።

ቀ. ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ

ሀገርዋ ቡልጋ ቅዱስጌ ነው። አባቷ ደርግኤ እናቷ እሌኒ ይባላሉ። እካለ መጠን ስትደርስ ሠምረ ጊዮርጊስ ለሚባል ደግ ካህን ዳሯት። አሥራ ሁለት ልጆች ወልዳለታለች። ንጉሡ አጼ ገብረ መስቀል የልጇን ትንንት የምግባሯን ደግነት ሰምተው የምትለብሰው የምታጥፈው አልባስ ወርቅ ወጥተው ወርደው የሚያገለግሏት መቶ ሰባ አራት አገልጋዮች ሠደውላታል። ከነኛ እንዲቷ አንድ ቀን ከእሳት ዳር



[illegible]

ተቀምጣ እንቿ እጣውን እየቀባጠረች ብታስጨንቃት ፍሕሙን በእጇ ዘግና ከአፍዋ ጣለችባት። በዚህ ጊዜ አገልጋይዋ ተቃጥላ ሞታለች። ክርስቶስ ሠምራም ሕንፃ እግዚአብሔር አፍርሼ ከጌታዬ ተጣልቼ የምሸልክበት ቀዳዳ የምርጥበት ሜዳ አጥቼ ብላ በማልቀስ ይህችን ብላቴና ብታስነሳልኝ ከዓለም ተለይቼ ገዳም ገብቼ አገለግልሃለሁ ብላ ቃል ገብታ ተነሣች። ከዚህ በኋላ ልብስ ምንኩስና አዘጋጅታ ስትሔድ ሕፃን ልጇን ይዛ ኖር ልጁ ከዚህ አይገባም ቢሏት ከበር ትታው ገብታለች። ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ሄሮድስ ካስፈጃቸው ፲፬ እልፍ ሕፃናት ደምሮታል። እሷንም በከንፉ ተሸክሞ ከጣና ሐይቅ አድርሷታል። በዚያም ከመከራዋ ብዛት ከገድሏ ጽናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የዓሣ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባሕሩ ገብታ ወደገራና ቀኝ ሳትል አሥራሁለት ዓመት ጸልያለች። በመጨረሻ ጌታ ምን አደርግልሽ ዘንድ ትሻለሽ አላት እሷም ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለምና ውሉደ አዳም እንዳይጠፉ ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው። ከሆነልሽ ጠርተሽ አምጪው አላት ቅዱስ ሚካኤል ወስዶ ከጽንፈ ሲዖል አደረሳት። ዲያብሎስን ና ውጣ አለችው። በምድር ፈልጌ ባጣሽ ሳዝን እኖር ነበር። አሁንማ ከቤቴ መጣሽልኝ ብሎ ጉትቶ አስገባት። ቅዱስ ሚካኤል ተከትሎ ገብቶ በከንፉ ነጥቆ አውጥቷታል። ስትወጣም ስለገድልዋ ጽናት ስድስት ክንፍ ተሰጥቷት በዚያ ነፍሳትን ማርካ ወጥታለች። ከዚህ በኋላ ዜና ገድሏ ስንጽድቁ በየአህጉሩ ተሰምቶ ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ያላነሱ ደናግል ተሰብስበውላት ጽሙና ብሕትውና የምታስተምራቸው ሁናለች። በፍጻሜ ዘመኗ በቁመቷ ልክ በዓት ሠርታ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ ዐሥራ ሁለት ጦር ተክላ ወዲያ ወዲህ ሳትል ቆማ ዐሥራ ሁለት ዓመት ኖራለች። ስትሰግድም ሥጋዋ በጦሩ ተወግቶና ተፈትቶ አልቋል። ጌታም ይህን ሁሉ መከራዋን እንደመሥዋዕት ቆጥሮላት በቃል ኪዳኗ የተማፀነውን ስሟን የጠራውን እስከ አሥር ትውልድ እንዲምርላት ተስፋዋን ነግሯት ክብርት ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ በቃለ እቅርንት በዝማሬ መላእክት አሳርጓታል። የዕረፍቷም መታሰቢያ ነሐሴ ሃያ አራት ይከበራል።

* [illegible]

ቢ. አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ /ከ፱ - ፲፬ መቶ ክፍለ ዘመን/

ሀገራቸው ንሒሳ /ግብፅ/ ነው። አባታቸው ስምዖን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ። ልጅ ሳይወልዱ ሠላሳ ዓመት ሲያዝኑ ኑረዋል። አንድ ጊዜ አቅሌስያ ከቤተ ክርስቲያን ሄዳ ከሥዕለ ሥላሴ ሥር ወድቃ ስትማፀን ክብሩ ከሁሉ የሚበልጥ ልጅ እንኪ ተቀበይ የሚል ድምፅ ሰማች። በዚህም መሠረት አባታችን መጋቢት ሃያ ዘጠኝ ቀን ተፀንሰው ታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ቀን ተወለዱ። በተወለዱ ጊዜ አፈፍ ብለው ተነሥተው ለአብ ምስጋና ይሁን፣ ለወልድ ምስጋና ይሁን፣ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይሁን፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ለአወጣኸኝ ብለው አመሰገንዋል።



[illegible]

ሦስት ዓመት ሲሆናቸው ቅዱስ ገብርኤል በገነት ካሉ ቅዱሳን አበው ገዳማውያን ካሉበት ቦታ ወስዶ ከበሩ አኖራቸው። አበምኔቱ አባ ዘመደ ብርሃን ምልክት ተነግሮት ቢሄድ ፊታቸው ደስ የሚል ሆኖ አግኝቷቸዋል። አሳድጐና አስተምሮ ከመዓርገ ምንኩስና አድርሷቸዋል። ሀብተ ፈውስም ተሰጥቷቸው ስለነበር ብዙ ሰዎች ዝናቸውን ሰምተው እየመጡ ጉብር የሚያስፈቷቸው ቢሆን ቅዱስ ገብርኤል በከንፉ ነጥቆ ከጌታ ፊት አቅርቧቸዋል። ጌታም ከሰው ተለይተህ ወደ ሜላ ግባ፤ ኑሮህም ከአናብስት ከአናምርት ጋር ይሁን። ምግባቸውም የረገጥከውን ትቢያ መላስ ይሁን ብሏቸው ተሠወረ። በዚሁ መልኩ በገዳም ተወስነው ሠላሳ ዓመት ከቆዩ በኋላ ጌታ በአንድነት በሦስትነት ተገልጾ ምን ላድርግልህ ትሻለህ? አላቸው።

መጀመሪያ ያለሁበትን የምድረ ገቦታን ሰዎችን ማርልኝ አሉት ሦስት ሺህ ኃጥአን ከሲኦል አውጥቶ ገነት አግብቶላቸዋል። ከዚህ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሑድ ብሏቸው በደመና ሠረገላ ምድረ ከብድ ደርሰው ዳግመኛ ደብረ ዝቋላ ሄደው በንጽሐ ልቡና የኢትዮጵያን ሕዝብ ኃጢአት አይተው ከባሕሩ በራሳቸው ቆመው ይጸልዩ ጀመር። ዐርባ ቀን ሲሆናቸው መልአኩ መጥቶ መታሰቢያህን ያደረገ፣ ስምህን የጠራ እምርልሃለሁ ብሎሃል አላቸው በዚያም መቶ ዓመት ጸልየው መላ ኢትዮጵያን ምሬልሃለሁ ብሏቸው ወጥተዋል። ይህም የቃል ኪዳናቸው በዓል ጥቅምት አምስት ቀን ይከበራል። ከዚህ በኋላ ምድረ ከብድ ወርደው ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ሆነው ሰባት ዓመት እንደ ትክል አምድ (ቋሚ ምሰሶ) ሆነው ጸልየዋል። ሰይጣን ለምቀኝነት አያርፍምና ቁራ መስሎ መጥቶ ዓይናቸውን አንቁሮ አሳወራቸው። ነገር ግን ሁለት ሱባዔ ሲፈጽሙ መላእክት አፍ ብለው አድነዋቸዋል። አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አባ አንበስ ዘሐዘሐሎ፣ አባ ብንያም ዘጉባዔ ሊጠይቋቸው መጥተው በሰባተኛው ቀን ተገለጹላቸው። አናብስቶቻቸው በእርሳቸው አናብስት ተውጠው አገኘው ነበርና ትፉ ጌታ ያዘዛችሁ የእግሬን ትቢያ ነው እንጂ ሥጋና ደም ነውን? ብለው የአናብስቱን ትፋታቸውን ቢባርኩት አገበሶቻቸው ተነሥተውላቸዋል። ከዚህ በኋላ አባታችንን ወደ ምዕራብ ሀገር ወሰዷቸው፣ የዐረብ ንጉሥ በጣዖታቱ ያደሩ አጋንንት ፈርተው ሲሸሹ ጣዖታቱ ሲሰባበሩ አይቶ በሰይፍ ሊመታቸው ሲቃጣ መብረቅ ወርዶ ከነተከታዮቹ ፈጅቷቸዋል። ወዲያውም መላእክተ ጽልመት ነፍሶቻቸውን እጅ ሲያደርጉ አይተው ይህ ሁሉ በኔ ምክንያት አይደለምን ብለው እግራቸውን በገመድ አሥረው በታላቅ ገደል ቁልቁል ተሰቀሉ ሰይጣንም ገመዱን በጠሰው። ቅዱስ ሚካኤል ተቀብሏቸው ተወኝ በራሴ ልቁም አሉት በጥርሳቸው ድንጋይ ነክሰው ሠላሳ ዘመን አልቅሰዋል ጌታ ምሬልሃለሁ ብሏቸው ጥርሶቻቸው በድንጋዩ ላይ ተተክለው ቀርተዋል። በዚያም መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የሽቱ እንጨት፣ ደማቸው ከነጠበበትም ወይን በቅሎበት ተገኝቷል። ይህን በመሰለ ዕፁብ ድንቅ ሥራ በሀገራቸው ሦስት መቶ ዓመት

በኢትዮጵያ ሁለት መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት ኖረው በእምስት መቶ ስድሳ ሁለት ዓመታቸው መጋቢት ፭ ቀን በእለተ እሑድ ዐርፈዋል። መላእክት በአክናፈ እሳት (የእሳት ክንፍ) ገነት ወስደው በመሰዊያው በስተቀኝ ቀብረዋቸዋል። ወደ ኢትዮጵያም የመጡት በቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል።

፫.፫. ከአሕመድ ግራኝ እስካሁን

ሀ. ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ

አባትዋ ባሕር አሰግድ እናትዋ ደግሞ ክርስቶስ ዕበያ ይባላሉ። ትውልድዋ ከዳዋር /ምሥራቅ ኢትዮጵያ/ ወገን ነው፡ ወንድሞቿ ዮሐንስና ዘድንግል በንጉሥ ሱስንዮስ ዘንድ ታላላቅ ባለሥልጣናት ነበሩ።

እናትና አባትዋ በሕግ በሥርዓት ካሳደጉዋት በኋላ ለአንድ ትልቅ መኰንን ዳርዋት። ነገር ግን አጼ ያዕቆብ /፩ሺ፭፻፺፰ - ፩ሺ፭፻፺፱/ ባልዋን በግፍ ስለገደሉባት ሥዕለ ክርስቶስ የተባለ የሱስንዮስ የጦር አበጋዝ ቢትወደድ አግብታ ፫ ልጆች መውለድዋን ገድሏ ይናገራል። ፩፻፰፫ +፲፫። ይህ ቢትወደድ ይኖርበት የነበረው ግንብ ቤት ፍራሽ እስከ አሁን ድረስ በጋይንት ስማዳ ይታያል።

ወለተ ጴጥሮስ ከቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ጋር በሰላም በመኖር ላይ እያለች በመካከላቸው የማይታረቅ ቅራኔ ተፈጠረ። ንጉሡ አጼ ሱስንዮስ የተዋሕዶ ሃይማኖቱን ቀይር በሮማውያን በመታለል ካቶሊክነትን ተቀብሉ ዐወጀ። በዚህ ዐዋጅ የተነሣ በንጉሡ ደጋፊዎችና የቀደመ ሃይማኖታችንን አንለቅም ባሉት መካከል ታላቅ ጠብ ሆነ። የንጉሡ ሠራዊትም በተዋሕዶ ምእመናን ላይ ዘመቱ።

ቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ከዘመቻ ሲመለስ የጳጳሱን የአቡነ ስምዖንን ልብስ እንደግዳይ ሰልባ ለንጉሥ" ይዞለት መጣ። የሃይማኖትዋን መናኛ፣ የአባቶቿን መደፈር የተመለከተችው ወለተ ጴጥሮስ እንደዚህ ካለው ከሃዲ ጋር በአንድ ቤት መኖር አያስፈልግም ብላ ቆረጠች። ከቤቱ የምትወጣበትን መንገድ በድብቅ ከጣና መነኮሳት ጋር

በዚያም በገዳሙ የነበሩ መነኮሳትንና የአካባቢው ምእመናን ስለ ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው እያስተማረች በእምነታቸው እንዲጸኑ እየመከረች ጥቂት እንደቆየች የሚያሳጧትና የሚከሷት ስለበዙ ቦታውን ለቃ ወደ ዋልድባ ገባች። ዋልድባ ገብታ ሱባዔዋን ከፈጸመች በኋላ በገዳሙ የነበሩ አባቶችንና እናቶችን በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆዩ ትመክራቸው ጀመር።

አጼ ሱስንዮስ የወለተ ጴጥሮስ ተጋድሎ መነኮሳትንና ምእመናንን በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ፣ ከከሀደታቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ሲረዳ ብዙ ተከታዩቹን ይልክባት ነበር። በዋልድባ እያለችም የንጉሡ ሠራዊት ሲያስኖሯት ስላልቻሉ ወደ ጸለምት አመራች።

በጸለምት የወለተ ጴጥሮስ ትምህርት እንደ ችቦ እሳት ተስፋፋ። ምእመናን እየወደዷትና እየተቀበሏት ራሳቸውን ለሰማዕትነት አዘጋጁ። ይህንን የሰማው ሱስንዮስ ይህች ሴት እኔ ብተዋት እርስዋ አልተወችኝም፣ እኔ ብምራት እርስዋ ይቅር አላለችኝም፣ አለና የጸለምቱን ገዥ ባላምባራስ ፊላታዎስን ወለተ ጴጥሮስን እንዲያመጣለት አዘዘው።

ወለተ ጴጥሮስ በጸለምቱ ገዥ ተይዛ ወደ ሱስንዮስ መጣች። አስቀድመው ሃይማኖቷን እንድትለውጥ ሊያግባቡዋት ሞከሩ። እርስዋ ግን ጸናች። ሦስት የካቶሊክ ቀሳውስት መጥተው ስለሃይማኖትዋ ተከራከርዋት። ወለተ ጴጥሮስ ግን የሚገባቸውን መልስ ሰጥታ አሳፈረቻቸው። በየቀኑ የካቶሊክ ቀሳውስት ሃይማኖትዋን ትታ ካቶሊክ እንድትሆን በምክርም በትምህርትም ሞከሩ። ይሁን እንጂ ወለተ ጴጥሮስ በዓለት ተዋሕዶ ላይ ተመሥርታ ነበርና ፍንክች አላለችም።

በመጨረሻ አንዱ የካቶሊክ ቄስ 'እርስዋን አቀይራለሁ ማለት በድንጋይ ላይ ውኃ ማፍሰስ ነው' ሲል ለንጉሡ አመለከተ። ሱስንዮስ ይህንን ሲሰማ ሊገላት ቆረጠ። አማካሪዎቹ ግን 'አሁን እርስዋን ብትገል ሰው ሁሉ በሞትዋ ይተባበራል። ደግሞ ሰው ሁሉ ካለቀ በማን ላይ ትነግሣለህ። ይልቅስ ታሥራ ትቀመጥ' ብለው መከሩት። ንጉሡም ገርበል ወደተባለው በረሃ ሊልካት ወሰነ።

መልክአ ክርስቶስ የተባለው ዋነኛ የካቶሊኮች አቀንቃኝ ወደ ሱስንዮስ ፊት ቀርቦ "ንጉሥ ሆይ በፊትህ ሞገስን ካገኘሁ ከረምቱ እስኪያልፍ ድረስ እኔ ዘንድ ትከረም። እኔ እመክራታለሁ። የፈረንጆቹ መምህር አልፎንሱም ሁል ቀን መጽሐፉን ያስማታል። ይህ ሁሉ ተደርጐ አሻፈረኝ ካለች ያን ጊዜ ግዞት ላካት" ሲል ለመነው ንጉሡም ተስማማ።

መልክአ ክርስቶስ ወለተ ጴጥሮስን የካቶሊኮች ጳጳስ ከሚኖሩበት ጉንደር አዘዞ ወሰዳት። ሁለቱ ተከታዮቿ ወለተ ክርስቶስና እኅተ ክርስቶስ አብረዋት ስነበቱ። ወለተ ጳውሎስ ዘኋላ ቀርታለች፤ አልፎንሱ ሜንዴዝም ዘወትር እየሄደ የልዮንን ክህደት ያስተምራት ነበር። ንጉሡም ወለተ ጴጥሮስን ወደ ካቶሊክነት መቀየር በየጊዜው ይጠይቃል፤ የሚያገኘው መልስ ግን ሁልጊዜ አንድ ነው 'በፍጹም'። ክረምቱ አለፈ። ኅዳርም ታጠነ። ወለተ ጴጥሮስ በትምህርትም በማ-ባበልም ከተዋሕዶ ሃይማኖትዋ ንቅንቅ አልል አለች፡ ስለዚህ ወደ ስደት ቦታዋ ገርበል በረሃ በሱስንዮስ ወታደሮች ተጋዘች። ወለተ ጴጥሮስ ብቻዋን ገርበል ወረደች። በእርጅና ላይ ያለችው እናቷ ይህንን ነገር ስትሰማ እንዲት አገልጋይ ላከችላት። ቆራጧ ተከታይዋ እኅተ ክርስቶስም ወዲያው ወደርስዋ መጣች።

ገርበል በረሃ ሰ፫ ዓመት ስትኖር ብዙ ጊዜ ትታመም ነበር። ነገር ግን መከራውን ሁሉ ስለሃይማኖቷ ቻለችው። ከ፫ ዓመት በኋላ ዮሐንስ የተባለው ወንድሟ ከንጉሡ ልጅ ከፋሲለደስ ዘንድ ቀርቦ እኅቱ ትፈታ ዘንድ ለንጉሡ እንዲማልደው ነገረው። ካልሆነ ግን በመካከላቸው ታላቅ ቅያሜ እንደሚነሣ አሳሰበው። በፋሲል አማላጅነት ሱስንዮስ መፈታትዋን ፈቀደ። ከተፈታች በኋላ ደንቢያ ውስጥ ጫንቃ በተባለ ቦታ ተቀመጠች። በስደቱ ምክንያት ቆባቸውን አውልቀው የነበሩት እያሉ መነኩሳትም ስደቱ መለሰ ሲል በዙሪያዋ ተሰበሰቡ። በኋላም ወደ ጣና ቂርቆስ ተጉዛ በአንድ መነኩሴ ቤት መኖር ጀመረች።

በዚያ መኖርዋ ለወለተ ጴጥሮስ ደስ አላሰኛትም። ስለዚህም ከንጉሡ አስፈቅዳ ምጽሊ ወደተባለው ደሴት ተጓዘች። በዙሪያዋ እያሉ

መሳሳክ ጀመረች። የጣና ቂርቆስ ገዳም አበምኔት አባ ፊትለ ሥላሴም ወለተ ጴጥሮስን ይዘዋት እንዲመጡ ሁለት መነኮሳትን ላኩ። /በዚያ ጊዜ ልጆቿ ሁሉ ሞተውባት ነበር።/ ወለተ ጴጥሮስ ከመነኮሳቱ ጋር መጥፋቷን ያወቀው ቢትወደድ ሥዕለ ክርስቶስ ይዘው ያመጡለት ዘንድ እያሌ ሠራዊትን ከኋላዋ ሰደደ። ነገር ግን ወለተ ጴጥሮስና ሁለቱ መነኩሳት እልም ባለ ዱር ውስጥ ተደብቀው ስለነበር ሊያገኙዋቸው አልቻሉም። ይህ ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ 'ሳጋ ወለተ ጴጥሮስ' ይባላል። በኋላ ዘመንም በስሟ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል።

ከዚህ በኋላ ወደ ደብረ ዕንቁ ገዳም ገባችና ምንኩስናን ተቀበለች። ታላቁ ገድሏ የተጀመረውም ከዚህ በኋላ ነው። ወለተ ጴጥሮስ ከምንኩስናዋ በኋላ በመላ ሀገሪቱ እየተዘዋወረች ሕዝቡ በተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲፀና፣ በቅዛሊም ጊዜ ሃይማኖቱን የለወጠው የንጉሡ የሱስንዮስ ስም እንዳይጠራ ታስተምር ጀመር። ብዙ ሰዎችም በትምህርቱ ተስበው በሃይማኖታቸው እየጸኑ ሰማዕትነትን መቀበል ያዙ።

ይህንን የወለተ ጴጥሮስን ተጋድሎ የሰማው ንጉሡ ሱስንዮስ ተይዛ በፊቱ ለፍርድ ትቀርብ ዘንድ ብዙ ወታደሮችን በየአካባቢው አሰማራ። በመጨረሻም በሠራዊቱ ተይዛ በሱስንዮስ ፊት ቀረበች። መሳፍንቱ መኳንንቱና ሰእንጀራቸው ሲሉ ሃይማኖታቸውን የለወጡ ሊቃውንት በተሰበሰቡበት ትመረመር ጀመር።

ከሳሽዋ "ንጉሡን ካድሽ፣ እግዚአብሔርን ካድሽ፣ ትእዛዙን እምቢ አልሽ፣ ሃይማኖቱን ዘለፍሽ፣ ሌሎች ሰዎችም ሃይማኖቱን እንዳይቀበሉ ልባቸውን አሸከርሽ ሲል ከሰሳት። ወለተ ጴጥሮስ ግን እንደፈጣሪዋ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በከሳሾቿ ፊት ዝም አለች። ንጉሡም ርቃ እንዳትሄድ ነገር ግን ከቅርብ ዘመዶቿ ጋር ብቻ እንድ ትኖር /የቁም እሥር/ ፈረደባት።

ሃይማኖት ተንቃ፣ ቤተ ክርስቲያን ተዋርዳ የመናፍቃን መጫወቻ ስትሆን በማየት የሃይማኖት ፍቅርዋ ያላስቻላት ወለተ ጴጥሮስ በግዞት መልክ ከተቀመጠችበት ቦታ ጠፍታ ዘጌ ገዳም ገባች። አብረዋትም ወለተ ጳውሎስና እኅተ ክርስቶስ የተባሉ እናቶች ነበሩ።

መነኮሳት ተሰበሰቡ። ነገር ግን መከራ ያልተለያት ወለተ ጴጥሮስ መዝራዕተ ክርስቶስ የተባለው ሰው ካቶሊክ ያልሆኑ ምእመናንን አስገድዶ የሚያስጠምቅበት ደብዳቤ ይዞ ወደ አካባቢው መምጣቱን ስለሰማች መነኮሳቱን መከራና አስተምራ ወደየበረሃው ከበተነች በኋላ እርሷም እንደገና ስደት ጀመረች። ተመልሳ ወደ ምጽሊ የመጣችው አገር ሲረጋጋ በ፵፬ ዓመትዋ ነው።

ከስደት ስትመለስ መኖሪያዋ ያደረገችው መዝዞ የተባለው ቦታ ነው። በዚያ ቦታ ላይ በጸሎትና በስግደት ተጠምዳ ኖረች። በምጽሊ ገዳም አበሯት የነበረው የደብረ ማርያም አበምኔት አባ ጸጋ ክርስቶስም መጽሐፈ ሐዊን ይተረጉምላት ነበር።

አጼ ሱስንዮስ ምላሱ ተጉልጉሎ ከእግዚአብሔር ቅጣቱን ሲቀበልና የተዋሕዶ ሃይማኖት ስትመለስ አቡነ ማርቆስ ግብጻዊ ጽድስና ተሹመው በ፲፮፻፴፮ ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ከመንገድ ላይ ጠብቃ ቡራኬ ተቀበለች። ስለ ሃይማኖቷ ብላ ከባሏ መለየቱ እስከ ግብጽ ድረስ መሰማቱን ጳጳሱ ነገረዋታል።

ከዚያም ተመልሳ በመዝዞ ገዳም አቋቁማ በምግባረ ሠናይ ተቀመጠች። ያቋቋመችው ገዳም የወንዶችም የሴቶችም ነበር። ወንዶች መነኮሳት ሴት በወንዶች ላይ መምህርት መሆን የለባትም ብለው ተነሥተውባት ነበር። ነገር ግን አባ ፊትለሥላሴ የተባሉት አባት በነገሩ ገብተው ጠቡን አበረዱት።

የተዋሕዶ ሃይማኖት ከተመለሰችና አጼ ፋሲል ከነገሡ በኋላ ንጉሡን ለማግኘትና ወንድሞቿንና ዘመዶቿን ለማየት ወደ ጐንደር ከተማ ወጣች። ንጉሡም በታላቅ ክብር ተቀበላት። በየቀኑም ሳያያት አይውልም ነበር። ወደርስዋ ሲገባም እደግድጉ* ነበር። ይህም ስለ-ሃይማኖቷ ክብር ነው።

ወለተ ጴጥሮስ ፳፬ ዓመት በዓለም ፳፯ ዓመት በምንኩስና ኖራ በ፶ ዓመቷ በቀረቀረችው ገዳም ዐረፈች። መታሰቢያዋም ኅዳር

* [illegible]

፲፯ ቀን ይከበራል። የተከታይዋ ወለተ ክርስቶስ በዓል ደግሞ ኅዳር ፮ ቀን ይውላል፡ በሃይማኖት ጸንቶ መጋደል ወንድ ሴት አይልም። ቤተ ክርስቲያናችን እንደነ ወለተ ጴጥሮስ እያሌ ልጆች አሏት። የዛሬዎቹ እኅቶችና እናቶችም በምግባር ታንፆ በሃይማኖት ጸንቶ በእምነት መጋደልን ከነዚህ እናቶች ሊቀስሙ ይገባል።

ለ. ፍቅርተ ክርስቶስ

እናታችን ፍቅርተ ክርስቶስ በጉንደር ክ/ሀገር ደራና ፎገራ በሚባል ቦታ ከእናቷ ከወንጌላዊትና ከአባቷ ከካባ በስእለት ተወለደች። ይህች እናት በተወለደችበትና ክርስትና በተነሣችበት ቀን እግዚአብሔርን አመስግናለች። ኋላም ዕድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ በእግዚአብሔር የታዘዙ አባት ከበረሃ መጥተው ከፊደል ጀምሮ የብሉይና ሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ አስተምረዋታል።

ፍቅርተ ክርስቶስ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስም እናቷና አባቷ ዘርዓ ክርስቶስ ለተባለ ሰው ዳርዋት። ዘርዓ ክርስቶስ ጻድቅ ሰው ስለነበር ባልና ሚስቱ በመንፈሳዊ ፍቅር ሆነው ንጽሕናቸውን ጠብቀው ቀን ቀን ሰው መሀል እየዋሉ ሌሊት ሌሊት ከባሕር ገብተው እየጸለዩ በሥጋ ሳይተዋወቁ ዐርባ ዘመን ኖሩ። ከዚህ በኋላ መልአክ ተገልጾ ካእናንተ የሚገኝ ብሩህ ፍሬ አለ፤ ልጅ ትወልዳላችሁ፡ አላቸው። የሰይጣን መልእክት እንዳይሆን ብለው ዐርባ ቀን ከባሕር ገብተው በመጸለይ ቆዩ። የእግዚአብሔር ፍቃድ ነውና ከጸሎት በኋላ በሙሴ ላይ እንደሆነው ሁሉ ዘፀ.፳፱+፳፱ በግንባሩ የብርሃን መስቀል የተሳለ በት ወንድ ልጅ ወለዱ። ይህን ልጅ በሰባት ዓመቱ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት ሲሄዱ ሐናክ እንደተወሰደ መልአክ ነጥቆ ወደ ገነት ወሰደው። መልአኩም ገነትን እዙር አሳይቶት ወደዚህ ዓለም ሲመልሰው አትመልሰኝ ብሎ በመለመኑ በዚያው የሕፃናት አለቃ ሆኖ ቀረ። እንደ ቆንጣዊ ቂርቆስ ማለት ነው። /ገድለ ክርስቶስ ሠምራ ተመልከት/።

ፍቅርተ ክርስቶስና ዘርዓ ክርስቶስ በልጃቸው የተደረገውን ተአምራት እያደነቁና እያመሰገኑ በገድል ላይ ገድል እየጨመሩ

ክርስትናው ለመመለስና ለማስጠመቅ በቅታለች። እንዲሁም ዘር ዘርታ በአንድ ቀን በማብቀል እና ሌሎችን ተአምራት በማድረግ አስተምራ ስድስት ቤተ ክርስቲያን ተክላለች። በዚያው አድርጋም ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳ ለሰባት ዓመት ቆየች።

ምድረ ግብፅ ደብረ ቁስቋም የተባለውን ሥፍራ ለመሳለም ስትወርድ የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያን ከመንገድ በማግኘቷ ወደ ውስጥ ገብታ በእመቤታችን ሥዕል ፊት አብዝታ ሰገደች። በዚህም ጊዜ ከሥዕሉ ቃል ወጥቶ 'እንገዳ ነሽና ስግደቱ ይበቃሻል መቃብርሽ በኢትዮጵያ ነውና ወደዚያ ሂጂ። በዚህ ቦታሽም ላይ ለምልክት ሰባት ምንጮች ታገኛለሽ' የሚል መልእክት ሰማች። ፍቅርተ ክርስቶስ ግን የምቀበረው በኢየሩሳሌም ነው ብላ እያለቀሰች ሰባት ቀን ተቀመጠች። የእመቤታችንን ቤተ ክርስቲያንም ልትለይ አልወደደችም ነበር። በሰባተኛው ቀን ቅዱስ ሚካኤል ዓምደ ብርሃን ይዞ መጥቶ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነውና ተነሥተሽ ወደ ኢትዮጵያ እንሒድ አላት። እየመራትም በትግራይ በደብረ ቢዘን አድርጉ ይዟት ወደ ኢትዮጵያ ገባ።

የተለያዩ አድባራትና ገዳማትን እነ ደብረዳሞን፣ እነ ሐይቅ እስጢፋኖስን ከጐበኘች በኋላ ከአቡነ እስጢፋኖስ ገዳም አደረሳት። በገዳሙ የነበሩ አባቶች ጸሎት አድርገው ዛሬ 'እመ ምዑዝ' ተብሉ የሚጠራውን ገዳም አመልክተዋታል። ቅዱስ ሚካኤል በዓምደ ብርሃን እየመራ በወሎ ክ/ሀገር መቄት ወረዳ ጥባ ማርያም ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ዓምደ ብርሃኑ ተሰወራቸው። እነሱም በገዳሙ አካበቢ በስተ ምዕራብ በኩል ጥቂት ቀን ሰንብተው ለቤተ ክርስቲያን ሥራ አመቺ የሚሆን ቦታ እየተዘዋወሩ ሲፈልጉ የተሰወረው ዓምደ ብርሃን በድንጋጌ አሁን ቤተ መቅደሱ ያለበት ላይ ተተክሎ አያ በራ ታያቸው። በዚህ ደስ ብሏቸው ይህች ቦታስ ምን ታምር አለ። የቦታው ስም ከዚህ የተነሣ 'ምንታምር' ተብሎ ሲጠራ ይኖራል።

ወደ ቦታው ቀርበው ሲመለከቱ የቦታው ባለቤት የነበረ አንድ ሰው በቦታዬ ቤተ መቅደስ አትሠሩም ብሎ ብዙ ተፈታተናቸው። እንዲያውም ይህንኑ ጉዳይ ለቤተ መንግሥት አቅርቦ ውሳኔ ሊያሰጥ በት ወደ ጎንደር ሔደ። በዘመኑ አፄ ሱስንዮስ ሞቶ ልጃቸው አቤቶ

ኖረዋል። ኋላም አፄ ሱስንዮስ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን አጥፍተው ካቶሊክን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ብለው ምእመናንን ሲያስጨፈጭፉ እነዚህ ቅዱሳን ለሃይማኖታቸው ሲሉ ሰማዕትነትን ተቀብለዋል። ቅዱስ ጳውሎስ ተሰፋ የሚያደርጉት ሁሉ ጌታችን አክሊል እንዳዘጋጀላቸው በተናገረው መሠረት (፪ጢሞ.፬ + ፰) ለፍቅርተ ክርስቶስም ስለ ተጋድሎዋ ሰባት አክሊል ወርዶላታል።

ነገር ግን ፍቅርተ ክርስቶስ ተሰይፋ ከሞተች በኋላ አልዓዛርን ከመቃብር ያስነሣ አምላክ ነፍስና ሥጋዋን አዋሕዶ ዳግመኛ አስነሣት። ቅዱስ ጳውሎስ በሥጋ ሆኖ ሦስተኛ ሰማይ ደርሶ መምጣቱን እንዳተናገረ ፪ቆር.፲፪ + ፪ እርሷም እንደገና በሥጋ ፲፭ ቀን ገነትንና ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ሲያስጎበኟት ሰንብቶ ወደ ምድር ተመለሰች። ይህን ሁሉ ተመልክታ ስትመለስ ለምና በዚህ ወቅት በሰ ማዕትነት ያረፉ የቅዱሳን አፅም ስታገኝ ለአፄ ሱስንዮስ 'ይህ የቅዱሳን ፍሬ ነው' ብላ ላከችለት። ንጉሡም በመገረም 'አልገደላችኋትም?' ብሎ ባለሟሎቹን ጠየቀ። 'እኛስ አንገቷን ቆርጠን ገድለናት ነበር ፈጣሪዋ አስነሣት እንጂ' ብለው መለሱለት።

አፄ ሱስንዮስ ተገርሞ መጥተሽ አስተምሪኝ ብሎ ወደ ፍቅርተ ክርስቶስ ልኳል። እርሷ ግን 'የላኩልዎትን የቅዱሳን ዐፅም ከመቃብር ላይ ወስደው ያስቀምጡት፤ ሙት ያስነሣል' ብላ ላከችለት። እንደ ተባለው በመቃብር ላይ ወስዶ ቢያስቀምጠው በኤልሳዕ ዐፅም ሙት እንደተነሣ ሁሉ በቅዱሳኑም ዐፅም አባ ገብርኤል የሚባል መነኩሴ ተነሥቷል። (፪ነገ.፲፫ +፳) ይህ ሰው ከተነሣ በኋላ የተዋሕዶ ሃይማኖትን ክብር፣ የፍቅርተ ክርስቶስን ጽድቅ፣ የሱስንዮስን ሐሳር መስክሮአል። የቅዱሳኑን ዐፅም ይዞ ሕሙማንን እየፈወሰ ሙታንን እያስነሣ ሰባት ዓመት ሀገር ለሀገር እየተዘዋወረ ሲያስተምር ቆይቶ ዐርፏል።

ፍቅርተ ክርስቶስ ታቦተ ኪዳነ ምሕረትን አስይዛ ደናግል መናንያንን አስከትላ ወደ ወሎ ክ/ሀገር ቆቦ ወረዳ ራያና ዘቦ በመሔድ ራማ ኪዳነ ምሕረት የምትባል ገዳም ቆየች። ፳ የሚሆኑ መነኮሳትን አስከትላ ከሀገር ውጭ በመጓዝ አረማውያንን አስተምራ ወደ

ፋሲል የተተካበት ወቅት ነበርና ፋሲል ‘ቦታው ቤተ ክርስቲያን ከተሠራበት አይፍረስ፣ ካልተሠራበት ግን እንዳይሠራበት’ ብሎ ወሰነለት።

ቅዱስ ሚካኤል ቀድሞ ደርሶ ፍቅርተ ክርስቶስን ቤተ መቅደስ ሥራ ብዙ ተአምራት ይደረግልሻል አላት። ይህን ሲነግራት ከሳሹ ሳይደርስ /ዕለቱ ዓርብ ነበር/ በአንድ ቀን በስሚዛ ወይም በሠንሠል እንጨት፣ በነጠላ ማገር፣ በዓይጥ ሐረግ ግድግዳ ቤተ መቅደስ ሠሩ። ይህ የሆነው ታኅሣሥ ፲፱ ነው። ታኅሣሥ ፲፮ ሰሎሞን ቤተ መቅደ ስን ሠርቶ ሲጨርስ እንደባረከለት ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቦታውን ሊባርክላቸው ከቅዱሳን መላእክትና ከጻድቃን ሰማዕታት ጋር በክብር ተገልጦላቸዋል። (ዜናና + ፲፱)

በዚህ ጊዜ ምድር ከክብሩ የተነሣ ተናወጸች። የቢታንያ ድንጋዮች ለፈጣሪያቸው ክብር እንደዘመሩ ቤተ መቅደሱ በአራት ማዕ ዘን ሰገዷል። ፍቅርተ ክርስቶስም የፈጣሪዋን ግርማ አይታ በመደነቅ ‘ቤአውነት ልታጠፋኝ መጣህን?’ ጌታችን ግን ‘ላጠፋችሁ ሳይሆን ለምሕረት መጥቻለሁ ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳን አደርጋለሁ ላንቺም ቃል ኪዳን እሰጥሻለሁ’ በማለት ቃል ኪዳን ሰጣት። (መዝ.፹፰+፫) አምላክ ፍቅርተ ክርስቶስ ብሎ ባንቺ ስም የተማፀነ፣ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ፣ ግብር ለቤተክርስቲያን የሰጠና የረዳ፣ በዚህች የተቀበረ እስከ ፲፪ ትውልድ ይማርልሻል። መጀመሪያ ሳልምረው ቦታሽን አላስረግጠውም የሚልና ሌሎች ቃል ኪዳኖችን ተቀብላ የካቲት ፳፱ ቀን ዐረፈች።

ሐ. አቡነ መብዓ ጽዮን /በ፲፭ኛ መቶ ክፍለ ዘመን/

መብዓ ጽዮን በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ልጅ በማጣታቸው በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ከሚለምኑ ባልና ሚስት ተወለዱ። የንቡረ ዕድ ሳሙኤል ረባን ወገን የሆነው መብዓ ጽዮን አባቱ እስከ ዳዊት ያለውን ትምህርት አስተማረውና ዲቁናን ተቀበለ። ልጁ የትምህርት ዝንባሌ እንዳለው አባቱ ተረድቶ ቤተ ማርያም ከሚባ ለው ደብር ወስዶ ተክለ አማኑኤል ለሚባል የቅኔ መምህር ዘንድ

አስገባው። በዚያም ቅኔንና ሌሎችን የቤተ ክርስቲያን እውቀቶች ገበየ። ከዚያም በተጨማሪ ሥዕል መሳልና ጽሕፈት መጻፍ ተማረ። መብዓ ጽዮን የልጅነቱን ዘመን ሲፈጽም ‘ለነፍሳቸው ድኅነት ዋጋ ያገኙ ቅዱሳን ብዙ ናቸው። በመጾም ያገኙ አሉ፣ በትምህርት ያገኙ አሉ፣ በድካም ያገኙ አሉ፣ በጸሎት በትጋት ያገኙ አሉ፣ እኔ ግን የጌታዬን የኢየሱስ ክርስቶስን የሞቱን መታሰቢያ ማድረግ ይገባኛል። በዚሁም ፊቱን እያለሁ፣ እሱ ጌታ ለደቀመዛሙርቱ የትንሣኤዩን መታሰቢያ ብታደርጉ የሞቴን መታሰቢያ አድርጉ’ ብሏልና በማለት ፍላጐቱ በምንኩስና በመኖር ፈጣሪን ማገልገል መሆኑን ለወላጆቹ ገለጸላቸው።

አባትና እናቱም ፈጣሪህን ለማገልገል ኅሊናህ ከአሰበ እሽ በጄ ደስተኛ ነን ብለው ፈቀዱለት። ከዚያም መብዓ ጽዮን ዳሞት አባ ገብረ ክርስቶስ ወደሚባል መነኩሴ በመሔድ መነከሰ። አባ መብዓ ጽዮን ከአባ ገብረ ክርስቶስ ጋር በመቀመጥ ሥርዓተ ምንኩስናን ካጠኑ በኋላ አባ ገብርኤል ዘንድ ሔደው የቅስናን መዓርግ ተቀበሉ። ከዚያም በኋላ በአበው ሕግ በምንኩስና ተወስነው በበአታቸው ሁነው ‘ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የዕለተ ዓርቡን መከራህን አሳየኝ ስለራሴ ፈጽሞ አለቅስ ዘንድ’ ብለው በጸለዩ ጊዜ መከራ መስቀሉን ለማየት ትፈቅዳለህን? ብሎ ጠየቃቸው። ጻድቁ አባ መብዓ ጽዮንም ‘አዎ አይ ዘንድ እወዳለሁ’ ሲሉ ለጌታቸው መለሱለት። ያን ጊዜም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕፀ መስቀል ተተከለ። በመስቀሉ ላይም እጆቹና እግሮቹ ተቸንክረውና ተዘርግተው ታዩ በራሱ ላይም የእሾህ አክሊል ደፍቶ ነበር።

እንዲህ ሆኖ በርም አደባባይ ለቅዱስ ጴጥሮስ እንደታየው ጌታችን ለአባ መብዓ ጽዮን ታያቸው። ከዚያም በኋላ አባ መብዓ ጽዮን የጌታችን የመድኃኔዓለም ሕማሙን፣ መከራውን፣ ግርፋቱን፣ እስራቱን በጠቅላላ አሥራ ምስቱን ሕማማተ መስቀል በማሰብ ጀርባቸ ውን በአለንጋ ይገርፉ ነበር። ራሳቸውን በዘንግ ይመቱ ነበር።

የጌታን መከራ መስቀል እያሰቡ ዓይኖቻቸው እስከሚጠፋ ድረስ ያለቅሱ ነበር። ጌታችን ጉንደ መስቀሉን (የመስቀል ግንድ) እንደተሸከመ በማሰብ ትልቅ ደንጊያ ተሸክመው ይሰግዱ ነበር። መራራ ሐሞት መጠጣቱን በማሰብ ዓርብ ዓርብ ኮሶ ይጠጡ ነበር። የጌታ ደቀመዝሙር ዮሐንስ ወንጌላዊ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ አብሮ ስለነበረና ዐይን በዐይን ስለተመለከተ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል እያሰበ ሰባ ዘመን ፊቱ በሐዘን ተቋጥሮ እንደኖረ ሁሉ ጻድቁ አባ መብዓ ጽዮንም እንደ ዮሐንስ ወንጌላዊ የጌታችን መከራ መስቀል እያሰቡ ከዓለም ተድላና ደስታ ተለይተው በትምህርት በትሩፋት በገድል ጸንተው ኑረዋል።

ጻድቁ መብዓ ጽዮን በሕይወተ ሥጋ ዘመናቸው የላመ የጣመ እንዳልተመገቡ፣ በፈረስ በበቅሎ እንዳልሄዱ፣ አልጋ ላይ እንዳልተኙ፣ ገድላቸው ያስረዳል። የክርስትናን ትምህርት ሲጋፋት ሰዎች እንዲ ሰፋፋ ያደረጉት አባ መብዓ ጽዮን የጌታን ሕማማተ መስቀል እያሰቡ ዘወትር ስለሚያነቡ ዓይኖቻቸው ጠፍተው ነበር። ነገር ግን እመ ብዙኃን የሆነችው ቅድስት ድንግል ማርያም ወደኚህ ጻድቅ አባት በዓት የብርሃን ጽዋዕ ይዛ መጥታ ዓይኖቻቸውን ቀብታ አድናቸ ዋለች። ከዚህ የተነሣ ‘ብትረ ማርያም’ እየተባሉ ይጠሩ እንደነበር ገድላቸው ያስረዳል።

የጻድቁ መታሰቢያ በዓል በየዓመቱ ጥቅምት ፳፯ ቀን እና ከመድኃኔዓለም የስቅለቱ በዓል ጋር ይከበራል። ጥቅምት ፳፯ ቀን ለወዳጆቹ እውነተኛውን ዋጋ የሚከፍል መድኃኔዓለም ክርስቶስ ለጻድቁ /አባ.መብዓ ጽዮን/ ብዙ ቃል ኪዳን የገባበት ቀን ነው።

መ. አቡነ ተጠምቀ መድኅን /በ፩ሺ፯፻፲ ዓ.ም/

አቡነ ተጠምቀ መድኅን በጉጃም ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ኢንብሶ በተባለ ቦታ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፩ሺ፯፻፲ ዓ.ም ከአባታቸው ወልደ ክርስቶስ እና ከእናታቸው ወለተ ማርያም ተወለዱ። ስማቸው ተጠምቀ መድኅን የተባለው ጥምቀተ ክርስትናቸው ጥር ፲፩ ቀን የተፈፀመ በመሆኑ ነው።

አባ ተጠምቀ መድኅን በልጅነታቸው የወላጆቻቸውን በግና ፍየል እየነዱ ወላጆቻቸውን በቅን እያገለገሉ አድገዋል። በባልንጀሮ ቻቸው ዘንድ ልዩ ፍቅር ነበራቸው። ባልንጀሮቻቸው ሲጣሉ ያስታር ቃሉ። በእረኝነት ሲውሉ የሚሰጣቸውን ምግብ ለድሆችና ለመንገደ ኞች እያካፈሉ ይሰጡ ነበር። በወላጆቻቸው ቤት ጥግ የምትኖር የሥጋ ደዌ የጠናባት አንዲት መበለት እንጨት በመልቀም፣ ቁስሏን በማጠብ የሚያስፈልጓትን ሁሉ በማድረግ ይረዷት ነበር።

እኚህ አባት ከልጅነታቸው ጀምሮ በጾም በጸሎት የሚተጉ ትሑትና ትዕግሥትን የተላበሱ ለሰው ልጆች ሁሉ አክብሮትና ፍቅር ያላቸው ነበሩ። ጻድቁ አባታችን ለትምህርት ካላቸው ፍቅር የተነሣ የሚያግዷቸውን በጎችና ፍየሎች በዱር ትተው ከልጅነታቸው ጀምሮ እየወሰዱ ዳዊት ካስደገሟቸው ቅዱሳን መነኮሳት እግር ሥር ተቀም ጠው ትምህርታቸውን እየተማሩ አባታቸው እንዳያውቁባቸው በምሽት ይመለሱ ነበር። መጻሕፍት ያስተማሯቸው ባህታዊ አባታቸውን አግኝተው ‘ልጅህን ስጠኝ ላስተምረው’ አሏቸው። አባታቸው ግን ፍቃደኛ አልሆኑም ነበር። አንድ ቀን ወደቤት ሲገቡ አባ ተጠምቀ መድኅን ዳዊት እንግተው በማየታቸው ነገሩ ግራ ያጋባቸው አባት ነገሩን ለመረዳት ፍየሉቹና በጎቹ ከሚውሉበት ሜዳ ሔዱ። ከዚያ ያዩት ነገር አስገራሚ ነበር። ፍየሉቹና በጎቹ ሌሎቹም ከብቶች ከተኩላና ከነብር ጋር እየቦረቁ ሲጫወቱ ውለው ሲመሽ ተኩላዎቹና ነብሮቹ ፍየሉቹንና በጎቹን ከበረት አስገብተው ሲመለሱ ማየታቸው ነበር።

አባ ተጠምቀ መድኅን እንደተለመደው ማታ ዳዊታቸውን አንግተው ሲመጡ አባታቸው፦ ‘ልጄ ዛሬ የትዋልክ?’ በማለት ሲጠይቋቸው ከብቶች ሳግድ በማለት መልስ ሰጡ። አባታቸውም መልሰው፦ ልጄ ነገሩን ሁሉ ተረድቼዋለሁ ከብቶቹን እነዚያ ጠባቂዎቻቸው ይጠብቁቸዋል፣ አንተ ግን ሔደህ ተማር ብለው ከባሕታውያኑ ዘንድ እንዲማሩ ሰደዷቸው። ከዚህ ጊዜ አንስቶ መንፈሳዊ ትምህርት እየተማሩ አደጉ።

አባ ተጠምቀ መድኅን ፳፫ ዓመት ሲሆናቸው የምንኩስናን ሕይወት መርጠው ወደ መርጡለ ማርያም በመሔድ በአባ ዝክረ ማርያም እጅ ምንኩስናን ተቀበሉ። በዚያም በጾምና በጸሎት እየተጉ ከቆዩ በኋላ ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል ወደ ስግዳ ሔዱ። በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔር ለአቡነ ተጠምቀ መድኅን በሕልም ተገልጾላ ቸው ‘ለአንተ ኃጢአቱን የሚናዘዘውን ሁሉ እምርልሃለሁ’ በማለት ቃል ኪዳን ገባላቸው። ጻድቁ አባታችን በሕልም የተገለጸላቸውን ቃል ኪዳን ፈሩ። ለእኔ ለኃጢአተኛው ይኽ አይገባም በማለት ወደመጡበት ለመመለስ ፈለጉ። ሆኖም እግዚአብሔር በድጋሚ ተገልጾ ‘ወደ አዘዝኩህ ቦታ ሒድ፣ የማዝህንም አድርግ’ አላቸው። እላቸውም እንደ ታዘዙት ከአቡነ ማርቆስ ቅስናን ተቀብለው ወደ ቦታቸው ተመለሱ።

ከዚያም አባ ተጠምቀ መድኅን ምግባርና ቅድስና መማር አለ ብኝ በማለት ሡደታላቁ ቅዱስ ወደ አባ ባስልዮስ ዘንድ ሔደው ትሕትናና ትዕግሥት ሳይጉድልባቸው በአገልግሎታቸው እየተጉ ከእግራቿው ሥር ተቀምጠው ይማሩ ነበር። ሱቃሄ +፵፯ ዘወትር ወደ ፈጣሪያቸው ይጮሃሉ። ለጸሎት እንዲመቻቸው ብቻቸውን በስግደት ሲያሳልፉ በላያቸው ላይ ብርሃን ያርፍ ነበር።

በዚህ ዓይነት በገዳሙ አንድ ዓመት ከተቀመጡ በኋላ ወደ ኢንብሶ በመሔድ ወምበሪያ በተባለች ቦታ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የደካሞችን ልብስ እየሰፉ፣ ደወል እየደወሉ፣ በጾም በጸሎት እየተጉ ሥጋቸውን እያጉሳቆሉ መኖር ጀመሩ። የቅዱሳን መላእክትም አገልግሎትና እንቅስቃሴያቸው ይገለጽላቸው ነበር። መነኮሳትን ሰብስበው እግዚአብሔር የገለጸላቸ ውን ይመክራሉ። እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ብዙ ተአምራት ከመሥራታቸው በተጨማሪ ሰባት ገዳማት መሥርተው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት አሳንፀዋል። እነዚህ በአንድ አበምኔት የሚተዳ ደሩ ሲሆኑ በቻግኒ ሥጋዲ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም መሥርተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ወደ አሥራ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በቻግኒና አካባቢው አሳንፀዋል።

አባ ተጠምቀ መድኅን አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀው ሕዝ ቡን ካስተማሩ በኋላ በዓሐንቻ ማርያም በወንዶች ገዳም ለ፳፫ ዓመ ታት በተጋድሎ ቆይተዋል። የጋዝጌን ሕዝብ ጨምሮ እስከ ሱዳን ድን በር ድረስ አሕዛብን በማስተማር አጥምቀው ለክርስትና ሕይወት ካበቁ በኋላ ሰኔ ፳፫ ቀን ፩ሺ፯፻፹ ዓ.ም ዐርፈዋል። ዐፅማቸው በጋሾላ ቅዱስ ጊዮርጊስ እናቶች ገዳም ይገኛል። በዓለ ዕረፍታቸው በየዓመቱ ሰኔ ፫ ቀን በታላቅ መንፈሳዊ አገልግሎት በጋሾላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሴቶች ገዳምና በዓሐንቻ ማርያም ወንዶች ገዳም ይከበራል።

፫.፬. ሴሎች ቅዱሳን

ሀ. አቡነ ዜና ማርቆስ (በ፲፫ኛ መቶ ክ/ዘመን)



የሰላሌ ገንዶ ሰላሌ ሚዳ አቡነ ዜና ማርቆስን ሲወጓቸው

ሀገራቸው ዞረሬ /ጽላልሽ/ ነው። አባታ ቸው ቀሲስ ዮሐንስ የአቡነ ጸጋዘአብ ወንድም ነው። እናታቸው ዲቦራ (ማርያም ዘመዳ) ትባላ ለች። የአቡነ ቀውስጦስ እህት ናት። በብሥራተ ማርቆስ ወንጌላዊ ኅዳር ፳፱ ቀን ተወልደዋል። ዐርባ ቀን ሲሞላቸው ሊያስ ጠምቋቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወሰዷቸው። ጸሎተ ጥምቀቱ ደርሶ ከውኃ ውስጥ ሲከቷ ቸው ቆመው እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለው ሦስት ጊዜ ሰግደዋል። ውኃውም ፈላ እጥማቂው ቄስ የአቡነ ጸጋዘአብ ወንድም ካህኑ እንድርያስ ነበር። ዕድሜው ሰባ ሁለት ዓመት ስለነበር በሕፃኑ ድርጊት ፈርቶ ወደ ቤተመቅደስ ሮጠ። ቅዱስ ሩፋኤል ከፍርሃቱ እጽናንቶ ከማየ ጸሎቱ ራሱን እንዲቀባ ነግሮት በራ የነበረ ራሱ ፀጉር አብቅሎለታል። አቡነ ዜና ማርቆስ አምስት ዓመት ሲሞላቸው ወላጆቻቸው ለመምህር ሰጧቸው በሦስት ዓመት ብሉይ ሐዲስ አጥንተው በስምንት ዓመታቸው ከአባ ቄርሎስ ዲቁና ተቀብለው ሲመጡ ሽፍቶች የእጃቸውን በትር ነጠቋቸው። እሳቸውም ወደ ጌታ ቢያመለክቱ በትራቸው እባብ ሆና ነድፋ ገድላቸዋለች። እንዲህ እያሉ አድገው ሠላሳ ዓመት ሲሞላቸው ማርያም ክብራ ለምትባል ደግ ሴት አጋቡአቸው። ልማደ መርዓዊ ወመርዓት (ሙሽ ራውና ሙሽራይቱ) ያድርሱ ብለው መጋረጃ ሲጥሉባቸው በሌሊት ወጥተው ሔዱ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ሀገረ ምሑር አድርሷቸው መስፍን ብሔሩ (ሀገረ ገዥ) አውጊንትን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ራብኝ አብላኝ አሉት፣ እሱ ማን ነው? አላቸው። አምላካችን ነው አሉት። የኔስ አምላክ ማኮስ ነው አላቸው። ወስዶ ከቤተ ጣዖቱ ቢያሳያቸው በእግራቸው ረግጠው አስጠሙት። መስፍኑ ተቆጥቶ አሠራቸው። ነገር ግን መልአኩ ፈታቸውና ሔደው ለሁለተኛ ጊዜ እንደቀድሞው ያበላቸው ዘንድ ጠየቁት፣ በዚህ ተናዶ በጦር ሲወጋቸው ሲነሣ ምድር አፏን ከፍታ ባሕር ሆና አሰጠመችው። ወገኖቹ በዚህ ጊዜ አምነው ተጠምቀዋል። ሚስቱ መግደርም ከሰባት ልጆቿ ጋር ተጠምቃለች። እሱንም ከአምስት ዓመት በኋላ ጸልየው አድነውት የትሩፋት ሥራ ሠርቷል። ከዚህ በኋላ ምድረ ጉራጌ ወርደው ሕዝ ቡን አስተምረው ወደ ሃይማኖት መለሱ። የእሻል ንጉሥ አብደልማል ንም ከነሕዝቡ አስተምረው አሳምነው አጥምቀውታል። አንድ ቀን እንግዶች መጥተውባቸው እግር ሊያጥቡ ጉንበስ ቀና ሲሉ የጣዱት ፈላ እንሣለሁ ብለው እጃቸውን ፈጃቸው። አቡነ ተክለሃይማኖት ከተግባር ቤት መጥተው እፍ ቢሉባቸው ተፈውሰዋል። እንግዶቹም ያዩትን ተአምራት ለመስፍኑ ብሔሩ ለድል አስገድ ነገሩት። ጣዖት አምላኪ ነበርና አጠፋቸዋለሁ ብሉ ሔደ። የቆመበትን ቦታ ከሦስት ከፍለው ጠንቋዮቹን አስጥመው አሳምነው አጥምቀውታል። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በዚህ ጊዜ ምንኩስና ሰጥተዋቸው ወደ ደብረ አስቦ ሔዱ። አቡነ ዜናማርቆስም መዓርገ ምንኩስና ከተቀበሉ በኋላ ደብረ ብሥራትን ገድመው እያስተማሩ ኖረው በ፪፻ አናብስት በ፪፻ አናምርት ታጅበው በደመና ተጭነው ብዙ ቦታ በመሔድ አስተምረው አሳምነዋል። ከዕረፍታቸው በፊትም ልጆቻቸውን በሙሉ ከየሀገሩ ሰብስበው ቅዳሴ ቀድሰው ሲያቆርቡ ከብዛታቸው የተነሣ ፀሐይ ልትገባ ስለሆነ ወደጌታ አመልክተው አቀብለው እስኪፈጽሙ ድረስ ፀሐይ ባለችበት እንድትቆም አድርገዋል። ከዚህም የበዙ ተአምራት ሲያደርጉ ኖረው በተሰፋቸው ያመነ በኪዳናቸው የተማፀነ ዋጋውን እንደማያጣ ጌታ ቃልኪዳን ሰጥቷቸው በተወለዱ በ፻፶ ዘመናቸው ታኅሣሥ ፫ ቀን ዐርፈዋል።

ለ. አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ



[illegible]

ትውልዳቸው ከዘርዐ ጊዮርጊስ ነገድ እስጢፋኖስ ነው። አባታቸው እስጢፋኖስ እናታቸው እመተማርያም ይባላሉ። ለመምህር ሰጥተ ዋቸው ሲማሩ አድገው ኋላ ወላጆቻቸው ዕጮት ሲለዩ ላቸው ደብረበገ ኩል ገብ ተው ሥርዓተ ምንኩስና ከአበው እያጠኑ ለትልቁም ለትንሹም በትሕትና እየ ታዘዙ፣ ውኃ እየቀዱ እን ጨት እየሰበሩ በትጋር ምትሩ በጸሎት ይኖሩ ጀመር። ሲያጣን በውዳሴ ከንቱ ጾር ቢመጣባቸው

ከማኅበረ መነኮሳቱ ተለይተው በተባሕትዎ ለመኖር ሽተው ወጥተው ሲሔዱ ተከዜ ደረሱ። ወንዙ ሞልቶ የማያሻግራቸው ቢሆን ውኃውን በትእምርተ መስቀል ባርከው በአንድ እጃቸው መጽሐፍ በአንድ እጃቸው መብራት እንደያዙ ገብተው መብራቱ ሳይጠፋ መጽሐፉም ሳይበላሽ ተሻግረዋል። ዋልድባ ሲደርሱ ጌታ እዚህ ተቀመጥ ስለአላቸው ገዳም ገድመው ሥርዓተ ምንኩስና እያስተማሩ ተቀመጡ። ዛሬ በዋልድባ የሚያመሰግኑበትን ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያምን ከተከዜ ወዲህ ያመጡ እሳቸው ናቸው። ይህንንም እየጸለዩ ሲሔዱ ከንድ ከስንዝር ያህል መሬት ለቀው ይታዩ ነበር። አንድ ቀንም ይህንኑ ጸሎት ደግመው ውኃውን ሲባርኩት ኅብስተ ሕይወት ሆኖላቸው ከነደቀ መዛሙርቶቻቸው ተመግበውታል። እመቤታችንም የፍቅር መግለጫ ነጭ ዕጣንና ዕንቁ ሰጥታቸዋለች። ውዳሴዬን ከቅዳሴዬ አንድ አድርጎ የደገመውን አንተ ከገባህበት መካነ ሕይወት (የሕይወት ቦታ) አስገባዋለሁ ብላ ተስፋም ሰጥታቸዋለች። ጊዜ ዕረፍታቸውም ሲደርስ ጌታ በስብሐተ መላእክት ተገልጾ በስምህ የተማፀነውን በጉ የሠራውን ዜና ገድልህን ያጻፈ ያነበበ፣ የተማረ ያስተማረውን እስከ ዐሥር ትውልድ ድረስ ምሬልሃለሁ። በዚህም ቦታ የሚሰበሰቡ ልጆችህን ከዕፃ ከፍዳ እሠውርልሃለሁ አላቸው። እንኪያስ ቦታዋን ባርክልኝ ብለው እንደ መሶብ አንስተው አስባርከዋት በገዳመ ዋሊ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ዐርፈዋል።

ሐ. አቡነ ታዴዎስ ዘጽላልሽ

ትውልድ ሀገራቸው ጽላልሽ (ሆረሬ) ነው። አባታቸው ሮማንዮስ እናታቸው ማርታ ይባላሉ። ሮማንዮስ ቄስ ነው። የአቡነ ተክለሃይማኖት እኅት ነው። በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ በጽላልሽ ረሀብ ጸንቶ ነበር። እሳቸው ግንቦት ፳፫ ቀን በመንፈቀ ሌሊት በልብሰ ብርሃን ተጠቅልለው ተወለዱ። ቤታቸው በበረከት ተመላ። ለሀገሬው ዝናም ዘንሞለት ሕዝቡ ከጻድቁ እናትና አባት የተመጸወቱትን ከፍለው ዘሩ። አቡነ ታዴዎስ በተወለዱ በዐርባ ቀናቸው ሐምሌ ፪ ቀን ሲጠመቁ የተዘራው እህል አንድ ሳይቀር አፍርቶ ተገኝቷል። ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ስለ.ቀ ካህናቱ ለሕይወት ብ ስጥተዋቸው ሲማሩ አደጉ። አቡነ ተክለሃይማኖት ዳሞት (ወላይታ) ተሻግረው መተሉሚን አስተምረው 'በእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ጸሎት መተሉሚን በሃይማኖት ወልጄዋለሁ። በምግባር አሳድጌዋለሁና እኅትህን ይዘህ በቶሎ ና!' ብለው ላኩባቸው። እኅታቸው ትቤጽዮን ትባላለች። የመተሉሚን ወንድም ዝግናን አግብታ አባ ኤልሳዕን ወልዳለች። ከባሏ ተጣልታ ነበርና እሷን ከባሏ አስታርቀው እሳቸው አቡነ ተክለሃይማኖትን እያገለገሉ ዘጠኝ ዓመት ኖረዋል። በኋላ አቡነ ተክለሃይማኖት ወደ አባ በጸሎተ ሚካኤል ሲሔዱ እሳቸውም ወደ ጽላልሽ ተመልሰው ስለነበር አጼ ይኩኖ አምላክ እንድትመክረኝ እንድትገስጸኝ ከቤቴ ተቀመጥ ብለው ከቤተመንግሥት አስቀመጧቸው። ሰይጣን ለፀብ ለምቀኝነት አያርፍምና ጠላ ቤቷን ከቶ የሚገድል ሽታ አሸተታትና ሞተች። አባ ታዴዎስ ወንዝ ገብተው ሲጸልዩ ሙቷ ተነሥታለች። ከዚህ በኋላ ውዳሴ ከንቱ ይሆንብኛል ብለው ወደ ደብረ ሊባኖስ ተመለሱ። አቡነ ተክለሃይማኖት ወደ ጽጋጋ (ጅጅጋ) ሒድ አሏቸው። ለምን ቢሉ? አባ አኖሬዎስ ሒደው ሲያስተምሩ ያገሬው ሰዎች ደብድበው አሥረዋቸው ነበርና እሳቸውን ለማስፈታት ነበር። የአካባቢው ንጉሥ መቶጥ ይባላል። በነፋስ ሠረገላ ተጭነው ሒደው ከፊቱ ወርደው ሲቆሙ ደንግጦ ከሰማይ መላእክት ነህ ወይስ ከሰው ወገን? ቢላቸው። እኔ ከሰው ወገን ነኝ አሉት። ክርስትናንም አስተማሩት ጋኔን ከእሳት ላይ ጥሎት ሲሰቃይ የሚኖር ልጅ ነበረው አድነውለታል። ይህን አይቶ እምነ ሕዝቡም እንዲያ ምኑና ክርስትናን እንዲቀበሉ አዋጅ ነገረ። እንደ ሐዋርያው ታዴዎስ ሃያ አምስት ግመል በመርፌ ቀዳዳ በተአምራት አሳልፈው በማሳየታቸው አፍጃል የሚባል ያንድ ባለጠጋ ልጅ በምትሐት እንደሚያደርጉት አድርጉ በመናገሩ ከግመሉ፣ እንዲቱ ረግጣው ሞተ፤ ይህን ሙሳ የሚባል ልጅም በተቀበረ በሦስተኛ ቀን 'አልዓዛርን ከሙታን በአስነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ልጁ ና ተነሥ' ብለው ይህንን መቋሚያዬን ወስደህ ከመቃብሩ ላይ አኑር ብለው ለአፍጃል ሰጥተውት እንዳሉት ቢያደርግ አፈፍ ብሎ ተነሥቷል። ይህን አይተው ሕዝቡ ሁሉ አምነዋል። ከዚህ በኋላ ሙሳን ሙሴ ብለው ሊቀ ካህናት አድርገው ፲፪ አብያተ ክርስቲያናት አሳንፀው አኖሬዎስን ይዘው ተመልሰዋል። አቡነ ተክለሃይማኖትም ከንጉሡ ተማክረው ሊቀካህናት ዘጽላልሽ ብለው ሾመዋቸዋል። ንጉሡ ዓምደ ጽዮን ፍቅረ ዝሙት አድርዞት የአባቱን ቅምጥ ቢያገባት ሒደው ገሠጹት። በዚህ የተናደደች የንጉሡ ሚስት የኗሊት አሳስራ ከጥልቅ ገደል አስጣለቻቸው። በዚህ ጊዜ የመቶ ሃያ ዓመት አረጋዊ ነበሩ። የታዘዘ መልአክ ገብረ እግዚአብሔርና ውቢት የተባሉ ደጋግ ሰዎችን አስነስቶ ሥጋቸውን ወስደው ከበዓታቸው ቀብረው የተሰጣቸውንም ቃል ኪዳን በዳግማዊ አጼ ዳዊት ዘመን በሕዝቡ ፊት መስክረዋል። ንጉሥ ዳዊትም ዜና ገድላቸውን አጽፈዋል፤ ሥጋቸውንም ወደ ከተማቸው በክብር አፍልሰው በተቀደሰ ሥፍራ አኑረውታል።

መ. አባ ሊባኖስ ዘመጣዕ

አባ ሊባኖስ ዘመጣዕ- አባቱ አብርሃም እናቱ ንግሥት ይባላሉ፤ ሐምሌ ፫ ቀን ተወለደ። ስሙንም በመልአክ ሰያሚነት 'ሊባኖስ' ተባለ። ወላጆቹም ደጋጎች ስለነበሩ ልጅ በመውለዳቸው አበው መነኮሳትን ሰብስበው ግብዣ አደረጉ። ባደገም ጊዜ ሚስት ፈልገው ሰርግ ደግሰው ወደ ጫጉላ ቤት እንዲገባ አዘዙት ጻድቁ ሊባኖስም እኔ ከእባቱ ጋር እንጂ ከሙሽራይቱ ጋር አልተኛም በማለት እንቢ አለ። ተኝቶም ሳለ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል መልአክ ሌሊት መጥቶ ሦስት ጊዜ ሊባኖስ በማለት በስሙ ጠርቶ ና ውጣ ተነስ፤ ከአባትህም ተለይ፤ አንተ የሰማያዊ አባትህና የመንግሥተ ሰማያት ሙሽራ ነህ እንጂ የዚህ ዓለም ሙሽራ አይደለህም። የአባትህም ጉብረትና ሀብት ያልፋል አለው። በዚያችም ሌሊት አባቱ ሳይሰማ ከጉት ተነሥቶ መልአኩ እየመራ ወደ አቡነ ጳኩሚስ አደረሰውና ከሱ ተሠወረ። አባ ጳኩሚስም በዓት በመስጠት ሥርዓተ ገዳምን፣ እስኪማ* መላእክትን፣ ቅናተ ዮሐንስን** አስተምሮት በመጋቢት ፳፩ ቀን አመነኮሰው። ከዚህ በኋላ ያ መጀመሪያ የተገለጠለት መልአክ ወደ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ሂድና የብዙዎች አባት ትሆናለህ። ዝናህ እጅግ በስፋት ይነገራል አለው። ጻድቁም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በአክሱም ተቀመጠ ደግሞም ወደሽዋ መጣ ምድረ አሰቦ (ግራርያ) በዓቱን በጫካ ውስጥ አደረገ በዚያም ብዙ መነኮሳትን አወጣ። መልአኩም ዳግመኛ መጥቶ በዚህ ቦታ ሰውና እግዚአብሔርን የሚያገናኝ የሚያስታርቅ ጻድቅ ይወጣበታል። ሀገሩም በስምህ ደብረ ሊባኖስ ተብሎ ይጠራል። የመነኮሳትም መንደር ይሆናል ብሎት በሌሊት አስወጥቶ ወደ አክሱም ወሰደው። በአክሱምም ፊት ለፊት በዓቱን መስርቶ ሲኖር ሰባት ፀበል አፍልቆ በጸሎቱ ብዙ ተአምራትና ትሩፋት በመፈጸሙ ካህናት ቀንተው ምትሐት ነው ብለው በቅንዓት ሊገድሉት በፈለጉ ጊዜ ተነስቶ ደረታ ወደ ምትባል ቦታ ሄዶ እየጸለየ በነዚህ በጠሉት ሰዎች ሀገር ላይ ሦስት ዓመት ሙሉ ዝናብ እንዳይዘንብ አደረገ። ኋላም በጥፋታቸው ተጸጽተው ይቅርታ በጠየቁት ጊዜ ከፈጣሪ አማለዳቸው ዝናብም ዘነበ በሥራው አመኑ፤ ተደሰቱም። በመጨረሻም ወደ ኤርትራ አካለጉዛይ አውራጃ ልዩ ስሙ መጣዕ በተባለ ቦታ ጠበል አፍልቆ ሙት አስነሣ፣ እውር አበራ ታላቅ ገዳምም መሠረተ። አፄ ገ/መስቀል በትግራይ ተምቤን አምበራ ላይ ትልቅ ገዳም በስሙ ሠራለት። ቅዱስ ላሊበላም ካነፃቸው ፲፩ ቤተመቅደሶች አንዱ የአባ ሊባኖስ ነው። በሀገራችን በስሙ ፺፩ አብያተ ክርስትያናት ይገኛሉ። ጻድቁ በተወለደ ፲፱ ዓመቱ ጥር ፫ ቀን በክብር ዐረፈ።

* አስኬማ- [illegible]

** [illegible]

ሠ. አቡነ ሀብተማርያም (፲፬ኛ መ/ክ/ዘ)

ታላቁ ጻድቅ አቡነ ሀብተማርያም የተወለዱት በመንዝ አውራጃ ልዩ ስሙ የራዊ በተባለ ቦታ ሲሆን የአባታቸው ስም ፍሬ ብሩክ የእናታቸው ስም ዮስቴና ይባላል። ሁለቱም በሕግ ጋብቻ ጸንተው ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው ምግባር ትሩፋት ሠርተው በንጽሕና በቅድስና ይኖሩ ነበር። ሆኖም ልጅ አልነበራቸውም። በዚህ ሁኔታ ያሉት ቅድስት ዮስቴና መንነው በአካባቢያቸው ከሚገኝ ጫካ ውስጥ ዋሻ ፈልገው ገብተው ዘጉ። በዚያም አንድ መናኝ መነኩሴ አግኝተዋቸው እግዚአብሔር በቅድስቲቱ ያሰውን ድብቅ ነገር ስለገለጠላቸው 'አንቺ ለምንኩስና የተፈቀደልሽ አይደለሽም፤ ወደ ቤትሽ ግቢ ጸሎቱ ለዓለም ሁሉ የሚጠቅም ሰው ሁሉ የሚማፀነው ስሙ፣ ገድሉ፣ ትሩፋቱ በዓለም ሁሉ የሚነገርለት ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ' አሏቸው። የእግዚአብሔርን ድንቅ ተአምራት የሰሙ ቅድስት ዮስቴናም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። የተናገረውን የማያስቀር አምላክ በቸርነቱ ጉበኛቸውና ነሐሴ ሃያ ስድስት ቀን ፀነሱ። ግንቦት ሃያ ስድስት ቀንም ደምግባታቸው እንደ ንጋት ኮከብ ያማሩ ሀብተ ማርያም ተወለዱ። በዐርባ ቀናቸውም ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና በጥምቀት ተሰጣቸው። እግዚአብሔርም ለቅድስና ሥራ ስለመረጣቸው በእናታቸው ጀርባ ታዝለው ወደ ቤተክርስቲያን ሒደዉ በሕፃን አንደበታቸው ከቀዳሹ ካህን ጋር 'እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ' በማለት ይጸልዩ ነበር። በአደጉም ጊዜ ይህንኑ ጸሎት ደጋግመው ይጸልዩ ነበር። ሳባቸውም እስኪንጠፈጠፍ በመስገድ ይጋደሉ ነበር። አንድ ቀንም ከአባታቸው ጉን እንደተኙ በድንገት እግዚአብሔር በድምፅ 'ሀብተ ማርያም ሆይ! አንተን የተመረጠ ዕቃ አድርጌሃለሁና ቃሌን ለተጣመሙ ሰዎች ተናገር' አላቸው። ይህ ሁሉ የሆነው የቤተሰቦቻቸውን ከብቶች በእረኝነት ሲጠብቁ በነበረ ጊዜ ነው። ዕድሜያቸው እየገፋ በመጣ ጊዜ አባታቸው እረኝነቱን አስትተዋቸው ወደ ትምህርት ቤት አስገቡአቸው። ለአቅመ አዳምም በደረሱ ጊዜ ሚስት አጩላቸው፤ እርሳቸው ግን የድንግልናን ሕይወት በመምረጥ ከወላጆቻቸው ቤት ኮብልለው ገዳም ገቡ። በዚያም አባ ሳሙኤል ስተባሉ አባት በረዳትነት ሲያገለግሉ ብዙ ገቢረ ተአምራት ተደርጉላቸዋል። ዛሬ ይሰበይ ገዳም ተብሎ በሚጠራው ሥፍራ ለሦስት ወራት ጽሙድ እንደበሬ ትጉህ እንደገበሬ እንዲሉ በጾም በጸሎት ተጠምደው ሳለ መታሰቢያህን በዚህ ዋሻ አደርግልሃለሁ ብሎ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። ጊዜ ዕረፍታቸውም በደረሰ ጊዜ ጌታ ተገልጦ ስለ ተጋደሉአቸውና ስለንጽሕናቸው ሰባት አክሊላት እንደሚቀበሉ ነግሯቸው በ፲፬፻፹፱ ዓ.ም ኅዳር ፳፮ ቀን ዐርፈው በደብረሊባኖስ ገዳም መካነ ቅዱሳን ቀበሯቸው። /ምንጭ:- ሐመር መጽሔት ፱ኛ ዓመት ቁጥር ፫/

ረ. አባ ኢየሱስ ሞዓ (፲፪፻፲፩-፲፪፻፺፪)



[illegible]

አባ ኢየሱስ ሞዓ ከአባታቸው ከዘክርስቶስና ከእናታቸው ከእግዚእክብራ በጎንደር ክፍለ ሀገር ስማዳ ወረዳ ዳኅና በሚባል ቦታ በ፲፪፻፲፩ ዓ.ም ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ ለሠላሳ ዘመን ያህል በቤተሰቦቻቸው ዘንድ ትምህርተ ሃይማኖትንና ግብረ ገብን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በ፲፪፻፵፩ ዓ.ም ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም በምናኔ ገቡ። በዚያም መነኮሳቱን እየረዱና ቅዱሳት መጻሕፍትን እየገለበጡ መደበኛ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ለ፱ ዓመት ከቆዩ በኋላ በ፲፪፻፵፱ ዓ.ም ከገዳሙ ፫ኛ አበምኔት ከአባ ዮሐኒ መዓርገ ምንኩስናን ተቀበሉ። ከዕለታት በአንድ ቀንም ቅ/ገብርኤል ተገልጾ ገድላቸውና ትሩፋታቸው በዓለም ሕዝብ ሁሉ እንደታወቀ ነግሯቸው 'የስምህ መከበሪያ ወደ ሆነው ሐይቅ ወደ ተባለው ሥፍራ ሂድ' ብሏቸው መንገዱን እየመራ የብዙ ወራት የሆነውን ጉዞና በስድስት ሰዓት ፈጽሞ ከሐይቅ አድርሷቸው ተሰወረ። በዚያን ጊዜ ከሐይቅ ገዳም በስተሰሜን አቅጣጫ ከሚገኘው የጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስቲያን ለስድስት ወራት ቀን ሕዝቡን ሲያስተምሩ በመዋል ሲመሽ ወደ ሐይቁ በመግባት ሲጸልዩ ያድሩ ነበር። ከዚህ የተነሣ በሐይቅ እስጢፋኖስ አካባቢ የሚኖሩ መነኮሳት ማታ ማታ የብርሃን ዓምድ ወደ ባሕሩ ሲገባ ግሎዳ ደግሞ ሲወጣ ያዩት ነበር። በዚህ ዓይነት ክብራቸው የተገለጠው አባት በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድና በገዳሙ አባቶች ተማፅኖ የገዳሙ አበምኔት ሁነው ተሾሙ። አርባ አምስት ዓመት በቆየው ዘመነ ሲመታቸው ልዩ ልዩ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጻፍና በማሰባሰብ አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ቤተ መጻሕፍት በገዳሙ አቋቁመዋል። እንዲሁም የመጀመሪያውን ቋሚ የአብነት ትምህርት ቤት በማቋቋም ስምንት መቶ መነኮሳትን በትምህርተ ሃይማኖት አንፀው በገቢረ ዕድንት መዓርግ በመላው ሀገሪቱ አሠማርተዋል። ከነዚህም መካከል አቡነ ተክለሃይማኖት፣ አቡነ ሂሩተአምላክ አቡነ በጸሎተሚካኤል፣ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫና ሌሎችም ይገኙባቸዋል። በወቅቱ የነበሩትንም ንጉሥ አጼ ይኩኖ አምላክን በትምህርተ ሃይማኖት ያነጿቸው እርሳቸው ናቸው። በዮዲት ጉዲት ዘመን ተጉሳቁላ የነበረችውን ቤተክርስቲያን ዳግም ወንጌለ ብርሃን እንዲበራባት ገዳማትና አብያተ ትምህርት እንዲስፋፉ ያደረጉት እኒህ አባት ናቸው። አባታችን አቡነ ኢየሱስ ሞዓ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ለአርባ አምስት ዓመታት ከኖሩ በኋላ በዕለተ እሑድ ኅዳር ሃያ ስድስት ፲፪፻፺፪ ዓ.ም በ፹፩ ዓመታቸው ዐርፈው በዚያው ብዙ ትሩፋትና ገድል በፈጸሙበት ገዳም በክብር ተቀብረዋል። /ምንጭ:- ሐመር ፱ኛ ዓመት ቁ. ፪/

ሰ. አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ (፲፬ኛ መቶ ክ/ዘመን)

ጻድቁ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ በዋድላና ደላንታ አውራጃ በዳውንት ወረዳ ደብረ እስጋጅ በተባለ ቦታ ከአባታቸው ከካህን መልአክ ከእናታቸው ከወለተማርያም በታኅሣሥ ፰ ቀን ተወለዱ። ዐርባ ቀን ሲሞላቸው ጥር ፲፮ ቀን በጥምቀተ ክርስትና እስትንፋሰ ክርስቶስ ተባሉ። ከአባታቸው ቤት በሥነ ሥርዓት አድገው ሰባት ዓመት ሲሞላቸው አባታቸው ኪራኮስ ወደ ተባሉ መምህር ወስደው አስረከቡአቸው። በዚያም ንባብና ዳዊት ብሉያትንና ሐዲሳትን ተምረው ወደ ቤተሰቦቻቸው ተመለሱ። አባቶቻቸውም ወደ ጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ወስደው ዲቁና እንዲቀበሉ በማድረግ ለተወለዱበት

ለእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ሆነው እንዲያገለግሉ ሰጧቸው። በዚያም ለብዙ ዘመን በፍጹም ትሕትና ሲያገለግሉ ቆይተው ከትውልድ ሀገራቸው መንነው ወደ ደሴተ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሔዱ። ከዚያም ያለ ታንኳ ባሕሩን ተሻግረው በቤተ ክርስቲያን ምስጋና ለፈጣሪያቸው አቅረበዋል። በዚያ የሚኖሩ መነኮሳትም ያለ ታንኳ መሻገራቸውን አድንቀው ሰላምታ ካቀረቡላቸው በኋላ ከገዳሙ አበምኔት ጋር አገናኙተዋቸዋል። በዚህ ገዳም ለመመንኮስ እንዳሰቡ አበምኔቱ አውቀውባቸው መጽሐፈ መነኮሳት እንደሚያዘው ሦስት ዓመት በረድነትና በብሕትውና ከቆዩ በኋላ መልካም ትሩፋታቸውና ምግባራቸው ተመርምሮና ተጠንቶ በቅድስና የምታበቃውን የምንኩስናን መዓርግ ሰጧቸው። ቀጥለውም የቅስና የቁምስና መዓርጋትን ከጳጳሱ ከአቡነ ማርቆስ ተቀብለው በገዳሙ ሊቀ ዲያቆን፣ መጋቢና (የሚመግብ) ሊቀምርፋቅ (የምግብ ቤት አለቃ) በመሆን በጠቅላላው ለአሥራ አንድ ዓመት ከአገለገሉ በኋላ ወደ ሸዋ ምድር ወጥተው ወንጌል እየተዘዋወሩ አስተማሩ። አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰዎችን አሳምነው በማጥመቅ ሰባት አብያተ ክርስቲያናትን አሳንፀዋል። ለዐርባ ቀንም በዝቋላ ገዳም ሱባዔ ገብተው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተገልጸው ካነጋሯቸው በኋላ ተሠውረዋል። በዚህም የቅድስና ሥራቸው በእግዚአብሔር ቸርነት በቅዱስ ገብርኤል የምሥራች ነጋሪነት ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እንዲሔዱና ቅዱሳት መካናትን እንዲሳለሙ ተፈቅዶላቸው ሐደው ተሳልመው ሲመለሱም እጽፋቸውን በባሕር ላይ ዘርግተው በመጸለይ ያለ መርከብ ወደ እርማንያ ደሴት በመሻገር ከአቡነ ኤዎስጣቴዎስ መቃብር ላይ ጸልየው ወደ ግብፅ በመውረድ ገዳመ አስቄጥስን፣ መቃብረ እንጦንስንና በእስክንድርያ መንበረ ማርቆስን ተሳልመው ወደ አክሱም በመመለስ በኢትዮጵያ የሚገኙ ታላላቅ ገዳማት በመዞርና በመሳለም ድውይ ፈውሰዋል፣ ለምጽ አንጽተዋል፣ ዕውር አብርተዋል፣ መናፍስት ርኩሳንን አባርረዋል። ከዚህ በኋላ ዘመነ ዕረፍታቸው እንደደረሰ መልአክ እግዚአብሔር ነግሯቸው ተወልደው ወደ አደጉበት ወደ ዳውንት ተመልሰው ደብረ እስጋጅ በሚባል ቦታ ብዙ መነኮሳትን

ሰብስበው በማስተማር ይቀመጡ ጀመር:: ከዚህ በኋላ ከዚህ ዓለም የሚለዩበት ሲቃረብ የሚያርፉበትን ሰዓቱንና ዕለቱን ወሩንና ዓመቱን ለይቶ መልአኩ በነገራቸው መሠረት የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸውን ሰብስበው በነፍስ በሥጋቸው የሚጠቀሙበትን በማስረዳት ከመከሩአቸው በኋላ ሚያዝያ ሁለት ቀን ታመሙ፤ ከፈጣሪያቸውም እስከ አሥራ ሰባት ትውልድ ድረስ ዓሥራተ ምሕረት (የምሕረት ቃልኪዳን) ተቀብለው ሚያዝያ ዘጠኝ ቀን በዕለተ ዓርብ በሰማንያ ዘጠኝ ዓመታቸው ዐርፈው በደብረ አስጋጅ ገዳማቸው ተቀብረዋል:: በመቃብራቸውም ላይ የሃያ ዐራቱ ካህናተ ሰማይ ታቦት ተተክሎበት በመቃብሩ አፈርና ቆመው በጸለዩበት ቦታ በፈለቀው ጠበል ብዙ ድውያን ሥጋ እየተፈወሱበት ይገኛል ገድላቸውንም አባ አካለ ክርስቶስ የተባሉ ቅዱስ መነኩሴ ጽፈውላቸዋል:: /ምንጭ፡- ትንሣኤ መጽሔት ቁ.፲፯ ፲፱፻፹ ዓ.ም/

ሸ. አቡነ ተስፋ ኢየሱስ

እቡነ ተስፋ ኢየሱስ ኢትዮጵያዊ የተባለው ጻድቅ አባቱ ልውለ ቃል እናቱ ትርሲተ ወልድ ይባላሉ:: የአቡነ ዘርዓ ብሩክ ዝግሽ አባይ ታላቅ ወንድም ነው:: ትውልድ መንደሩ ጎጃም አሬት ዘኔ ማርያም ሲሆን እርሱም ወንድሙም የተወለዱት በብሥራተ መልአክ ነው:: አቡነ ተስፋ ኢየሱስ በመልአክ እግዚአብሔር መሪነት ጣና ሐይቅ ገዳም ገብቶ በዚያ ሥርዓተ ቀኖናን ተማረ:: የዋሸራን ገዳም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከመሠረቷት ፫፻ መነኩሳት ተመርጦ ሰኔ ፳፩ ቀን ተሹሞአል:: ከዚህ በኋላ ስለዋሸራ ገዳም ታላቅነትና ስለ ሕዝበ ክርስቲያኑ ደኅንነትና ጽኑ እምነት እንዲሁም ብዙ ሀብተ ሥጋና ሀብተ ነፍስ እንደሚገኝባት ገዳሟ ያለ ዕለተ ምጽአት እንደማትፈርስና ለዚህም ሕዝቡ በየጊዜው ሱባኤ እየገባ እግዚአብሔርን ቢለምን ሁሉም ነገር እንደሚፈጸምለት ተነግሮታል:: ጻድቁ የመሠረተውና የሚኖርበት ገዳሙ በባሕር የተከበበ ስለነበር እርሱ ቢባርከው እንደ ጠበል ሆኖለታል:: ገዳሙም በዋሽራ ይገኛል ዕረፍቱም ጥር ፳፩ ቀን ነው::

ቀ. አቡነ መድኃኒ እግዚእ

አቡነ መድኃኒ እግዚእ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ሀገሩ ትግራይ አዲግራት አካባቢ ልዩ ስሙ እንደዳ ማርያም ከተባለ ሥፍራ መጋቢት ፳፯ ቀን ተወለደ:: አባቱ ቀሲስ ሰንበት ተስፋነህ እናቱ ሂሩተ ማርያም ይባላሉ:: ደጋጐች ክርስቲያኖች ሲሆኑ አባቱ በተለይ ንጹሕና እውነተኛ ካህን ነበር:: ይህ ጻድቅ አቡነ መድኃኒ እግዚእ የደብረ በንኮልን ገዳም የመሠረተ የአቡነ አረጋዊ አራተኛ የቆብ ልጅ ነው:: ጻድቁ ሦስቱን ሳሙኤል ማለትም የዋልድባውን፣ የጣራጣውንና የቆየጻውን በአንድ ጊዜ ያመነከሰ ቀደምት አባት ነው:: ደብሩ ደብረ በንኮልም ሙራደ ቃል እየተባለ ይጠራል:: ጻድቁ በዘመኑ ችግር ረሀብ ሆኖ ለመናንያኑ ውኃ ቀድቶ የሚያጠጣ በመጥፋቱ እንበሳን ሰባት ዓመት ውኃ በትእዛዝ ያስቀዳ አራዊት ሁሉ በጸሎቱ የተገዙለት ታላቅ አባት ነው:: ገዳሙም ዛሬ ከስድስት መቶ ዘመን በላይ አስቆጥሯል:: በዚህ ገዳም ሩባሰዊት የተባለ በጣም አስደናቂና ገባሬ ተአምራት የሆነ ጠበል አለ:: በጻድቁ ተባርኮ የፈለቀና ዛሬም ቃል ኪዳኑ ያልተሻረ ነው:: ለአእምሮ በሽተኛና ርኩስ መንፈስ ያደረበትን ሰው ለማዳን ቃል ኪዳን የተሰጠው ነው:: በጻድቁ ገዳም መናንያንና መነኮሳት በአንድነት ኑሮ ያለመበላለጥና ያለመለያየት ይኖራሉ:: ጻድቁ በተወለደ በ፻፹ ዓመቱ በኅዳር ፫ ቀን ዐርፎ በዚሁ በመሠረተው ቦታ ተቀብሯል:: በስሙም በሀገራችን አምስት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ::

በ. አቡነ ዐሥራተ ማርያም

አቡነ ዐሥራተ ማርያም ኢትዮጵያዊ ትውልድ ሀገሩ ጎጃም ጎዛምን ወረዳ ልዩ ስሙ ጨሰባታ ማርያም ከተባለ ሥፍራ ነው:: አባቱ አምኃ ኩሩ እናቱ ወለተ ማርያም ይባላሉ:: በተወለደም ጊዜ በወላጆቹ ቤት ብርሃን ወርዶአል:: በዚህም ምክንያት ይህ ሕፃን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው እያለ ሕዝቡ በአንክሮ ይመለከቱትና ይጠብቁት ነበር:: ይህ ጻድቅ በምድረ ኢትዮጵያ ዞሮ ያላገለገለበት ገዳም የለም:: ወደ ምናኔ ዓለም ሲገባም ወላጆቹ ሀብታም ስለነበሩ የአባቱ ንብረት ሳያሳሳው ሁሉን ንቆና ትቶ ነው:: በተወለደበትም ቦታ መካነ ቅዱሳን አቡነ ዐሥራተ ማርያም የሚባል የአንድነት ገዳም አለ:: ይህን ቀድሞ የመሠረቱት ጻድቅ አቡነ መዝሙር የተባሉ ሲሆኑ ገዳሙ ጠፍ ከሆነ ከ፰፱ ዓመት በኋላ አቡነ ዐሥራተ ማርያም አቀኑት:: አሁን ገደሙ የሚጠራው በርሳቸው ስም ነው:: በዚህም ገዳም የሚያስደንቅ ጠበል ያገኛል:: ይህ ታላቅ ጻድቅ በተወለደ በአንድ መቶ ዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን አርፎ በራሱ ገዳም ተቀብሯል::

ተ. አቡነ ገብረ ክርስቶስ ዘትግራይ

አቡነ ገብረ ክርስቶስ ዘትግራይ ኢትዮጵያዊ አባቱ አጼ ካሌብ እናቷ ሥምረተ ክርስቶስ ይባላሉ:: ይህ ጻድቅ መጽሐፈ ገድሉ "መናኔ መንግሥት ቀብአሲት ከመ ገብረ ክርስቶስ ዘአርማንያ" ይለዋል:: አባቱ አጼ ካሌብ መንግሥቱን ወርስህ ንግሥና ተቀመጥ ቢለው ጻድቁ አባቱን ይህ ያንተ መንግሥት ያልፋል፤ ይቀራል፤ ንብረትም ያልቃል፤ ይጠፋል፤ የማያልፈውና ሽረት እልፈት የሌለበት የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ስለሆነ እኔ የዚህን ኃላፊ ዓለም መንግሥት አልፈልግም ብሉ ትቶና ጠፍቶ ደብረ ዳሞ ገዳም ገባ:: በዚህም ገዳም ፮ ዓመት ከኖረ በኋላ በ፳፩ ዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በአቡነ ጸንጠሌዎን እጅ መነከሰ:: ሥርዓተ ገዳማትን ቀኖና ሃይማኖትን በሚገባ ተማረ:: እንዲሁም የሐዲሳትንና የብሉይ መጻሕፍትን ጠንቅቆ አወቀ:: ይህ ጻድቅ በተወለደ በ፹፯ ዓመቱ ዐርፎ ራሱ በመሠረተው አክሱም አካባቢ ከአባ ጸንጠሌዎን ገዳም አጠገብ በስሙ በሚጠራው ቤተክርስቲያን ተቀብሯል::

ቸ. አቡነ ያፌቅረነ እግዚእ

አቡነ ያፌቅረነ እግዚእ የተባለው ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ትውልድ ሀገሩ ትግራይ አክሱም ልዩ ስሙ ሀገራይ ሲሆን ሐምሌ ፲፱ ቀን ተወለደ:: አባቱ ገብረ ኢየሱስ እናቱ አፎምያ ይባላሉ:: ሰባ ሁለቱ ዐበይት ቅዱሳን ተብለው ከሚጠሩት አንዱ ነው:: ይህ ጻድቅ በአንድ ዓመት ዕድሜው በሊቀ ጳጳስ ተባርኮ ካደገም በኋላ ዘመሉ ከተባለ ቦታ ሄዶ ተማረ:: ይህ ጻድቅ በሕይወቱ ከሚታወቅበት ታሪክ አንዱ ማኅበረ ዶጊ(ጉዱ) በመባል የሚታወቀውን የሦስት ሺህ ቅዱሳን አንድነት ማኅበር የተመሠረተበትን ገዳም መቆርቆሩ ነው:: በዚህ ገዳም ውስጥ ከሰማይ የወረደው ጌታችን ከ፲፫ ቅዱሳን ጋር ማኅበር የጠጣበት ጽዋ ይገኛል:: እንዲሁም መጽሐፈ እልፍ ሰማንያ የተባለው አስደናቂ መጽሐፍ ይገኛል:: አቡነ ያፌቅረነ እግዚእ ከደራ ፎገራ ተነሥቶ በጣና አድርጐ ፈላሾችንና ቅማንቶችን በሚገባ ያስተማረና አሳምኖ በማጥመቅ የተከበረ ታላቅ ጻድቅ ነው::

በአክሱም በናዕጽር ቀበሌ ውስጥ ንጉቤን ከተባለው ቦታ ታላቅ ገዳም መሥርቶ በጥር ፲፱ ቀን ዐረፈና በዚያው ተቀበረ::

ኀ. አቡነ ገብረ ኢየሱስ

አቡነ ገብረ ኢየሱስ የተባለው ጻድቅ በትውልዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ገዳማተ ግብፅን ለመጐብኘት ተነሥቶ በመሄድ ወደ አባ መቃርስ ገዳም ገባ:: ከዚያም ወጥቶ በአባ ዮሐንስ ሐጺር ገዳመ ታርም ገባ:: በዚያም ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር ተሰጠው:: ግብፃውያኑም በዚህ በጣም ቀኑበት:: የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ቄርሎስ በሞተ ጊዜ ግብፃውያን ማንን እንሹም ብለው በኃዘን አባ ገብረ ኢየሱስን ጠየቁት:: እርሱም አትዘኑ በመካከላችሁ ስመ ገብርኤል የተባለ ጻድቅ ይገኛልና እሱን ሹሙት አላቸው:: እንዳላቸውም አደረጉ:: ይህ ጻድቅ እጅግ ብዙ ሚስቶች የነበሩትን የግብፅ ንጉሥ በድፍረት ቀርቦ በማስተማር በአንድ ሚስት እንዲፀና አደረገ:: ይህ ጻድቅ ሰኔ ፲፩ ቀን ዐርፎ በገዳመ ቁስቋም ተቀብሯል:: ቅዱስም ተብሎ ታቦት ተቀርጾለታል::

ነ. አቡነ ተክለ አልፋ

አቡነ ተክለ አልፋ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ሀገሩ ሸዋ ይፋት ሲሆን ተክለ አልፋ ዘደብረ ድማህ እየተባለም ይጠራል:: አባቱ ካህን አሮን ይባላል:: ተክለ አልፋ የስሙ ትርጓሜ ለዘለዓለም የሚኖር ድንቅ ሥራ ማለት ነው:: እርሱም ታኅሣሥ ፰ ቀን ተወለደ:: ይህ ጻድቅ ሰባ ሁለቱ ዐበይት ቅዱሳን ከሚባሉት ፲፩ኛው ነው:: በዘመኑም የነበረው ንጉሥ አጼ ይስሐቅ ይባላል:: በደብረ ድማህ ገዳም አበምኔትነት ተመርጦ ፲፫ኛ በመሆን አገልግሎአል ጻድቁ እንዲት ገባሬ ተአምራት የሆነች መቋሚያ የነበረችው ይህች መቋሚያ እሙ መሳድ የተባለችውን የሴቶችን ማኅፀን በማክሸት የታወቶችውን የዛር መንፈስ እንደዝንብ አብርራ አጥፍታለች:: በዚህ የተነሣ ዛሬ በዲማ የዚህ ታላቅ አባት ጸሎት ታላቅ መማጸኛ ሆኗል:: ጻድቁ በ፹፭ ዓመቱ ታኅሣሥ ፰ ቀን በተወለደበት ዕለት ሲያርፍ ያች መቋሚያ ያው መሞቱን ለገዳሙ መነኮሳት ተናገረች:: ከዚህ በኋላ በተሾመበትና ፵፭ ዓመት በአገለገለበት በደብረ ድማህ ተቀብሯል::

ኘ. አቡነ በርተሎሜዎስ

አቡነ በርተሎሜዎስ ኢትዮጵያዊ የተባለው ጻድቅ ትውልድ ሀገሩ ሸዋ ቡልጋ መጋቢት ፫ ቀን ተወለደ:: አቡነ ተክለሃይማኖት ከሾሙአቸው ፲፪ቱ ንቡራነ ዕድ ውስጥ አንዱና ሹማግሌው ይህ ጻድቅ ነው:: የማዕጠንት ወር ተራውም በዳንሜን ስለነበር ደብረ ሊባኖስን ያጥን ነበር:: ሀገረ ስብከቱም የቆቦ የጠጠራና የኩረም ኢጲስ ቆጶስ ተብሎ ተሾመ:: ታላቋንና ባለታሪኳን በወሎ ላስታ ውስጥ የምትገኘውን ደብረ ዘመዶ የተባለችውን ገዳም የመሠረተ አባት ሲሆን ይህች ደብረ ዘመዶ የተባለችውም ቦታ ዮናስ በተባለ ደግ ገበሬ ሚስት ስም የተሰየመች ልዩ ትርስና ባለታሪክ ቦታ ነች:: በዚህ ገዳም ከዓመት እስከ ዓመት ሰዓታትና ቅዳሴ አይታጐልበትም:: ጨቅጨቅና ጨበርታ የተባሉ ሁለት የማይ መቅጃ ጠበሎች አሉአት:: ሉቃስ የሣላት ሥዕለ አድኅኖ ከኢየሩሳሌም ዮሐንስ የተባለ ጻድቅ ያመጣት በዚሁ ገዳም ትገኛለች:: የዚህች ገዳም ዋነኛ ዘብ ድኩላ ሲሆን አካባቢውም በአውሬ የተከበበ ገዳም ነው:: ጌታችንም ለጻድቁና ለቦታዋ ቃል ኪዳን ገብቶለታል:: ጻድቁ ጥቅምት ፫ ቀን ዐርፎ በዚሁ ገዳም ተቀብሯል::

አ. አቡነ ሐራ ድንግል

አቡነ ሐራ ድንግል ኢትዮጵያዊ የስሙ ትርጉም ታማኝ ወታደር ማለት ነው:: አባቱ ዮሐንስ እናቱ ወለተ ጊዮርጊስ ይባላሉ:: የተወለደውም ጥር ፲፩ ቀን ነው:: የትውልድ ሀገሩም በቤጌምድር በደብረ ታቦር አውራጃ በደራ ወረዳ ነው:: የጻድቁ አባት ላንና በተባለ ቦታ ልዩ ስሙ ራማስ በተባለው ሀገር ሊቀ ካህናት ነበር:: ጻድቁ የሚታወቅበት አንድ ታሪክ አለው:: እርሱም ማርያም ባርኪ የተባለውን ግብር የሚሰበስበለት የማነ ብርሃን የተባለ እህያ ነበረውና ካንገቱ ላይ ቃጭል ተደርጉበት ማንም ሰው ሳይከተለው እህያው ራሱ እየዞረ በየአውድማው ይሰበስብና ለገዳሙ ያመጣ ነበር:: ከዕለታት አንድ ቀን እህያው አርጅቶ ሲሞት አቡነ ሐራ ድንግል አዝኖና አልቅሶ በእጁስ ጨርቅ ገንዞ ቀብሮታል:: ከዚያም ከተቀበረበት ሥፍራ ጠበል ፈልቆ ሙት አስነስቷል፤ እውር አብርቷል:: ዛሬም ያ ጠበል ይዘቱን ሳይቀይር ፈውስ እያደረገ ይገኛል:: የሥጋ ደዌ በሽታ ያለበትም የጠበሉን አፈር (ጭቃ) እየቀባ ከደዌው ይፈወሳል::



አቡነ ሐራ ድንግል [illegible]

ጻድቁ በብዙ ተጋድሎ ቆይቶ በተወለደ በ፹፰ ዓመቱ ግንቦት ፲፭ ቀን ዐርፎ በባሕር ጻርና በወረታ መካከል ባለ ራሱ በቆረቆረው ገዳም ተቀብሯል:: በተቀበረም ጊዜ ፯ ቀን ቀስተ ደመና ተተክሎ ብርሃን ወርዷል::

ከ. አቡነ ዮሴፍ

አቡነ ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ አባቱ አጼ ዳዊት እናቱ ዳግም ሞገሳ ይባላሉ:: ትውልድ ሀገሩ ወሎ መቂት እንጂፋት ሲሆን ኅዳር ፲፮ ቀን ተወለደ:: በተወለደም ጊዜ ፲፫ ሙታን ተነሥተዋል:: ይህ ጻድቅ ያልገባበት ገዳምና ያላየው የቅዱሳን ቦታ የለም:: በኋላም በብቃቱ ይህ ጻድቅ ከዕለታት በአንደኛው ቀን ዝንጀሮዎች ተሰብስበው መጡና እጅ ነሱት:: ጻድቁም አምላኩን እነዚህን ሁሉ ምን አበላቸዋለሁ ብሎ ጠየቀ:: ጌታችንም አንተን ያጅቡ፤ ቅጠሉንና የእህሉን ቃርሚያ ይብሉ ብሎ አዘዘው:: በአንድ ወቅትም ረሀብ ሆኖ እርሱን ተከትለው መንገድ ሲሔዱ ውለው ራበን ቢሉት ጻድቁ ድንጋዩን ባርኮ ለውጦ ሥጋ አድርጐ መገባቸዋል:: በላስታ አውራጃ በግዳን ወረዳ ልዩ ስሙ ወለቃ ከተባለው ቦታ ገዳሙን መሠረተ:: በዚህ አካባቢ እህል የሚትረፈረፍበት ቦታ ስለሆነ ዝንጀሮዎቹ የሰውን እህል እንዳይበሉ ሰውም የእህሉን ቃርሚያ እንዳያገኝ ለዝንጀሮዎቹ እንዲተውላቸው ለጻድቁ ጌታ ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል:: እንዲሁም አካባቢው ዋና የአባብ መንጋ መፈልፈያ ሲሆን ከአቡነ ዮሴፍ ገዳም ክልል ሲገቡ እባቡ ሰውን አይተናከልም:: ጻድቁ ፫ ጊዜ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቀድሶ ተመልሷል:: በእጁም አባ ሚካኤል አባ ዘማርያም አባ ቅዱስ አምላክ የተባሉ ቀደምት አበው አመንኩሶ ለቦታው ተተኪ አድርጓል:: በዚህ ሁኔታ በአጼ በዕደ ማርያም ዘመን በጸሎት ላይ እንዳለ በተወለደ በ፻፫ ዓመቱ ግንቦት ፲፱ ቀን ዐርፎ በወለቃ ገዳም ተቀብሯል:: በስሙም አምስት ቤተክርስቲያናት ተተክለዋል::

ኸ. አቡነ አምኂ ዘናህሶ

አቡነ አምኂ ዘናህሶ ኢትዮጵያዊ የተባለው ጻድቅ በአክሱም የካቲት ፩ ቀን ተወለደ:: በተወለደም ጊዜ ሠይጣናት የወላጆቹን ቤት ከበቡ:: እሱም እንደተወለደ መንፈስ ቅዱስ ስለሞላበት (ስለአደረበት) በእጁ በትምህርተ መስቀል አምሳል ቢያመለክት በአንድ ጊዜ ፰ ሠይጣናት እንደጢስ በንነው ጠፍተዋል፤ ተሸንፈዋል:: ስለዚህ አምኂ ተብሏል አሸናፊ ማለት ነው:: ይህ አባት በሰኔ ፩ ቀን በአባ ክርስቶስ ቤዛ እጅ መነከሰ:: በኋላም ለ፯ ዘመን የሰው ፊት ሳያይ የኖረና ከመላእክት ጋር ያመሰገነ አባት ነው:: ይህ ጻድቅ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ደብረ ዘይት ከአባ አብሱይ ጋር የተገናኘ አባት ነው:: ከአባ ዮሐኒና ከአባ አበጊዶ ጋር ፰ ዓመት ኑሮአል:: በስሙ የተሠራው ገዳም በትግራይ ተምቤን ደብረ ዓሣ እየተባለ ይጠራል:: የዚህም ምክንያት ተራራው የዓሣ ቅርፅ ያለው በመሆኑ ነው:: ጻድቁ ተጋድሎውን በመልካም አርጅና ፈጽሞ በተወለደ በ፻፭ ዓመቱ ኅዳር ፩ ቀን በገዳሙ ዐርፎ በዋሻ ውስጥ ተቀብሯል::

ወ. አቡነ አካለ ክርስቶስ

አቡነ አካለ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ትውልድ ሀገሩ በጌምድር እስቴ ወረዳ ሳጋ ወለተ ጴጥሮስ ሲሆን አባቱ ንባውዴዎስ እናቱ ወለተ አዳም ይባላሉ:: ይህ ጻድቅ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በልደተ እግዚእ ተወለደ:: በተወለደ ጊዜም ሙት አስነስቷል:: በአደገም ጊዜ ከአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ዘንድ በመሄድ ቀኖናተ ቤተክርስቲያንን በሚገባ ተምሮ በ፳፩ ዓመቱ በሐይቅ ገዳም መንኩሶአል:: ከዚያም በመመለስ ራሱ በቆረቆራት በጋይንት አውራጃ በዞጋ ቀበሌ በምትገኘው ምዕራፈ ቅዱሳን ገዳም ከአንድ ቦታ ሳይንቀሳቀስ የወይራ ዛፍ ተደግፎ ፺ ዓመት ሙሉ በመጸለይ ከፈጣሪው ጋር ተገናኝቷል:: ያች ዛፍ ዛሬም በገዳሙ ተከብራ ትገኛለች:: እንዲሁም በዚሁ ገዳም ጻድቁ በእጁ የሚይዛት ሙት የምታስነሳ እንደሰው የምታነጋግረው መቋሚያው ዛሬም ተአምር ትሠራለች:: ቤተመቅደሱ ሳይታጠን የቀረ እንደሆነ ወይም ሊያቆኑ መብራት ሳያጠፉ የሄደ እንደሆነ እንደሰው እፍ አውጥታ ታቃጭላለች:: አንዳንድ ጊዜ ትሠወራለች ይባላል:: አሁንም በክብር ትገኛለች:: ዘካርያስ የተባለ በስሙ አላላች የሆነ ጣዖት አምላኪ ለጣዖት አልሰገድክም በሚል ምክንያት ጻድቁን አሥሮ በአምስት ችንካር ቸንክር እጅግ ባሰቃየው ጊዜ አምላክ ቅዱሳን እንደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጽና ብሎ እንዳነጋገረውና ሰፊ የሆነ ቃል ኪዳን እንደሰጠው ገድሉ ይናገራል:: ከዚህም ቃል ኪዳን ውስጥ በገዳም አካባቢ የሚገኙ አባቦችና ልዩ ልዩ መርዛማ አውሬዎች የጻድቁን ስም ከጠሩባቸው አይተናከሉም:: ድንገት እባብ የነደፈው ሰው ሄዶ ጠበሉን ከጠጣና አፈሩን ከተቀባበለ ፈጥኖ ይድናል:: አእምሮውን የነሳው ሰውም ካለ በአቡነ አካለ ክርስቶስ መቋሚያ ፯ ቀን ከተሻሸ ወደ ጤንነቱ ይመለሳል:: በዚህ ዓይነት አንጋፋ ከተባሉት ቅዱሳን አበው አንዱ የሆነው አቡነ አካለ ክርስቶስ በተወለደ በ፻፲፬ ዓመቱ ጥር ፲፱ ቀን ዐርፎአል:: በዚህ ቀንም ሙታን ተነሥተዋል:: ልዩ ልዩ ተአምራት ተደርጓል::

ዐ. ቅድስት አመተ ክርስቶስ

ቅድስት አመተ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊት ትውልድ ሀገሯ ትግሬት ሲሆን በተጋድሎዋ የጸናች እናት ናት:: ነሐሴ ፰ ቀን ተወለ

ደች። ለዐርባ ስምንት ዓመት ያህል ሳትንቀሳቀስ ቆማ እንደ አቡነ ተክለሃይማኖት የጸለየች ባለታሪክ ናት። መጽሐፍ ስለ እርሷ ሲተርክ ፍጹም ተሐራሚትና ገዳማዊት እንደነበረች ይገልጻል። አባ ፊንኤል የተባለ ጻድቅ ስለ እርሷ አጥብቆ የተናገረለት እናት ስትሆን የካቲት ፳ ቀን በመመንኮስ ግንቦት ፳፰ ቀን ዐርፋለች። በስሟ አንድ ገዳም በሀገራችን አለ።

ዘ. ቅድስት ሰባሲተ ክርስቶስ

ቅድስት ሰባሲተ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊት ሀገሯ ትግራይ ሲሆን በጾም በጸሎት ተጋድሎ የተመሰከረላት እናት ስትሆን በስሟ የተሠራ ቤተክርስቲያን በትግራይ እንደርታና በታሕታይ ተምቤን ይገኛል። ዕረፍቷም ሰኔ አሥራ አምስት ቀን ነው ትልቅ ጠበልም ፈልቆላታል።

ዠ. ቅድስት መክበበ ድንግል

ቅድስት መክበበ ድንግል ኢትዮጵያዊት ሀገሯ ትግራይ፣ በሰጋጅነቷ የተመሠከረላት ባሕታዊት እናት ስትሆን በስሟ በትግራይ ሽሬ ቃሕታይ አዳቦ ቤተክርስቲያን ተሠርቶላታል። ዐፅሟም በዚሁ ቤተክርስቲያን ይገኛል።

የ. ቅድስት እንተ ጴጥሮስ

ቅድስት እንተ ጴጥሮስ ሀገሯ ጎንደር ሲሆን በዳሞ ተራራ ሥር የኖረችና በኋላም ወደ ጎንደር መጥታ ከነ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ጋር በመሆን አላውያንንና ካቶሊካውያንን ስትከራከር ቆይታለች። ከዚህ በኋላም ደብረ ሞጊና ገዳም ሄዳ በገዳሙ ውስጥ ስትጸልይና ስትሰግድ ኑራ ዘመኑ የረሃብ የችግር ሆኖ የወረርሽኝ በሽታ በደብረ ዳሞና በማኅበረ ሥላሴ ገዳም ገብቶ መነኮሳቱ በመታመማቸውና በሞት በማለፋቸው ወደዚያው በመሄድ እየረዳችና እያስታመመች መነኮሳቱን ያዳነች እናት ናት። ይህ ሥራዋም በመላእክት የተመሠከረላት ድንቅ እናት ስትሆን በቀን ፳፪ ፳፫ ስግደትና ፳፪ አቡነ ዘበሰማያት ትደግም ነበረ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከመላእክት ጋር ስትነጋገር ኖራ በተወለደች በ፹፯ ዓመቷ ሐምሌ ፯ ቀን በካቶሊካውያን እጅ እጅግ ተሰቃይታ በሰማዕትነት የጽድቅ ሥራዋን ፈጽማ ዐርፋለች።

ሮ.ፌ. ሌሎች መናኞች

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከምትታወቅባቸው ልዩ ሀብታቷ አንዱ ምናኔ ነው።። የኢትዮጵያ ቆላማና በረሃ ቦታዎች ፍጹም ደጋዎችና ዋሻዎቿ ናቸው። አሁንም በመጋደል ላይ ያሉት እጅግ ብዙዎች እንደሆኑ የታመነ ነው።

ይሁን እንጂ የአንዱ ኮከብ ክብር ከሌላው ኮከብ ይበልጣል እንደተባለ ቅዱሳን ሁሉም በክብር አንድ አይደሉም። ጌታችንም በወንጌል አንዱ ሠላሳ አንዱ ስድሳ አንዱ መቶ ፍሬ አፈራ በማለት የገለጸው ይኸው የክብራቸውን መለያየት ለመግለጽ ነው። በዚህ ንዑስ ርእስ በሠንጠረዥ የምናቀርባቸው ቅዱሳንም በዚህ ጽሑፍ ዕይታ ከእነዚህ ከሦስቱ መዓርጋት በአንዱ የሚሆኑ ነገር ግን ስለቅድስናቸው ገድል ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው፣ ቅዱስ ተብለው ታቦት ይቀርጽላቸው አይቀርጽላቸው ማረጋገጫ ልናገኝላቸው ያልቻልናቸው ናቸው። ወደፊት ግን ከተሰጠው መረጃ በላይ ከአንባብያንም ሆነ ከሌሎች ሲገኝ ለመጻፍ ያመች ዘንድ በዚህ ርእስ በዚሁ መልክ ልንገልጻቸው ተገድደናል። ለዚሁ ሥራ የሚሆን መረጃ ሲገኝና ክብራቸውና መዓርጋቸው በትክክል እየታወቀ ሲመጣ ግን በዚህም ሆነ በሌላ መጽሐፍ ሊገለጽ ይችላል። ይህም ቅዱሳት እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑና ከመቶ ጠር በላይ መሆናቸውን ከማስረዳቱም በላይ በየጊዜው ቅድስት ቤተክርስቲያን በቀኖናዋ እየወሰነች ልታሳውቅ የሚገባት መሆኗንም የሚጠቁም ነው።

ተ.ቁ	የገዳሙ ስም	አጽመ ያረፈ ቦት	የትውልድ ሀገር	የተወለዱበት ቀን	ዕድ ሜው	የዕረፍት ቀን	ዘመን
[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]		-	-
[illegible]	[illegible]	-	ትግራይ	[illegible]		[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	-	-	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-
[illegible]	[illegible]	-	ትግራይ	[illegible]	-	-	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	-	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	-	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	-		[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	-	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]

ተ.ቁ	የገዳሙ ስም	አጽመ ያረፈ ቦት	የትውልድ ሀገር	የተወለዱበት ቀን	ዕድሜው	የዕረፍት ቀን	ዘመን
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	-
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	-	[illegible]	-
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	-
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	

ታሪካቸው በሰፊው ያልተጻፈ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ዝርዝር

ተ.ቁ	የገዳሙ ስም	አጽመ ያረፈ ቦት	የትውልድ ሀገር	የተወለዱበት ቀን	ዕድ ሜው	የዕረፍት ቀን	ዘመን
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	-	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	-	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	-	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ				
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]		[illegible]		[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]			[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]		[illegible]			[illegible]	
[illegible]	[illegible]		[illegible]		[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]		[illegible]			[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]			[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]			[illegible]	
[illegible]	[illegible]		ትግራይ			[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]			[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]				
[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]		[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]				[illegible]
[illegible]	[illegible]		[illegible]				[illegible]
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]			[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]		[illegible]				

ተ.ቁ	የገዳሙ ስም	አጽመ ያረፈ ቦት	የትውልድ ሀገር	የተወለዱበት ቀን	ዕድ ሜው	የዕረፍት ቀን	ዘመን
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]				
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]		[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]				
[illegible]	[illegible]	[illegible]					
[illegible]	[illegible]		[illegible]				
[illegible]	[illegible]	[illegible]				[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ				
[illegible]	[illegible]		[illegible]			[illegible]	[illegible]
[illegible]	[illegible]		[illegible]				
[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]		ትግራይ		[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]		ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]		[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	[illegible]	
[illegible]	[illegible]	[illegible]	ትግራይ	[illegible]		[illegible]	

መመሪያ I. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አራት አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ/።

፩. ቅዱስ ጀሮም የኢትዮጵያ ሐዋርያ በማለት የጠራው ማንን ነው?
ሀ. ኢትዮጵያዊ ጃንደረባን ለ. ሐዋርያው ፊልጶስን
ሐ. አቡነ ሰላማን መ. አቡነ ተክለሃይማኖትን

፪. የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ጳጳስ የሾመው፡-
ሀ. ቄርሎስ ለ. እለእስክንድሮስ
ሐ. አትናቴዎስ መ. ጎርጎርዮስ

፫. "አንቀጸ ብርሃን" የተሰኘውን የእመቤታችንን ምስጋና የደረሰው ማን ነው?
ሀ. ቅዱስ ያሬድ ለ. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ
ሐ. አቡነ ሰላማ መ. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ

፬. ከሚከተሉት ውስጥ ስለመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ፍሬምናጦስ ይባል ነበር። ለ. ከሣቴ ብርሃን ተብሎ ይጠራል
ሐ. ከሱርስት ጽርዕ እና ዕብራይስጥ ቋንቋ መጻሕፍትን ወደ ግእዝ ቋንቋ መልሷል /ተርጉሟል/
መ. እግዚአብሔርን ማመን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማረው እሱ ነበር

፭. ከሚከተሉት ውስጥ በትክክል ያልተዛመደው የቱ ነው?
ሀ. አባ አረጋዊ - ዘሚካኤል
ለ. አባ ገሪማ - ይስሐቅ
ሐ. አባ አቢብ - አባ ቡላ
መ. አባ ጉባ - አባ አሌፍ

፮. ከእንስት ቅዱሳት ውስጥ የማትመደበውን ለይ/ዪ/።
ሀ. ወለተ ጴጥሮስ ለ. ሐርቤ
ሐ. ፍቅርተ ክርስቶስ መ. ክርስቶስ ሠምራ

፯. በንግሥና ሕይወት ያሳለፈው ማን ነው?
ሀ. ካሌብ ለ. አብርሃ ሐ. ዜና ማርቆስ መ. ይምርሐነ ክርስቶስ

፰. የአቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ የቆብ አባት ማን ናቸው?
ሀ. አቡነ አረጋዊ ለ. አቡነ መድኃኒነ እግዚእ
ሐ. አቡነ ዐሥራተ ማርያም መ. አቡነ ያፌቅረነ እግዚእ

፱. በኢትዮጵያ ባሉት ገዳማት ተዟዙረው ያስተማሩ አባት፡-
ሀ. አቡነ ዐሥራተ ማርያም
ለ. አቡነ ተክለ አልፋ
ሐ. አቡነ ሐራ ድንግል
መ. አቡነ አካለ ክርስቶስ

፲. ከኢትዮጵያ ሐጼ የገባውን ንጉሥ የገሠጸ ጻድቅ፡-
ሀ. አቡነ በርተሎሜዎስ ሐ. አቡነ ተክለ አልፋ
ለ. አቡነ ተ/ሃይማኖት መ. አፄ ካሌብ

፲፩. አፄ ሱስንዮስ ምእመናንን በማስጨፍጨፉ ምክንያት ምላሱ ከተንሰነሰበት በኋላ ወደ ቦታው የመለሰለት አባት፡-
ሀ. አቡነ ሀብተ ማርያም ሐ. አቡነ ሙሴ ዘዲማ
ለ. አቡነ ተስፋ ኢየሱስ መ. አባ አምደ ሥላሴ

፲፪. ለዐርባ ዓመታት ያህል ሳትንቀሳቀስ ቆማ እንደ አቡነ ተ/ሃይማኖት የጸለየች እናት፡-
ሀ. ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ
ለ. ቅድስት አመተ ክርስቶስ
ሐ. ቅድስት ማርያም ዘደብረ ጽላልሽ
መ. ቅድስት እንተ ጴጥሮስ

መመሪያ II. በ"ሀ" ሥር ያሉትን ሐረጎች ከ"ለ" ሥር ጋር አዛምድ/ጂ/።

ሀ	ለ
፩. አሥራ አንድ ወቅር አብያተክርስቲያናትን ያነፀ	ሀ. አቡነ ጴጥሮስ
	ለ. ቅዱስ ሐርቤ
፪. የጸሎት ቦታቸውን ዝቋላ ያደረጉ አባት	ሐ. አባ አረጋዊ
፫. በፋሽስት ኢጣሊያ ሰማዕት የሆኑ	መ. ገብረ መስቀል
፬. መጽሐፈ ስዓታትን የደረሰው አባት	ሠ. ቅዱስ ላሊበላ
፭. በአፄ ሱስንዮስ ምክንያት ብዙ መከራን የተቀበለች ቅድስት	ረ. አቡነ ተክለሃይማኖት
	ሰ. ይምርሐነ ክርስቶስ

፮. የቅዱስ ላሊበላ ወንድም	ሸ. አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ
፯. በሰማያዊ መና ይተድስ የነበረ	ቀ. አጼ ካሌብ
፰. ሰዲያብሱስ ምሕረትን የለመነች	በ. መስቀል ክብራ
፱. ከእናታቸው ጋር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አባት	ተ. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ
፲. ዳግማዊ ኤልያስ በመባል ይታወቃል	ቸ. አቡነ ገሪማ
፲፩. ሞተሉሚን አስተምሮ ያጠመቀ	ነ. ነአኩቶ ለአብ
፲፪. የንግሥናውን ዘውድ ወደ ጎልጎታ ልኮ የመነነ	ኘ. አባ ኢየሱስ ሞዓ
	አ. ክርስቶስ ሠምራ
	ከ. አባ መብዐ ጽዮን

መመሪያ III. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች አሟሉ/ዪ/።

፩. ፀሐይን በጸሎታቸው ካቆሙ አባቶች ______ ና ______ ይጠቀሳሉ።

፪. አቡነ ተክለሃይማኖትን ያመነኮሱ አባት ____ ይባላሉ።

፫. አባ መብዐ ጽዮን ዓርብ ዓርብ ራሳቸውን ይገርፉ የነበሩት ___ ለማሰብ ነበር።

፬. ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን ሲደግሙ ከመሬት ከፍ ብለው ይጓዙ የነበሩ አባት ________ ይባላሉ።

፭. በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ከግራ ወደቀኝ የአጻጻፍ ስልትን የጀመሩት ______ ናቸው።

፮. አፄ ካሌብ ክርስቲያኖችን ለመርዳት ለውጊያ የሔደበት ሀገር _____ ትባላለች።

፯. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቤተመጻሕፍትና ዩኒቨርስቲ በ ______ አማካይነት የተከፈተው /የተመሠረተው/ ሲሆን ቦታው ___ ነበር።

፰. የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶች ___፣___፣___፣___ እና __ በመባል ይታወቃሉ።

መመሪያ IV. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ስጥ/ጪ/።

፩. የኢትዮጵያ ጃንደረባ ከጥምቀት በኋላ በነበረው ዘመኑ ያከናወናቸውን ዐበይት ተግባራት ዘርዝር/ሪ/።

፪. ኢዛናና ሳይዛና ሕዝቡን ለምን "አንነግሥም" አሉት? በኋላስ ለምን ነገሡ?

፫. ኢትዮጵያ የኢዛና ሀገር ትባል የነበረው ከምን የተነሳ ነው?

፬. የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ በማን ዘመን ተሾሙ? የየት ሀገር ሰውስ ነበሩ?

፭. ከ፭ኛው መቶ ክ/ዘመን በፊት ቤተክርስቲያን በምን ዜማ ትገለገል ነበር? ከዚያስ በኋላ?

፮. የኢትዮጵያውያን እምነት ከአብርሃ ወአጽብሐ ዘመን በኋላና በፊት ምን ዓይነት ገጽታ ነበረው?

፯. ተስዓቱ (፱) ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዕድገት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ አስረዳ/ጂ/።

፰. ምንኩስና በኢትዮጵያ የተጀመረው እንዴት ነበር?

፱. አባ ጰንጠሌዎን ያመነኮሰው ንጉሥ ለየትኛው ታሪኩ ይታወሳል?

፲. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን ቀኖና መሆኑን ከሚገልጹ ድርጊቶች ዋና ዋናዎችን ጥቀስ/ሺ/።

፲፩. በየዘመናቱ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ቅዱሳት/ን/ የተጋድሎ ታሪክ ምን ትምህርት አገኘህ/ሽ/።

፲፪. የኢትዮጵያ የክርስትና ታሪክ ከየትና እንዴት ተገኘ?

፲፫. በኢትዮጵያ የክርስትና ታሪክ ቀድመው የተጠመቁት አረማዊና ሌላው በዝቅተኛ ኑሮ ያለው ሕዝብ ሳይሆን ነገሥታቱ ነበሩ። ከሌሎች ሀገር ታሪክ አኳያ ከዚህ ምን ትረዳለህ(ሽ)።

፲፬. ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን የሚያመሳስላቸው ታሪክ ምን ነበር?

፲፭. በካቶሊካውያን ሤራ ተጋድሎን ከፈጸሙት ቅዱሳን አባቶች እና ቅዱሳት አንስት ውስጥ የሦስቱን ታሪክ በአጭሩ አብራራ/ሪ/።

፲፮. ከአራዊትና እንስሳት ጋር የተገናኘ ታሪክ ያላቸውን ቅዱሳን አበው እና ቅዱሳት አንስት ጥቀስ/ሺ/፤ ግንኙነታቸውንም አብራራ/ሪ/።

ምዕራፍ ዐራት

፩. የኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪክ ምንጮች

፩.፩. ገድል

ገድል ማለት ቅዱሳን ሰዎች ይህን ዓለም ንቀው ምረረ ገሃነምን አውቀው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሕግ አስገዝተው ከፍትወታት እኩያትና ከጸብአ አጋንንት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎና ያሸነፉበትን መንገድ የሚያሳይ በቅዱሳንም ሕይወት ጠቃሚ ትምህርት የሚያስጨብጥ መጽሐፍ ነው። የቅዱሳን ገድል ጌታ በወንጌል የተናገረው ቃልና ያዘዘው ትእዛዝ ሊፈጸም የሚችልና አማናዊ መሆኑን የሚያስረዳ ዝርዝራዊ ትርጓሜ ነው። ይኸውም ጌታ በዮሐንስ ወንጌል "በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ብሎ የተናገረውን ቃል ተፈጻሚነትና እውነተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ቅዱሳን ራሳቸውን ክደዋልና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ተችሏቸዋል። የራሱን ፈቃድ የካደ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም የሚያዳግተው አንዳች ነገር የለምና። ስለዚህ በጎ መዓዛ እንዳለው መሥዋዕት የሚጣፍጥ የሥራቸውን ነገር የሚዘረዝር መጽሐፍ ገድል ይባላል።** በመሆኑም ገድላት የቅዱሳንን ታሪክ የምናገኝባቸው ምንጮች ናቸው። ይልቁንም ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ታሪካቸው በሌሎች መዛግብት /encyclopedia/ ከሚገኘው ይልቅ ከገድላት የሚገኘው ይበልጣልና ግንባር ቀደም የቅዱሳን የታሪክ ምንጮች ሊባሉ ይችላሉ።

፩.፪. ስንክሳር

ስንክሳር ማለት ስብስብ ማለት ነው። ይህም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከአብ በባሕርይ መወለዱን ድኅረ ዓለም ያለ አባት በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ከጸናች ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ መወለዱን፣ የቅዱሳን ኃያላን መላእክትን ተራዳኢነት፣ የቅዱሳን ነቢያትንና ሐዋርያትን ተልእኮ፣ የቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታትን ተጋድሎ በጥቅሉ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ ሥራን አካቶ ቱእምራታቸውን ገድላቸውንና ትሩፋታቸውን የሚያዘክርና መታሰቢያቸውን አጠቃሎ የያዘ መድበል ነው። የመጽሐፈ ስንክሳር ምንጮች ብሉያትና ሐዲሳት መጻሕፍት ድርሳናትና ገድላት እንዲሁም የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የጻፏቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው። ይህንንም መጽሐፍ መጀመሪያ ያዘጋጁትና የሠሩት የአትሪብ ኤጲስ ቆጶስ አባ ሚካኤልና የበርለስ ኤጲስ ቆጶስ አባ ዮሐንስ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን አባቶችና መምህራን ናቸው። ከታሪክም መጨረሻ ታሪኩን ጠቅለል አድርጎ የሚያስረዳ በግጥም መልክ የተዘጋጀ አርኬ የሚባል ድርሰት አለ። በመሆኑም ስንክሳር ስለ ቅዱሳን ታሪክ የሚናገር መድበል ስለ ቅዱሳን ማወቅ ለሚፈልጉም መሠረታዊ ምንጭ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም።

፩.፫. የአብነት ት/ቤቶች ትውፊት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል እንደተናገረው ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራ ሊጻፍ፣ ተመዝግቦም ሊገኝ አይችልም። ዮሐ.፳፩፥፳፭ ይህም እግዚአብሔር አድሮባቸው ሥራ የሠራባቸው ቅዱሳን ሁሉም እንደማይታወቁ ያመለክተናል። ከእነዚህ በጽሑፍ ከማይታወቁት ቅዱሳን መካከል ከፊሎቹ ሊታወቁበት የሚችሉበት ተጨማሪ መንገድ ትውፊት ነው። መጻፍ የማይችሉ የቅዱሳኑ አርድእት (ረዳቶች) ከቅዱሳኑ ዕረፍት በፊትም ይሁን በኋላ ወደ ተለያዩ አብያተ ጉባኤያት በመግባት ስለቅዱሳኑ ስለሚናገሩ የብዙ ቅዱሳን ታሪክ በአብነት ትምህርት ቤቶች በቅብብል እየተነገረ ይገኛል። ይልቁንም ደግሞ የቅኔ እና የመጻሕፍት አብያተ ጉባኤያት የብዙ ቅዱሳን ታሪክ ስለሚተርኩ ስለቅዱሳን እንድናውቅ ተጨማሪ ምንጮች ሆነው አገልግለዋል። ስለዚህ የአብነት ት/ቤቶች ትውፊት ለቅዱሳን ታሪክ በምንጭነት ሊጠቀስ ብቁ ሆኖ እናገኘዋለን።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ /ጪ/።

፩. ስንክሳር ከገድል የሚለይበት ዐቢይ መንገድ ምንድነው?

፪. በአብነት ት/ቤት የሚነገሩ ትውፊቶችን ለቅዱሳን ታሪክ ምንጭነት የምንጠቀምበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አለ ወይ? ካለስ የቱ?

፫. ከኢትዮጵያውያን ቅዱሳት አንስት ገድላት ውስጥ ሁለቱን ይጥቀሱ

፬. መጽሐፈ ስንክሳርን ማዘጋጀት የጀመሩት ሁለቱ ኤጲስ ቆጶሳት እነማን ናቸው?

---
* [illegible]

** [illegible] ገጽ